ርየ ፡ መለኮት ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፤ በቅድምና ፡ የነ
በረ ፡ ወልድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ስለ ፡
ሰዎች ፡ እኛን ፡ ስለማዳን ፡ ከሰማያት ፡ ወርዶ ፡ ከአም
ላካዊ ፡ ባሕርዩ ፡ ሳይለይ ፤ የተዋሐደው ፡ ሥጋም ፤
መለኮትን ፡ ወደ ፡መሆን ፡ ምንም ፡ ምን፡ፈጽሞ ፡ ሳይ
ለወጥ ፡የምታውቅ፤የምትናገር ፡ነፍስ ፡ ያለችውን ፡
እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ እንላለን ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፫ ። ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፫ ።

፮ ፤ ወአስተዋሐዶ ፡ ህላዌሁ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡እም ፱ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ዘውእቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትስ ብእት ፡ ፍጹማን ፡ ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ አማኑኤል ፡ አም ላክነ ፡ ነአምን ፡ ቦቱ ፭ደ ፡ ወልዶ ፡ ወ፭ደ ፡ እግዚአ ዘበአማን ፡ ፭ደ ፡ አካለ ፡ ወ፭ደ ፡ ገጸ ፡ ወ፭ደ ፡ህላዌ ፡ ወ፭ደ ፡ መልክአ ፤ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ ወተሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ ዘበአማን ፡ ወኢንከፍሎ ፡ ኅበ ፡ ፱ቱ ፡ ህላዌ ያት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ወዘኢይ ትነገር ፡ እንበለ ፡ ቱሳሔ ፡ ወኢትድምርት ፡ ወኢው ላጤ ፡ ወኢተፈልጦ ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘኢይት ነገር ፡ ወይትዐዶ ፡ እምልቡና ፡ ወኢይረክቦ ፡ ሕሊና ፡ ሰብእ ፡ ዕጹብ ፡ ወመድምም ፡ ውእቱ ፡ መዋኤ ፡ ንባብ ፡ ወልቡና ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ።

፯ ፤ ከሁለት ፡ ባሕርያትም ፡ ያለ ፡ መለየት ፡ ባሕርዩን ፡ አንድ ፡ አደረገ ፤ እነዚህ ፡ ፍጹማን ፡ የሚሆኑ ፡ መለ ኮትና ፡ ትስብእት ፡ ናቸው ፤ አምላካችን ፡ አማኑኤል አንድ ፡ ነው ፤ በእውነት ፡ ፍጹም ፡ሥጋን ፤ ነፍስን ፡ ንሥቶ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ወልድ ፤ በው ነት ፡ አንድ ፡ ገዥ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ መልክ ፡ እንደሆነ ፡ እና ምንበታለን ፤ የሰው ፡ ሕሊና ፡ መርምሮ ፡ በማያገ ኘው ፤ ከልቡና ፡ በራቀ ፤በማይነገር ፡ድንቅ ፡ ሥራ ፡ መካፈል ፤ መለወጥ ፤ መደባለቅ ፤ መቀላቀል ፤ሳይኖር ከተደረገ ፤ከማይመረመር ፤ ከማይነገር ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላው ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፤ ሁለት ፡አካል ፡ብለን፡ አን ከፍለውም ፤ ልቡና ፡ የማይመረምረው ፡ አንደበት ፡ የማይናገረው ፡ረቂቅ ፤ ድንቅ ፡የባሕርይ ፡አምላክ ፡ነው ።

፰ ፤ ወናርሕቅ ፡ ዙሎ ፡ ጕልቍተ ፡ ህላዌ ፡ ዘመለኮት ። ወንዕቀብ ፡ ትሥልስተ ፡ አካላት ፡ ወገጻት ፡ ወን ንግር ፡ ተዋሕዶቶ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ዘኢይትፈለጥ ፡ ወዘኢይትበሀል ፡ ዘከመ ፡ እፎ ውእቱ ፡ ወተመሰለን ፡ በዙሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ተሠገወ ፡ ወፈጸመ ፡ ዙሉ ፡ ዘዚአነ ፡ ወኢተወለጠ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ለከዊነ ፡ መለኮት ፡ ወህላዌ ፡ መለኮትኒ ፡ ለከዊነ ፡ ሥጋ ፡ ወባሕቱ ፡ ለሊሁ ፡ ወረደ ፡ በፈቃዱ ፡ እምሰማያት ፡ ወተሠገወ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በዙሉ ፡ ጊዜ ፡ ማርያም ።

፱ ፤ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ ተራበ ፤ ተጠማ ፤ መንገድ ፡ በመ ሔድ ፡ ደከመ ፡ በጥፊ ፡ ተመታ ፤ ተገረፈ ፤ ተሰቀለ ፤ ሕይወትን ፡ የሚያድል ፡ እሱ ፤ በከበረ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ እጆቹን ፤ እግሮቹን ፡ ተቸነከረ ፤ እሱ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ቃል ፡ የማይታመም ፡ ሲሆን ፡ ታመመ ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ ሲሆን ፡ የማይሞተው ፡ ሞተ ።

፲ ፤ እመሰ ፡ መጽአ ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ፡ እፎኑ ፡ እም ኮነ ፡ ይደሉ ፡ ይንግእ ፡ ሕማመነ ፡ ወድካመነ ፡እመ ኢተዋሐደ ፡ በሥጋ ፡ ዘይትማሰለነ ፡ ወይትዔረየነ ፡ ሐማሚ ፡ ወመዋቲ ፡ ወሶበሂ ፡ ሐመ ፡ ኢተፈልጠ ፡ መለኮቱ ፡ እምትስብእቱ ፡ ወለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡ ወሰብእ ፡ ፍጹም ፡ ኅቡረ ፡ ተወ ክፈ ፡ ሕማመ ፡ በሥጋሁ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንትሜካህ ፡ በእንተ ፡ዘአግዐዘነ ፡እምቅኔ ፡ሞት ፡ ወዜ ወወ ፡ ሲያለ ፡ ወእንገፈነ ፡ እምእደ ፡ አጽራር ፡ ዘውእቶሙ ፡ ሞት ፡ ወሰይጣን ፡ ወአግዐዘነ ፡ እም ቅኔሆሙ ።

፲፩ ፤ ከአምላካዊ ፡ ክብሩም ፡ ፈጽሞ ፡ አልተለየም ፤በሐ ሱትም ፡ አልታመመም ፡ በእውነት ፡ ታመመ ፤እንጂ ፤ በእውነት ፡ ተራበ ፤ በእውነት ፡ ተጠማ ፤ ንጽሕት ድንግል ፡ ከምትሆን ፡ ከእናቱ ፡ ከእመቤታችን ፡ከቅ ድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕፀን ፡ በነሣው ፡ በዚህ ፡ ሥጋ ፡ በእውነት ፡ ደከመ ፤ የማይታመመው ፡ ታመመ ፤ የማይሞተውም ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋ ፡ሞተ ።

፲፪ ፤ ወኢዐረቀ ፡ እመንበሩ ፡ አምላካዊት ፡ ወኢተፈልጠ ፡ ለግሙራ ፡ ወኢሐመ ፡ በምትሀት ፡ አላ ፡ ሐመ ፡ እሙነ ፤ እሙነ ፡ ርኅበ ፡ ወእሙነ ፡ ጸምአ ፤ እሙነ ፡ ደክመ ፡ በዝንቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምከርሠ ፡ እሙ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ዘኢየሐምም ፡ ሐመ ፡ ወዘኢይመውት ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፩፲፫ ።

፲፪ ፤ ወእመሰ ፡ ንትአመን ፡ እምዝንቱ ፡ ካልአ ፡ እም ኢኮነ ፡ ግውዛነ ፡ እምዝንቱ ፡ ሕማም ፡ ወእምኢ ተፈታሕነ ፡ እማዕሰረ ፡ ሞት ፡ አላ ፡ እምኮነ ፡ ከመ ፡ ነኪራን ፡ ወርሑቃን ፡ እምጽድቀ ፡ ትንሣኤ ፡ ወእምተልሕኮ ፡ ዳግማዊት ፡ ወእመሰ ፡ ኢሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ በሞተ ፡ ዚአነ ፡ በእንተ ፡ ኃጣውኢነ ፡ ወኢሐመ ፡ በሥጋ ፡ ከመ ፡ ሕማምነ ፡ እምኢተግዕዝነ ፡ እመርገመ ፡ አበሳ ፡ ዘቦአ ፡ ባቲ ፡ አዳም ፡ አቡነ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ሠዐረ ፡ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ በትንሣኤሁ ፡ ማሕየዊት ፡ ወመድኃኒት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ አምላካዊ ።

፲፫ ፤ ውእቱሰ ፡ ኮነ ፡ ይትናገር ፡ በጥበብ ፡ ዘተነበየ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ዘኮኑ ፡ እምሥጋ ፡ ወደም ፡ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ በዝንቱ ፡ ፍኖት ፡ ወበዝንቱ ፡ አርአያ ፡ ተመሰለ ፡ ከመ ፡ ያብጥል ፡ በሞቱ ፡ ሞተ ፡ ወዘሎቱ ፡ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ ዘውእቱ ፡ ሰይጣን ፤ ኢነሥአ ፡ እመላእክት ፡ አምሳለ ፡ ወኢሥጋ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ደለዎ ፡ ከመ ፡ ይትመሰሎሙ ፡ ለአኃዊሁ ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ ወነሥአ ፡ ሥጋ ፡ ዘይትዔረየን ፡ ወየሐምም ፡ ዘከመ ፡ ሕማምነ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፩—፲፯ ።

፲፩ ፤ ወዝንቱ ፡ ዘእምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ወነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ እምኔሃ ፡ በፈቃዱ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያጌብሮ ፡ በእንቲአሃ ፡ ወገብረ ፡ ትእምርታተ ፡ አምላካዊ ፡ ወምግባራተ ፡ ሰብአዊ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ወትስብእቱ ፡ ውእቱ ፡ ይትናገር ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ወይገብር ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ተአምራተ ፡ ወጎይላተ ፡ ወይትዌከፍ ፡ ሕማማተ ፡ ወአኮ ፡ በተፈልጦ ፡ ህላዌ ፡ አምላካዊት ፡ እምሥጋ ፡ ሰብእዊት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ወዘኢይትነገር ፡ ወኢንፍልጥ ፡ ቃላተ ፡ ወምግባራተ ፡ ወሕማማተ ፡ በበይናን ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለመለኮት ፡ ወትስብእት ፡ አላ ፡ በኀዱ ፡ ህላዌ ፡ ወበኀዱ ፡ ገጽ ፡ ወበኀዱ ፡ አካል ።

፲፭ ፤ ወኢንብል ፡ ከመ ፡ ማኅበረ ፡ ኬልቄዶን ፡ ዐላውያን ፡ ወፀራፍያን ፡ ወኢንትአመን ፡ ከመ ፡ ልዮን ፡ ዘሮማ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያተ ፡ ወኢ፪ቱ ፡ አካላተ ፡ ወኢ፪ቱ ፡ ገጻተ ፡ ወኢ፪ቱ ፡ ምግባራተ ፡ ወኢ፪ቱ ፡ ሥምረታተ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ንርሕቅ ፡ እምዝንቱ ፡ ወንዘልፍ ፡ አለ ፡ ይብሉ ፡ እሎንተ ፡ ቃላተ ፡ ምኑናተ ፡ ንሕነሰ ፡ ኢነአምር ፡ በባዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ እንበለ ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካል ፡ ወ፩ዱ ፡ ገጽ ፤ ወእሉሰ ፡ ማኅበረ ፡ ኬልቄዶን ፡ ነበቡ ፡ ክንዶ ፡ ወመነኑ ፡ ጽድቀ ፡ ወወፅኡ ፡ እምሕግ ፡ ወፀረፉ ፡ ወሰመይዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ሃያማኖት ፡ ኦርቶዶክሳዊ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፩፲፫ ።

፲፪ ፤ ከዚህ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ ሃይማኖት ፡ ብናምንስ ፤ ከዚህ ፡ ሕማም ፡ ነፃ ፡ ባልሆንን ፡ ነበር ፤ ከሞት ፡ ቍራኝነ ትም ፡ ባልተላቀቅንም ፡ ነበር ፤ ከእውነተኛ ፡ ትንሣኤ ፡ ከሐዲስ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንደራቁ ፤ እንደ ፡ ተለዩ ፡ በሆነ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ ክርስቶስ ፡ የእኛን ፡ ኃጢአት ፡ ለማስተስረይ ፤ የእኛን ፡ ሞት ፡ ባይሞትስ ፡ ኖሮ ፤ በሥጋም ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሕማም ፡ ባይታመም ፡ ኖሮ ፤ አባታችን ፡ አዳም ፡ ተይዞባት ፡ ከነበረችው ፡ ከኃጢአት ፡ ፍዳ ፡ ባልዳንም ፡ ነበር ፤ ስለዚህም ፡ አምላክ ፡ ያደረበት ፡ ሐዋርያ ፡ እንደተናገረ ፤ በምታድን ፡ በምታከብር ፡ ትንሣኤው ፡ የሞትን ፡ ሥልጣን ፡ አጠፋ ።

፲፫ ፤ እሱ ፡ ጳውሎስ ፤ ልጆች ፡ ከሥጋ ፤ ከደም ፡ ተገኙ ፤ እሱም ፡ እንዲሁ ፡ በሞቱ ፡ ሞትን ፡ የሞት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሰይጣንንም ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፤ በዚህ ፡ መንገድ ፤ በዚህ ፡ አርአያ ፡ መሰላቸው ፤ መምሰልን ፤ ከአብርሃም ፡ ባሕርይ ፡ ነሣ ፡ እንጂ ፡ ከመላእክት ፡ ባሕርይ ፡ አልነሣም ፤ ስለዚህም ፤ የአብርሃም ፡ ልጆች የሆኑ ፡ ወንድሞቹን ፡ ይመስላቸው ፡ ዘንድ ፡ ተገባው ፡ እያለ ፡ በዕውቀት ፡ ይነግራቸው ፡ ነበር ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፤ እንደምንታመምም ፡ የሚታመም ፤ እኛን ፡ የሚመስል ፡ ሥጋን ፤ ነሣ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፩—፲፯ ።

፲፩ ፤ ይህም ፤ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃልን ፡ ከወለደችው ፡ ከእመቤታችን ፡ ከንጽሕት ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ ግድ ፡ ሰውን ፡ ያለው ፡ ሳይኖር ፡ ከእሷ ፡ በፈቃዱ ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ፤ ለመለኮትነት ፤ ለትስብእት ፡ እንደሚገባ ፡ ያለ ፡ መከፈል ፤ የአምላክነት ፤ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ አንጋገር ፡ ይናገራል ፤ አምላክ ፡ እንደ ፡ መሆኑም ፡ ሙት ፡ ያስነሣል ፤ ድውይ ፡ ይፈውሳል ፤ መከራም ፡ ይቀበላል ፤ ግን ፤ ከማይነገር ፤ ከማይመረመር ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አምላካዊት ፡ ባሕርይ ፤ ከሰብአዊት ፡ ባሕርይ ፡ ተለይታ ፡ አይደለም ፤ አንጋገሩን ፤ ሥራውን ፤ መከራውን ፡ ይህ ፡ ለመለኮት ፡ ይገባል ፤ ይህ ፡ ለትስብእት ፡ ይገባል ፡ እያልን ፡ በየራሳቸው ፡ አንለይ ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ በመሆን ፡ ሠራው ፡ እንበል ፡ እንጂ ።

፲፭ ፤ ከሐዲዎች ፤ ተሳዳቢዎች ፤ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ እንደሚሉት ፡ አንልም ፤ እንደ ፡ ሮም ፡ ሊቀ ፡ጳጳሳት ፡ እንደ ፡ ልዮን ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፤ ሁለት ፡ አካላት ፡ ሁለት ፡ ገጻት ፤ ሁለት ፡ ግብራት ፤ ሁለት ፡ ፈቃዳት ፡ ብለን ፡ አናምንም ፤ ስለዚህም ፡ ከዚህ ፡ ርቀን ፤ እነዚህን ፡ የተናቁ ፤ የተነቀፉ ፡ ቃላትን ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎችን ፡ እንቃወማለን ፤ እኛስ ፡ በፈጣሪያችን ፡ በክርስቶስ ፡ ከአንድ ፡ ባሕርይ ፤ ከአንድ ፡ አካል ፡ ከአንድ ፡ ገጽ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አናውቅም ፤ በኬልቄዶን ፡ የተሰበሰቡ ፡ እነዚህ ፡ መናፍቃን ፡ ግን ፤ እውነተኛውን ፡ ሃይማኖት ፡ ንቀው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ተናገሩ ፡ ከሕግም ወጡ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ካዱ ፤ ይህንንም ፡ ከሕዳጣቸውን ፡ የቀና ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ አሉት ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፲፫ ።

፲፯ ፤ ንሕነሰ ፡ ናወግዞሙ ፡ በሐጻ ፡ ንባብነ ፡ ወበቃልነ ገሃደ ፡ በአፉነ ፡ ወውሳጥያተ ፡ ሕሊናነ ፡ ወእምነትነ ፡ እስመ ፡ ሕዝብ ፡ መሪራን ፡ እሙንቱ ፡ ዘይከፍልዎ ፡ ለጸዲ ፡ ክርስቶስ ፡ ጎበ ፡ ፪ቱ ፡ ወናሴስል ፡ ዓዲ ፡ እከዮ ፡ ለልዮን ፡ ወንጎድፎ ፡ በሐጻ ፡ ግዘት ፡ ወንመትሮ ፡ በሰይፈ ፡ መለኮት ፡ ወከማሁ ፡ ለዙሎሙ ፡ አርሲሳን ፡ ተቃራንያን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ አምላክ ፡ እለ ፡ ይትአመኑ ፡ ፪ተ ፡ ጎላዌያተ ፡ ወፀተ ፡ አካላተ ፡ ወፀተ ፡ ገጸተ ፡ ወፀተ ፡ ፈቃዳተ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘውእቶሙ ፡ አፍሮጢኖስ ፡ ወጢማ ፡ ወጳውሎስ ፡ ሳምሳጢ ፡ ወአርዮስ ፡ ትያድርስ ፡ ወንስጥሮስ ፡ ወዋሊጦስ ፡ ስዱድ ፡ ወርሑቅ ፡ እምሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወእምስባሔ ፡ ንጹሕ ፡ ወግሁድ ፡ ዝኩ ፡ ዘኮነ ፡ ዐላዌ ፡ ወመስተጋዕዘ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተቃራኔ ፡ ለጽድቅ ።

፲፰ ፤ ወዓዲ ፡ ለአንርያና ፡ ወለታአድሪጦስ ፡ ወለአቡሊናርዮስ ፡ እምጣውና ፡ ወለእስክንድሮስ ፡ ዕቡይ ፡ ወላውቲኖስ ፡ ወኑሪ ፡ ወለዮንልንስ ፡ እለ ፡ አሕጕሉ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ሦክ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ፍሬ ፡ ወለቆድ ፡ ወለታሪብ ፡ ርኩሳን ፡ ወምኑናን ፡ ወለዮልያኖስ ፡ ፈረሳዊ ፡ ወለዙሎሙ ፡ ዐላውያን ፡ እለ ፡ ይክሕዱ ፡ ፲ተ ፡ ወፀተ ፡ ቃላተ ፡ ብሩሃተ ፡ ወርቱዐተ ፡ ዘበአማን ፡ ሕግ ፡ ጽድቅት ፡ እንተ ፡ ዘቅዱስ ፡ ወብፁዕ ፡ መምህረ ፡ ርትዕ ፡ ቁርሎስ ፡ ፍቁር ፡ ወቆላፋን ፡ አልባብሂ ፡ መስቱቃርናን ፡ እሉ ፡ አይሁድ ፡ ርኩሳን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ንስጥሮስ ፡ ወካልኣኒሁ ፡ ዘቃላቲሆሙ ፡ መስተቊጥዒተ ፡ እግዚአብሔር ወለኵሉ ፡ ዘይሰነዐዎሙ ፡ ወየጎብር ፡ ምስሌሆሙ ፡ በሃይማኖት ፡ ርኩስት ፡ ወበእከዮሙ ፡ ወበዕልወቶሙ ፡ መስተቃርንት ፡ ወስካረ ፡ ዕበዶሙ ፡ ምትሀታዊት ፡ እለ ፡ ሥጡማን ፡ በንዋመ ፡ ዕቅፍት ፡ ወዘይመስሎሙ ።

፲፱ ፤ ንሕነሰ ፡ ናወግዞሙ ፡ ወንመትሮሙ ፡ እምኔነ ፡ ለእሉ ፡ ዐላውያን ፡ ወለባውጢናስ ፡ ወለባስሊድስ ወለዘይኑን ፡ ወለማኒ ፡ ፋርሳዊ ፡ ወለአውሊናርዮስ ፡ ወለአውጣኪ ፡ አብድ ፡ ዘአልቦቱ ፡ አእምሮ ፡ ዝኩ ፡ ዘኢይደልዎ ፡ ይለቡ ፡ ወኢከመ ፡ ይምሀር ፡ ወምስለ ፡ ዓዲ ፡ ናወግዝ ፡ አርዮስሃ ፡ ወመቅዶንዮስሃ ፡ ወአውናምዮስሃ ፡ ወኵሎ ፡ ዘይመስሎሙ ፡ በዕልወት ፡ ወበካሕድ ፡ ወዘይተልዎሙ ፡ ወኩኑ ፡ እምኔሆሙ ፡ እሉ ፡ እለ ፡ ይትቃረኑ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ዕሩያነ ፡ ሀልዎ ፡ ወቅድምና ፡ ወኩነ ፡ ይትዐረወዩ ፡ በካሕያሙ ፡ ጸር ፡ ተጻባዕያን ፡ እሉ ፡ አብዳን ፡ እለ ይፈልጡ ፡ መለኮተ ፡ እምትስብእት ፡ በምግባሮሙ ፡ ሙስንት ፡ ወለትሥልስተ ፡ አካላት ፡ ወገጸት ፡ ያመጽኡ ፡ ትድምርተ ፡ ወለሀላዌ ፡ መለኮትኒ ፡ ፍልጠተ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፲፫ ።

፲፯ ፤ እኛ ፡ ግን ፤ በእንደበታችን ፤ በጎይለ ፡ ቃላችን ፡ ገልጠን ፡ በአፋችንም ፤ በልባችንም ፤ አምነን አውግዘን ፡ እንለያቸዋለን ፤ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ የሚከፍሉት ፡ የተረገሙ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸውና ፤ ዳግመኛም ፤ የልዮንን ፡ ከሕይት፡ በውግዘት ፡ እናርቃለን ፤ በውግዘት ፡ ፍለጻ ፡ እንነድፋዋለን ፤ በመለኮት ፡ ሰይፍም ፡ እንቈራርጠዋለን ፤ እንዲሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፤ ሁለት ፡ አካላት ፤ ሁለት ፡ ገጸት ፤ ሁለት ፡ ፈቃዳት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ የሚታመኑትን ፤ አምላክ ፡ ያላደረባቸው ፤ ተከራካሪዎች ፡ መናፍቃንን ፡ ሁሉ ፡ አውግዘን ፡ እንለያቸዋለን ፤ እነዚህም፡ አፍሮጢኖስና ፡ ጢማ ፤ ጳውሎስ ፡ ሳምሳጢና ፡ አርዮስ ፤ትያድርስ ፤ ንስጥሮስና ፡ ከምእመናን ፡ የተለየው ፤ አውነተኛውን ፡ ሃይማኖት ፤ ከማቅረብ ፤ የታወቀውንና ፡ ንጹሕ ፡ ምስጋናን ፡ ከማቅረብ ፡ የራቀው ፤ ያ ፡እውነትን ፡ የሚቃወምና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚሰድብ ፡ መናፍቅ ፡ ዋሊጦስ ፡ ናቸው ።

፲፰ ፤ ዳግመኛም ፤ አንርያንና ፡ ታአድሪጦስን ፤ የጣውና ፡ ሰው ፡ አቡሊናርዮስን ፤ ትዕቢተኛ ፡ እስክንድሮስን ፤ ፍሬ ፡ እንደሌለው ፡ እሾህ ፡ ነፍሳቸውን ፡ የጐዱ ፡ ላውቲኖስን ፤ ኑሪንና ፡ ዮልንዮስን ፤ የተናቁ ፤ የተዋረዱ ፡ ቆድንና ፡ ታሪብን ፤ ፈረሰኛ ፡ ዮልያኖስንም ፤ የቀናች ፡ ሃይማኖትን ፡ ያስተማረ ፤ የተወደደ ፤ የተመሰገነ ፡ ቅዱስ ፡ ቁርሎስ ፡ በውነት ፡ የተረዳች ፡ሕግ አድርጎ ፡ የሠራላቸውን ፤ የቀኑ ፤ ለሰው ፡ ዕውቀት ፡ የሚሆኑ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ግዘት ፡ የሚከዱ ፡መናፍቃንን ፡ ሁሉ ፡ እናወግዛቸዋለን ፤ልበ ፡ ደንቆሮ ችም ፡ እነዚህ ፡ ርኩሳን ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፤ እነዚህም ፡ ንስጥሮስና ፡ አነጋገራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምታሳዝነው ፡ ወገኖቹ ፡ ናቸው ፤ የሚተባበራቸውን ፤ በረከሰች ፡ ሃይማኖታቸውና ፡ በክፉ ፡ ትምህርታቸው ፤ ሃይማኖትን ፡ በምትቃወም ፡ ክሕደታቸውና ፡ ምትሀት ፡ በሆነች ፡ አእምሮ ፡ ማጣታቸው ከእነሱ፡ጋር ፡ አንድ ፡ የሚሆነው ፡ ሁሉ ፤ በክሕደት ፡ እንቅልፍ ፡ የተያዙትና ፡ የሚመስሏቸውም ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

፲፱ ፤ እነዚህን ፡ መናፍቃን ፤ ባውጢናስንና ፡ ባስሊድስን ፤ ዘይኑንና ፡ የፋርስ ፡ ማኒን ፤ አውሊናርዮስንና ፡ አእምሮ ፡ የሌለው ፤ ማወቅ ፤ ማስተማር ፡ የማይቻለው ፡ መናፍቅ ፡ አውጣኪን ፡አውግዘን ፡ እንለያቸዋለን ፤ ከእነዚህም ፡ ጋር ፡ ደግሞ ፡ አርዮስን ፡ መቅዶንዮስን ፤ አውናምዮስን ፤ በክሕደት ፡ የሚመስላቸውን ፤ አብነት ፡ አድርጎ ፡ የሚከተላቸውንም ፡ ሁሉ ፡ እናወግዛለን ፤ በቅድምና ፤ በመኖር ፤ አንድ ፡ የሚሆኑ ፤ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ የሚክዱ ፡ እነዚህ ፡ ከእነዚያ ፡ ተምረዋልና ፡ የሚደፋፈሩ ፡ ጠላቶች ፡ እነዚህ ፡ በክሕደታቸው ፡ አውሬ ፡ ሆነዋል ፤ በመጥፎ ፡ ሥራቸው ፡ መለኮትን ፡ ከትስብእት ፡ የሚለዩ ፤ በአካላት ፤ በገጻት ፡ ሦስትነት ፡ አንድነትን ፤ በመለኮት ፡ ባሕርይም ፡ መከፈልን ፡ የሚያስተምሩ ፡ እነዚህ ፡ ዐላዋቂዎች ፡ ናቸው ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፫ ። ም ፡ ፻፲፯ ።

፲፱ ፤ ንሕነሰ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ናርሕቅ ፡ እምኔነ ፡ እሎ ንተ ፡ እምነታተ ፡ ርኩሳተ ፡ ወንትዌከፍ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ዘኢይትፈለጥ ፡ ወዘኢይትከፈል ፡ ወዘኢይ ቶሳሕ ፡ ወንጸመድ ፡ በርትዕ ፡ ለሃይማኖት ፡ ጽድቅት ፡ እንተ ፡ ዘአበዊነ ፡ ርቱዐነ ፡ ሃይማኖት ፤ ንሰ ግድ ፡ ወንትቀነይ ፡ ለክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ዘአ ስተጋብአነ ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወቅድስት ፤ ወንገኒ ፡ ለመለኮተ ፡ አምላክነ ፡ ዘኢ ይትከፈል ፡ ወዘኢይትዌለጥ ፡ ወዓዲ ፡ ንትላጸቅ ፡ በጽድቀ ፡ ወንጌሉ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ በኪዳን ፡ ሐዲስ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ እምነትነ ፡ ላዕለ ፡ ቅድ ስት ፡ ሥላሴ ፡ በፍሥሓ ፡ ወበሐሜት ።

፳ ፤ ወንስእል ፡ ለነገሥትነ ፡ ምእመናን ፡ ከመ ፡ የሀ ቡሙ ፡ ሥልጣነ ፡ ውኅይለ ፡ ወመዊአ ፡ ወለዙሉ ፡ ዓለም ፡ ማህለ ፡ ወምሕረተ ፡ ወለአብያተ ፡ ክርስቲ ያናትሂ ፡ ወለምኔታት ፡ ዛኅነ ፡ ወመርሰ ፡ ሰላመ ፡ ወህድአተ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ለዓ ለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፻፲፬ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

፩ ፤ እመልእከተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአብ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእንጾኪያ ፡ ወሀገረ ፡ ምሥራቅ ፡ ወእለ ፡ ምስሌሃ ፡ ኅበ ፡ አባ ፡ አኪርስ ቶዶሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ወግብጽ ፡ ወኖባ ፡ ወኢትዮጵያ ፡ ወምዕራብ ፤ ናሁ ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ በልብ ፡ ወበአእምሮ ፡ ወል ባቄ ፡ እምኵሉ ፡ ነፍስ ፡ እምነተ ፡ ጽድቅተ ፡ዘይ ደሉ ፡ ላዕለ ፡ ሃይማኖት ፡ ክብርት ፡ ዘትትሌዐል ፡ እምኵሉ ፡ ክብር ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፪ ፤ ሥላሴ ፡ በተዋሕዶ ፡ ልዑላን ፡ ወቀዳማውያን ፡ ዕሩ ያን ፡ ህላዌ ፡ ወዕሩያን ፡ መለኮት ፡ ወኅይል ፡ በአ ሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወበፈዱ ፡ ፈቃድ ፡ ወበአሐቲ ፡ ሥምረት ፡ ወበፈጢረ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ቦቱ ፡ አካላት ፡ ወቦቱ ፡ ገጸት ፡ ቅዱሳን ፡ ወፍጹማን ፡ወአ ልቦ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ሕጸት ፡ ወኢፍድፋዴ ፡ አላ ፡ ፍጹማን ፡ ወዕሩያን ፡ እሙንቱ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወኵሉ ፡ ለለፈዱ ፡ ፈዱ ፡ እምአካላት ፡ ህልዋን ፡ በበ አካላቲሆሙ ፡ ኅቡራን ፡ ህላዌ ፡ ወመለኮት ፡ እን በለ ፡ ተፈልጦ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ወላዲ ፡ ወዘተወልደ ፡ ወዘሠረጸ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፫ ። ም ፡ ፻፲፯ ።

፲፱ ፤ አርቶዶክሳውያን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ የረከሱ ፡ እምነቶችን ፡ ከእኛ ፡ እናርቃለን ፤ የማይሰይ ፤ የማይ ከፈል ፤ የማይቀላቀል ፤ ተዋሕዶን ፡ እናምናለን ፤ ሃይማኖታቸው ፡ የቀናች ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ላመኑባት ፤ ለተረዳች ፡ ሃይማኖት ፡ በቅን ፡ እናገለ ግላለን ፤ በዚች ፡ በተመረጠች ፤ በከበረች ፡ ሃይማ ኖት ፡ አንድ ፡ ላደረገን ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንገዛለን ፤ እንሰግዳለን ፤ የማይከፈል ፤ የማይለወጥ ፡ የሆነ ፡ የፈጣሪያችንን ፡ ባሕርይ ፡ እናምናለን ፡ ዳግመኛ ፤ በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ሆነን ፡ ለዘላለሙ ፡ በወንጌል ፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፤ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ብለን ፡ የምናምነው ፡ እምነት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፳ ፤ ለታመኑ ፡ ነገሥታት ፤ ሥልጣንን ፤ ኃይልን ፤ ድል ፡ መንሣትን ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፤ ለዓለሙም ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታን ፤ ቸርነትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፤ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፤ ለገዳማትም ፤ ጸዋታን ፤ ርካታን ፤ ፍቅርን ፤ አንድነትን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እንለምን ፡ አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፻፲፬ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

፩ ፤ የአንጾኪያ ፤ የሶርያ ፤ የባቢሎን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡አባ ዮሐንስ ፡ የእስክንድርያ ፤ የግብጽ ፡ የኖባ ፤ የኢት ዮጵያ ፤ የስናር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ሚሆን ፡ወደ አባ ፡ አኪርስቶዶሎስ ፡ ከላከው ፡ መልእክቱ ፤ በልብ ፤ በዕውቀት ፤ ከፍጥረትም ፡ ሁሉ ፡ በተለየ ፡ ማስተ ዋል ፤ ከክብር ፡ ሁሉ ፡ ለምትበልጥ ፡ ለከበረች ፡ሃይ ማኖት ፡ እንደሚገባ ፡ የተረዳች ፡ እምነትን ፡ በአብ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናምናለን ፤ እንታ መናለን ።

፪ ፤ ሥላሴ ፡ በአንድነት ፡ የማይመረመሩ ፡ ቀዳማውያን ፡ ናቸው ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ በመለኮት ፡ በኅይል ፤ በአንዲት ፡ ሥልጣን ፤ በአንድ ፡ ፈቃድ ፤ በአንዲት ፡ ውድ ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመፍጠር ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ ሦስቱ ፡ አካላት ፤ ሦስቱ ፡ ገጸት ፡ ፍጹማን ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ፡ በእነሱ ፡ ማነስ ፡ መብ ዛት ፡ የለባቸውም ፤ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ የተካከሉ ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ፤ እንጂ ፤ ከአካላት ፡ እያንዳንዱ ፡ ሁሉም ፡ በየአካላቸው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ ባለመ ለየት ፡ በባሕርይ ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ እነ ዚህም ፤ የወለደ ፡ አብ ፤ የተወለደ ፡ ወልድ ፤ የሠ ፈጸ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፲፱ ።

፫ ፩ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ አብ ፡ ኢተወልደ ፡ እምካልእ ፡ ወኢ ይነሥእ ፡ ልደተ ፡ እምካልእ ፤ ወ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ ዓዲመ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ፡ ቀዳማውያን ፡ እሙንቱ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወህልዋን ፡ አልቦሙ ፡ ጥንት ፡ ወኢይትዌሰኑ ፡ ኢፍጡራን ፡ ወኢግቡራን ፡ አላ ፡ ፈጣርያነ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ኢይተረክቡ ፡ በህላዌ ፡ ወኢይበጽሑሙ ፡ አእምሮተ ፡ ሰብእ ፡ ወዘእንበለ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ኢኮነ ፡ ምንትኒ ፡ እምዝኮነ ፡ ፫ቱ ፡ ቅዳሴያት ፡ እስትጉቡአን ፡ ዘይ ሴብሕዎሙ ፡ ሱራፌል ፡ ለእሉ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ቅዱሳን ፡ ወዘንተ ፡ ለበውነ ፡ እምቃሉ ፡ ዐቢይ ፡ ወክቡር ፡ አትናቴዎስ ፡ ዘይቤ ፡ ወዓዲ ፡ ነአምን፡ ወንትአመን ፡ እምኵሉ ፡ ነፍስ ፡ በ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ እንተ ፡ ዘእሉ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ቅዱሳን ፡ ወአልቦ ፡ ውፁእ ፡ ምንትኒ ፡ እምእሉ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ እንዘ ፡ አሐቲ ፡ መንግሥት ፡ ወ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ ወአሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ።

፬ ፩ ወብፁዕስ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ይሜህረነ ፡ በድ ርሳኑ ፡ በእንተ ፡ ልደት ፡ ወዓዲ ፡ በእንተ ፡ ጥምቀት ፡ ከመዝ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ወሶበ ፡ ንቤ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ንብል ፡ በእንተ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ በሥላሴ ፡ ወሥላሴ ፡ በተዋሕዶ ፡ ወሶበኂ ፡ ንቤ ፡ ፫ቱ ፡ አካላተ ፡ ለለ ኵሉ ፡ አካላት ፡ በበአካላቲሆሙ ፡ ንቤ ፡ ባሕርየ ፡ ፍጹመ ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ እንተ ፡ ዘቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ወ፫ቱ ፡ ገጻት ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ መንግሥት ፡ ወ፩ዱ ፡ ዕበይ ፡ ወአሐቲ ፡ ክብር ።

፭ ፩ ይትበህል ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ አካላት ፡ አብ ፡ ብርሃን ፡ ወልድ ፡ ብርሃን ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብርሃን ፡ ዳእሙ ፡ ፩ዱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይትከፈል ፡ ወኢይት ዌለጥ ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወዓዲ ፡ ንብል ፡ አብ ፡ ሕይወት ፡ ወልድ ፡ ሕይወት ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕይወት ፡ እንዘ ፡ ፩ዱ ፡ ሕይወት ፡ በህላዌ ፡ መለ ኮት ።

፮ ፩ ወካዕበ ፡ ይትበህል ፡ አብ ፡ ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ፩ዱ ፡ ወመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ ውአቱ ፡ ወለለ፩ዱ ፡ እምአካ ላት ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ እሙንቱ ፡ ወኢይትበህሉ ፡ ፫ተ ፡ አማልክተ ፡ ወአኮ ፡ እምነትነ ፡ በ፫ቱ ፡ ዕደው ፡ ወ፫ቱ ፡ አማልክት ፡ ወኢበ፫ቱ ፡ መለኮት ፡ አላ ፡ ነአምን ፡ በ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ወ፫ቱ ፡ ገጻት ፡ ፍጹማን ፡ ወበ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ወበ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወበእንተ ፡ አካላትሰ ፡ ፫ቱ ፡ ወ፫ቱ ፡ ገጻት ፡ እንተ ፡ ዘ፩ዱ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ በስም ፡ ወበግ ግባር ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፲፱ ።

፫ ፩ አብ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከሌላ ፡ አልተ ገኘም ፤ ከሌላም ፡ ልደትን ፡ ገንዘብ ፡ አያደርግም ፤ ከአብ ፡ የተወለደ ፡ ወልድም ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከአብ ፡ የሠረጸ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ከአብ ፡ ጋር ፡ ጥንት ፡ የነበሩ ፡ ዛሬም ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ተገኙ ፡ አይባሉም ፡ አይወሰኑም ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የተፈጠሩ ፡ አይደሉም ፤ በባሕርይ ፡ አይመረመሩም ፤ የሰው ፡ ዕውቀትም ፡ መርምሮ ፡ አይደርስባቸውም ፤ ከተፈጠረው ፡ ፍጥ ረት ፡ ሁሉ ፡ ሥላሴ ፡ ያልፈጠሩት ፡ የለም ፤ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ ሱራፌል ፡ የሚያመሰግኑ ባቸው ፡ ሦስቱ ፡ ቅዳሴያት ፡ በምሥጢር ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ ይህንንም ፡ የእነዚህ ፡ የሦስቱ ፡ ቅዱሳት ፡ አካላት ፡ ገንዘብ ፡ የሚሆን ፡ ባሕርይ ፤ መለኮት ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ በነፍስ ፤ በሥጋ ፡ እናምናለን ፤ እንታመናለን ፤ ብሎ ፡ ደገኛው ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴ ዎስ ፡ በተናገረው ፡ አነጋገር ፡ ዐወቅን ፤ አንዲት ፤ መንግሥት ፤ አንድ ፡ መለኮት ፡ አንዲት ፤ ሥልጣን ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ ከእነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ ምንም ፡ የሚለይ ፡ የለም ።

፬ ፩ የተመሰገነ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስም ፡ የልደትን ፤ እን ዲሁም ፡ የጥምቀትን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ ድርሳኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፤ አብ ፡ ስለ ፡ ወልድ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንናገራለን ፤ አንድ ፡ መለ ኮት ፤ በሦስትነት ፤ ሦስትነትም ፡ በአንድ ፡ መለ ኮት ፡ አለ ፤ በየአካላቸው ፡ ያሉ ፡ አካላትንም ፡ እያን ዳንዳቸው ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፤ የማይከፈል ፡ ባሕርይን ፡ መናገራችን ፡ ነው ፤ ልዩ ፡ የሚሆኑ ፡ የሦስቱ ፡ አካላት ፡ ባሕርይም ፡ አንድ ነው ፤ አካላት ፤ ገጻት ፡ ሦስት ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ ባሕ ርይ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ መንግሥትም ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ጌትነትም ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ክብርም ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ ያስረዳናል ።

፭ ፩ ስለነዚህም ፡ አካላት ፤ አብ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ ወልድ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ፤ ነገር ፡ ግን ፤ በመለኮት ፡ ባሕ ርይ ፡ የማይከፈል ፤ የማይለወጥ ፡ አንድ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ ዳግመኛ ፡ በመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ሕይ ወት ፡ ሲሆን ፤ አብ ፡ ሕይወት ፡ ነው ፤ ወልድ ፡ ሕይ ወት ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሕይወት ፡ ነው እንላለን ፡

፮ ፩ ዳግመኛ ፤ አብ ፡ አንድ ፡ ይባላል ፤ ወልድም ፡ አንድ ፡ ይባላል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አንድ ፡ ይባላል ፤ ከአ ካላት ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ናቸው ፤ ግን ፤ ሦስት ፡ አማልክት አይባሉም ፡ ማመናችንም ፡ እንደ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ሦስት ፡ አማልክት ፡ ብለን ፡ ሦስት ፡ መለኮት ፡ አይ ደለም ፤ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ በሦስቱ ፡ አካላት ፡ በሦስቱ ፡ ገጻት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ መለኮት ፡ ብለን ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፤ ስለ ፡ ሦስቱ ፡ አካላትም ፡ የአ ንድ ፡ ባሕርየ ፡ መኮት ፡ ገንዘብ ፡ የሚሆን ፡ ገጻት ፡ በስም ፡ በግብር ፡ ሦስት ፡ ናቸው ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

፯ ፤ ከመዝ ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፤ ወአኮ ፡ ከመ ፡ እምነተ ፡ ሰባልዮስ ፡ ረሲዕ ፡ ዘይትአመን ፡ እምነተ ፡ ሙስንተ ፡ በፎዱ ፡ አካል ፡ ወሰመየ ፡ አስማተ ፡ ባሕቲቱ ፡ በከመ ፡ ንባቡ ፡ ርኩስት ፡ ዘይቤ ፡ ፎዱ ፡ አካል ፡ ወፎቱ ፡ አስማት ፡ ዕሩቃን ፡ በተውላጣት ፡ ዘይቄልጦሙ ፤ በበዘመን ፡ ቦ ፡ አመ ፡ ይሰምዮ ፡ ለአብ ፡ አበ ፡ ወቦ ፡ አመ ፡ ይሰምዮ ፡ ወልደ ፡ ወቦ ፡ አመ ፡ ይሰምዮ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወኢከመ ፡ እምነተ ፡ አርዮስ ፡ ወአውናምዮስ ፡ እለ ፡ ተህበሉ ፡ ወዐለዉ ፡ ወረሰዩ ፡ ህላዌያተ ፡ ፍሉጣተ ፡ ለአካለ ፡ መለኮት ፡ ወይቤሉ ፡ እግዚእ ፡ ወፈጣሪ ፡ ወፍጡር ፡ ወሠርው ፡ አግልክታተ ፡ ፍሉጣተ ፡ በውሳኔ ፡ ለዘኢይትቄሰን ፡ በክሕደት ፡ ወዕልወት ፡ ወአብኡ ፡ ማእከለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መዋዕላተ ፡ ርሑቃተ ።

፰ ፤ ወለነሰ ፡ ለክርስቲያን ፡ እምነትነ ፡ ጽዱቅ ፡ ርሑቅ ፡ ውእቱ ፡ ጥቀ ፡ እምዝንቱ ፡ ንባብ ፡ ርኩስ ፡ ወዕልወተ ፡ አቡሊናርዮስ ፡ ዕልው ፡ ከሐዲ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአምጽአ ፡ ላዕለ ፡ መለኮት ፡ መዐርጋተ ፡ ፍሉጣተ ፤ ወከሂለ ፡ በብሂሎቱ ፡ ዐቢይ ፡ ወዘየዐቢ ፡ እምኔሁ ፡ ወዘይፈደፍድ ፡ በዕበይ ፡ ፎዱ ፡ ይቀድም ፡ እምካልኡ ፡ ወካልኡ ፡ እምሣልሱ ፡ ወአምጽአ ፡ ፍልጠተ ፡ ላዕለ ፡ ዕሪና ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወለነሰ ፡ እምነትነ ፡ ርሑቅ ፡ እምእምነተ ፡ እሉ ፡ ዐሳውያን ፡ ወእምክሕደቶ ፡ መቅዶንዮስ ፡ ዘፀረፈ ፡ ላዕለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሰመዮ ፡ ፍጡረ ፡ በክሕደት ፡ ሰይጣናዊ ፡ ተቀዋሚ ፡ ወንጌል ፡ ወኢፈርሀ ፡ እምቃሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ ዘሰ ፡ ፀረፈ ፡ ላዕለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይትነደግ ፡ ሎቱ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወኢበዘይመጽእ ፡ ወእምትሩፋተ ፡ ቃል ክሙ ፡ ማሕየዊ ፡ ወትምህርትክሙ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ዘከርነ ፡ እሎንተ ፡ ቃላተ ፡ ሕጹጸተ ፡ በእምነት ፡ ርትዕት ፡ ወበልቡና ፡ አምላካዊ ፡ ወበነሢእ ፡ እእምሮ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ በሎሉ ፡ ግብር ።

፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ ንትመየጥ ፡ ወንንግር ፡ በእንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፎዱ ፡ እምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ዘንሰግድ ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ ቀዲሙ ፡ እንበለ ፡ ወሰን ፡ ወዘእንበለ ፡ ድካም ፡ ዘእንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ወተከፍሎ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምዙሉ ፡ አምሳል ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወቦቱ ፡ ኮነ ፡ ዙሉ ፡ አዝማን ፡ ዘነለፈ ፡ ወዓዲ ፡ ቦቱ ፡ ይከውን ፡ ዙሉ ፡ መዋዕል ፡ ዘተወሰነ ፡ ወቦቱ ፡ ይከውን ፡ ዓለምሂ ፡ ዘይመጽእ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

፯ ፤ እንዲህ ፡ እናምናለን ፤ እንታመናለን ፤ አንድ ፡ አካል ፡ ብሎ ፡ የረከሰ ፡ እምነትን ፡ እንደሚያምን ፡ እንደ ፡ ከሐዲ ፡ ሰባልዮስ ፡ እምነት ፡ አይደለም ፡ እሱ ፡ በረከሰች ፡ አነጋገሩ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ስሞች ፡ ግን ፤ በየዘመኑ ፡ በሚአመጣው ፡ መለዋወጥ ፡ ብቻ ፡ የሚለዋወጡ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ፡ ይላል ፡ አብን ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አብ ፡ ይለዋል ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወልድ ፡ ይለዋል ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይለዋል ፤ ደፍረው ፤ ክደው ፤ ገሹ ፤ ፈጣሪ ፤ ፍጡር ፡ ብለው ፡ ለአካለ ፡ መለኮት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባሕርያትን ፡ የሰጡ ፤ በፍጹም ፡ ክሕደት ፡ የማይወሰነውን ፡ ወሰነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አግልክትን ፡ የሠሩ ፤ በአብ ፤ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መካከል ፤ በዘመን ፡ መራራቅ ፡ እንዳለ ፡ የተናገሩ ፡ አርዮስና ፡ አውናምዮስ ፡ እንደሚያምኑት ፡ እምነትም ፡ አይደለም ።

፰ ፤ የእኛ ፡ የክርስቲያን ፡ የተረዳ ፡ እምነታችን ፡ ግን ፤ ከዚህ ፡ ከተነቀፈ ፡ ከአርዮስና ፡ ከሰባልዮስ ፡ አነጋገር አንድ ፡ ታላቅ ፤ ከእሱም ፡ የሚበልጥ ፤ ከዚያም ፡ በክብር ፡ የሚበልጥ ፡ አለ ፤ አንዱ ፡ ከሁለተኛው ፡ ሁለተኛው ፡ ከሦስተኛው ፡ ይቀድማል ፡ በማለቱ ፡ በመለኮት ፡ የመዓርግ ፤ የሥልጣን ፡ መለያየትን ፡ ያመጣ ፡ በሦስቱ ፡ አካላት ፡ ባሕርይ ፡ አንድነትም፡ መከፋፈልን ፡ ያመጣ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የካደ ፡ ርኩስ ፡ አቡሊናርዮስም ፡ ከተናገረው ፡ ክሕደት ፡ ፈጽሞ ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ የእኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ፤እነዚህ ፡ መናፍቃን ፡ ከሚያምኑት ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን የነቀፈ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፤ በሚመጣውም፡ዓለም፡ኃጢአቱ ፡ አይሰረይለትም ። ሲል ፡ ጌታችን ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ሳይፈራ ፡ ወንጌልን ፡ የሚቃወም ፡ ሰይጣን ፡ በአስተማረው ፡ ሐሰት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የካደ ፤ ፍጡርም ፡ ያለው ፡ ርኩስ ፡ መቅዶንዮስ ከተናገረው ፡ ክሕደትም ፡ ፈጽሞ ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ በሥራ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ዕውቀትን ፡ ገንዘብ ፡ በማድረግ ፡ አምላክ ፡ በገለጠልን ፡ ዕውቀት ፤ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ሆነን ፡ ከሚያደን ፡ ከፍጹም ፡ ነገራችሁ ፤ ከሐዋርያዊ ፡ ትምህርታችሁ ፡ የተነሣ ፡ እነዚህን ፡ ጥቂቶች ፡ ቃላትን ፡ ተናገርን ።

፱ ፤ የምንሰግድለት ፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ የመሆኑን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ መናገር ፡ እንመለስ ፡ ዘመን ፡ ሳይወሰነው ፤ ተድኅሮ ፤ ተፈልጦ ፤ ተከፍሎ ሳይኖርበት ፡ አስቀድሞ ፡ ከአብ ፡ የተወለደ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ይህን ፡ ያህላል ፤ ይህን ፡ ይመስላል ፡ ከመባል ፡ የራቀ ፡ አምላክ ፡ ቃል፡ ሲሆን ፤ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፤ በእሱ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ ዓለም ፡ ሊኖርበት ፡ የተወሰነውም ፡ ዘመን ፡ በእሱ ፡ ይወሰናል ፤ ዘላለም ፡ ለመኖር ፡ የሚመጣው ፡ ዓለምም ፡ በእሱ ፡ ይገኛል ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

፲ ፡ ወኢኮነ ፡ ፍሉጠ ፡ ማእከለ ፡ አዝማን ፡ ዘነሰፈ ፡ ወኢድኅረ ፡ ዘመን ፡ ዘተወከፍናሁ ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ጎይሉ ፡ ወጥበቡ ፡ ውእቱ ፡ ለአብ ፡ ወብርሃኑ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወአምሳለ ፡ አካሉ ፡ ወበዝንቱ ፡ ይትሌበው ፡ ልደቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ በክብር ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጎድጓድ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩-፲፰ ።

፲፩ ፡ ወከማሁ ፡ በዓለ ፡ ምሥጢራተ ፡ መንፈስ ፡ ጸውሎስ ፡ ጎሩይ ፡ ዘውእቱ ፡ መሠረተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይቤ ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ዘመን ፡ መጽአ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወለሐድሶትነ ፡ ወከመ ፡ ይሚጠነ ፡ ጎበ ፡ ዐቅምነ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ተሠገወ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ወዝኬ ፡ ውእቱ ፡ እምአመ ፡ ይቤላ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ለድንግል ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌኪ ፡ ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ በቅጽበት ፡ ኮነ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትፈለጥ ፡ ወዘኢይትነከር ፡ ወዘኢይትሌበው ፡ ወባሕቱ ፡ በከመ ፡ የአምር ፡ ለሊሁ ፡ ተሠገወ ፡ እንዘ ፡ ኢየአምር ፡ መኑሂ ፡ ወኢይክል ፡ ፈክሮ ፡ ከዋኔሁ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ መለኮት ፡ ቅዱስ ፡ እምትስብእተ ፡ ቃል ፡ ዋሕድ ፡ ወቀዲሙ ፡ ነበረ ፡ እንበለ ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሶበ ፡ ሠምረ ፡ ወፈቀደ ፡ ለሊሁ ፡ ተሠገወ ፡ ወኢኮነ ፡ ፍሉጠ ፡ እምሥጋ ፡ አላ ፡ ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ እም፪ቱ ፡ መለኮት ፡ ፍጹም ፡ ወትስብእት ፡ ፍጹም ፡ በ፭ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፭ዱ ፡ አካል ፡ ወ፭ዱ ፡ ገጽ ፡ ዘተሠገወ ፡ ወአኮ ፡ እመንገለ ፡ ተፈልጦተ ፡ ህላዌያት ፡ አለ ፡ ይትጋብኡ ፡ በተዋሕዶ ፡ ይከውን ፡ ፪ተ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ፭ደ ፡ ወኢፈለሰ ፡ እምህላዌሁ ፡ ወኢተወለጠ ፡ ለግሙራ ።

፲፪ ፡ ወሶበሂ ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ ኢተወለጠ ፡ እምዘነበረ ፡ ቦቱ ፡ ቀዳሚ ፡ አላ ፡ ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ወአልቦሙ ፡ ፍልጣን ፡ ለግሙራ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ወሶበ ፡ ጠየቀ ፡ ልቡና ፡ ተዋሕዶተ ፡ ዝንቱ ፡ ወይቤ ፡ ፭ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፭ዱ ፡ አካል ፡ ወ፭ዱ ፡ ገጽ ፡ አኮ ፡ ዘይከልእ ፡ ዝንቱ ፡ ትሥጉተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘውእቱ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ሥጋ ፡ አላ ፡ ናፍጥን ፡ በልባዌ ፡ ጎበ ፡ አእምሮተ ፡ ተዋሕዶ ፡ እምነ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ጎቡረ ፡ በ፭ዱ ፡ ገጽ ፡ ወበ፭ዱ ፡ አካል ፡ ወበ፭ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወይሰመይ ፡ እንስሳ ፡ ነባቤ ፡ ዘውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ እንዘ ፡ ኢይትዌለጥ ፡ ወኢይትመየጥ ፡ ተዋሕደ ፡ በሥጋ ፡ በ፭ዱ ፡ አካል ፡ ወ፭ዱ ፡ ህላዌ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

፲ ፡ በአለፈው ፡ ዘመን ፡ መካከል ፡ ያልነበረ ፡ አይደለም ፤ ከዘመን ፡ በኋላ ፡ ተገኝቶ ፡ ያመንነው ፡ አይደለም ፡ ወልድም ፡ የአብ ፡ ጥበቡ ፡ ጎይሉ ፡ ነውና ፡ መታወቂያው ፤ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ እንደ ፡ አብ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ፤ ለመለኮት ፡ በሚገባ ፡ ክብር ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሚሆን በት ፤ ጥንት ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ቀዳማዊ ፡ ልደቱም ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፤ ወልደ ፡ ነጎድጓድ ፡ የተባለ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፰ ።

፲፩ ፡ እንዲሁም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፤ መንፈሳዊ ፡ ምሥጢር ፡ የተገለጸለት ፤ የተመረጠ ፡ ጳውሎስም ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፤ እኛን ፡ ለማክበር ፤ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ክብራችንም ፡ ለመመለስ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ነፍስን ፤ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ድንግልን ፤ እግዚአብሔር ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ካላት ፡ ጊዜ ፡ ዝምሮ ፡ ነው ፤ በዚያች ፡ ሰዓትም ፡ ሊለይ ፡ የማይቻል ፡ የማይነገር ፤ የማይመረመር ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ጥቅሻ ፡ ፈጥሮ ፤ ተደረገ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ሳያውቀው ፤ ሁኔታውንም ፡ ሊረዳ ፡ ሳይችል ፡ እሱ ፡ ባወቀ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ስለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ መለኮት ፤ ዋሕድ ፡ ቃል ፡ ከነሣው ፡ ሥጋ ፡ አይለይም ፤ ቀድሞ ፤ እንደ ፡ አብ ፤ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋን ፡ ሳይዋሐድ ፡ ነበረ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እሱ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ከሥጋ ፡ የተለየ ፡ አይደለም ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ በመሆኑ ፡ ከፍጹም ፡ መለኮት ፤ ከፍጹም ፡ ትስብእት ፡ ከሁለቱ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ የሆኑ ፡ ባሕርያት ፡ ካለመቀላቀላቸው ፡ የተነሣ ፡ ሁለት ፡ አይባልም ፤ አንድ ፡ ሆኖአልና ፡ መቸም ፡ መች ፡ ባሕርዩን ፡ አልለቀቀም ፤ አልተለወጠም ።

፲፪ ፡ ሥጋንም ፡ በነሣ ፡ ጊዜ ፤ ቀድሞ ፡ ከነበረበት ፡ ባሕርዩ ፡ አልተለወጠም ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ መለየት ፡ የለባቸውም ፤ ልቡና ፡ የእሱን ፡ ተዋሕዶ ፡ ቢረዳ ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ ቢልም ፤ ይህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ የሚከለክል ፡ አይደለም ፤ ይኸውም ፡ ሥጋን ፡ መዋሐዱ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፤ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በመሆኑ ፡ አንድ ፡ ከሆኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ባሕርያት ፡ አንድ ፡ መሆኑን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ በማስተዋል ፡ እናፋጥን ፤ ነባቢ ፡ እንስሳ ፡ ይባላል ፤ ይኸውም ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፤ የአምላክ ፡ ልጅ ፡ ቃል ፡ ሳይለወጥ ፤ ባሕርዩን ፡ ሳይለቅ ፡ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በመሆን ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፩፲፬ ።

፲፫ ፤ ወተሰምየ ፡ ስሙ ፡ ዐማኑኤልሃ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ አምላክነ ፡ ምስሌነ ፤ ወውእቱ ፡ ፭ዱ ፡ ገጽ ፡ ወ፭ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፭ዱ ፡ አካል ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተ ሠገወ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢትድምርት ፡ ወኢቱ ሳሔ ፡ ዘእንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ ህላ ዌያት ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይት ክፈል ፡ ዘውእቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡ ወተ ዋሐደ ፡ ረቂቅ ፡ በሥጋ ፡ ገዚፍ ፡ ምስለ ፡ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ እንተ ፡ አልቦቱ ፡ ነውር ፡ ዘእንበለ ፡ ፍል ጠት ፡ ወኢውላጤ ፡ ወኢዘከረ ፡ መጽሐፍ ፡ ፪ተ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወዘኢይትዌ ሰን ፡ ወለብሰ ፡ ሥጋ ፡ መዋቲ ፡ እሙነ ፡ ወኢኮነ ፡ ምትሀተ ፡ ወኢነሥአ ፡ ክፍለ ፡ እምኔሁ ፡ ወባሕቱ ፡ ፈጸመ ፡ ዙሎ ፡ ዘዚአነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕ ቲታ ፡ ወኮነ ፡ ዕሩየ ፡ ምስሌነ ።

፲፬ ፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተወከፈ ፡ ዙሎ ፡ ዘዚአነ ፡ ርገዘ ፡ ወጸምዓ ፡ ኖመ ፡ ወደክመ ፡ እምሐሚረ ፡ ፍኖት ። ተንኰነ ፡ ተሰቅለ ፡ ወሐመ ፡ ወተቀንወ ፡ ወበጽሐ ፡ ለሞት ፡ በፈቃዱ ፡ በክመ ፡ ነገራ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻ ሕፍት ፡ ምሥጢር ፡ ዐቢይ ፡ ወግሩም ፡ ውእቱ ፡ ትስብእቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ወይሁበከ ፡ ተፈልጦተ ፡ ወተከፍሎተ ፡ ወተዋሕዶተ ።

፲፭ ፤ ወእመሰ ፡ ተብህለ ፡ ኮነ ፡ መድኃኒትነ ፡ በሰብእ ፡ ዝንቱ ፡ ዕልወት ፡ ወክሒድ ፡ ውእቱ ፡ ዳእሙ ፡ መድ ኃኒትነሰ ፡ ኮነ ፡ በአምላክ ፡ ዐቢይ ፡ መንክር ፡ ወመ ድምም ፡ ውእቱ ፡ ከዊነ ፡ አምላክ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹም ፡ ወዝንቱሰ ፡ ኮነ ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘይትዐዶ ፡ እምልበ ፡ ዕጓለ ፡ ሕመሕያው ፡ ከዋኔ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለአምላክ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ መኑሂ ፡ ፍካሬሁ ፡ ወኢዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ፡ ዕጹብ ፡ ወመንክር ፡ ውእቱ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዊሁ ፡ ለአምላክነ ፡ ቃል ። ወኢሳይያስኒ ፡ ሰመዮ ፡ መንክረ ፡ ወመድምመ ፡ በግብር ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወዘኢይትረከብ ፡ ወለሊሁ ፡ ይትሌዓል ፡ እምልቡና ፡ ሰብእ ፡ ወርሑቅ ፡ ውእቱ ፡ እምኵሉ ፡ ምትሀት ፡ ወተዐቅፎ ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፩፲፬ ።

፲፫ ፤ ስሙም ፡ ዐማኑኤል ፡ ተባለ ፤ ትርጓሜውም ፡ አም ላካችን ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የማይከፈል ፡ ተዋሕዶ ፡ ከእነሱ ፡ በተደረገ ባቸው ፡ በሁለት ፡ ባሕርያት ፤ በእነዚህ ፡ በመለኮ ትና ፡ በትስብእት ፡ መካከል ፤ መለየት ፤ መለወጥ ፡ መቀላቀል ፤ መደባለቅ ፡ ሳይኖር ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ ባሕ ርይ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ነው ፤ ረቂቅ ፡ መለኮት ፡ ግዙፍ ሥጋን ፡ ለመሆን ፡ ያለ ፡ መለየት ፤ ያለ ፡ መለወጥ ፡ ነውር ፡ ነቀፋ ፡ ከሌለበት ፡ ከሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ጋር ፡ ተዋሕደ ፤ ከማይወሰን ፤ ከማይነገር ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላ ፤ መጽሐፍ ፡ ሁለትነትን ፡ አልተናገረም ፤ ሐሰት ፡ ያይደለ ፡ በውነት ፡ መዋቲ ፡ ሥጋን ፡ ተዋ ሐደ ፤ ከእሱ ፡ ከፍሎ ፡ አልተዋሐደም ፤ ከኃጢ ጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ የእኛ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጸመ ፤ ከእኛም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ።

፲፬ ፤ የእኛ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ ተራበ ፤ ተጠማ ፤ ተኛ ፤ መንገድ ፡ በመሔድ ፡ ደከመ ፤ ይሙት ፤ በቃ ፡ ተፈረደበት ፤ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ተቸነከረ ፤ በፈቃዱ ፡ እስከ ፡ መሞት ፡ ደረሰ ፤ ቅዱ ሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፤ የመድኃኒታ ችን ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ የማይመረመር ፡ ረቂቅ ፡ ምሥ ጢር ፡ ነው ፤ ባሕርያት ፡ ጥንቱን ፡ እየራሳቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ መዋሐዳቸውን ፡ ያስረ ዳኻል ።

፲፭ ፤ ድኅነታችን ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ተደረገ ፡ ከተባለ ፤ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ክሕደት ፡ ነው ፤ ድኅነታችን ፡ በባ ሕርይ ፡ አምላክ ፡ ተደረገ ፡ እንጂ ፤ አምላክ ፤ ፍጹም ሰው ፡ መሆኑ ፡ ድንቅ ፤ ረቂቅ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ አም ላክ ፡ ሰው ፡ የመሆኑ ፡ ነገር ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ከመ መርመር ፡ በራቀ ፤ ድንቅ ፡ በሚሆን ፡ ተዋሕዶ ፡ ተደ ረገ ፤ እንደምን ፡ እንደሆነም ፡ ነገሩን ፡ የሚያውቅ ፤ የለም ፤ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ የመሆኑ ፡ ምሥ ጢር ፡ ዕጹብ ፤ ድንቅ ፡ ነው ፤ ኢሳይያስም ፡ በማይ መረመር ፤ በማይነገር ፡ ሥራ ፡ ረቂቅ ፡ ድንቅ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፡ እሱም ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ከመመ ርመር ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ ምትሀት ፤ ጎድሬት ፡ ከመሆ ንም ፡ የራቀ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፭ ።

፲፯ ፤ ወአኮ ፡ በእንተ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ በልቡና ፡ ዕንለ፡ እመሕያው ፡ ዘይርሕቅ ፡ ሕሊና ፡ በእንተ ፡ ተወክፎቱ ፡ እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ሚ ፡ የዐቢ ፡ ግብርከ ፡ እግዚኦ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢአበሰ ፡ ወኢተረክበ ፡ ጉሕሉት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወከማሁ ፡ ኢሳይያስኒ ፡ ዓዲ ፡ ወሶበ ፡ ኢተሣገወ ፡ እፎኑ ፡ እምሐመ ፡ ወሶበኒ ፡ ኢሐመ ፡ እምኢሞተ ፡ ዝኩ ፡ ዐዚዝ ፡ ወክብር ፡ ወሶበኒ ፡ ኢሞተ ፡ እፎኑ ፡ ይከውን ፡ መድኃኒትነ ፡ በከመ ፡ መሀረን ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ ሊቀ ፡ አርዳእ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ ፡ በእንቲኣነ ፡ በሥጋ ፡ ሶበሰ ፡ ሐልዮ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ሐመ፡ወአኮ፡ አምላክ፡ ተሰብአ፡ እምኢይቤ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ በእንቲኣነ ፡ ዘኮነ ፡ ቀዲሙ ፡ እንበለ ፡ ሥጋ ፡ ወኢተወክፈ ፡ ሕማም ፡ ወባሕቱ ፡ ይቤ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ወኢሐመ ፡ በመለኮቱ ፡ ወኢዘከሮ ፡ ለሥጋ ፡ ዓዲ ፡ ፍሉጠ ፡ እመለኮት ፡ ወእጠየቀ ፡ ተዋሕዶቶ ፡ ለመለኮት ፡ ዘተዋሐደ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ አመ ፡ ተሣገወ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ እስመ ፡ አምላክ ፡ ዘተሣገወ ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ዘሐመ ፡ በተዋሕዶ ፡ ዘኢይትከፈል ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፬—፲፩ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬—፳፭ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፰ ፤ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ መሀረነ ፡ ዐምድ ፡ ጽኑዕ ፡ ወማኅቶት ፡ ብሩህ ፡ ወመምህር ፡ ዐቢይ ፡ አርቶዶክሳዊ ፡ አትናቴዎስ ፡ ዝኩ ፡ ዘነበረ ፡ ላዕለ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘትምህርታቲሁ ፡ እም እስትንፋስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤ ፡ በድርሳኑ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ተዋሐደ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ ወቦቱ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወኢሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ በመለኮቱ ፡ ወአመረ ፡ ተሣገወ ፡ ርኅበ ፡ ወጸምዓ ፡ እንዘ ፡ ኢይትፈለጥ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ እምኔሁ ፡ ፍጹመ ፡ ለማሙራ ፡ ወኢይመውት በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤ ፡ ውእቱሰ ፡ ሐመ ፡ እንዘ ፡ ኢይከውን ፡ ሥጋ ፡ ውዑአ ፡ እምኔሁ ፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋ ፡ ፍጹም ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወዘይደሉ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋ ፡ ደለወ ፡ ላዕሌሁ ።

፲፱ ፤ ወአመረ ፡ ነበረ ፡ ይገብር ፡ ተአምራተ ፡ ኢኮነ ፡ ሥጋ ፡ ፍሉጠ ፡ እምኔሁ ፡ ወባሕቱ ፡ ኮነ ፡ ይትኄበር ፡ ዙሉ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ዘትስብእትኒ ፡ ወዘመለከ ትኒ ፡ በኀዲጉ ፡ ህላዌ ፡ ወኀዲጉ ፡ አካል ፡ ወበዝንቱ ፡ ኮነ ፡ ይፈጽም ፡ ዙሉ ፡ ምግባራተ ፡ በተዋሕዶ ፡ ዘኢይትነገር ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ በሐማተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወበዕውርኒ ፡ ወበዘለምጽ ፡ ወከማሁ ፡ በአልዓዛርኒ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ዙሉ ፡ በግሪሠ ፡ እድ ፡ ወበወሪቀ ፡ ምራቅኒ ፡ ወነቢበ ፡ ልሳን ፡ ወዝንቱ ፡ ያጤይቅ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ወበኀዲጉ ፡ ሥልጣን ፡ ወአሐቲ ፡ መንግሥት ፡ ወበኀዲጉ ፡ ፈቃድ ፡ ወበአሐቲ ፡ ሥምረት ፡ ይፈጽም ፡ ዙሉ ፡ ተአምራተ ወይትዌከፍ ፡ ዓዲ ፡ ሕማማተ ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ሎቱ ፡ ውእቱ ፡ ማር ፡ ፭ ፡ ፳፱ና ፡ ፵ ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፭ —፰ ፡ ፲፭ ፡ ፵፫ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፮ ።

፲፯ ፤ በሰው ፡ ልቡና ፡ የማይመረመር ፡ ስለሆነ ፤ እሱን ፡ ለማመን ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ የራቀ ፡ አይደለም ፤ አቤቱ ፡ ሥራህ ፡ ምን ፡ ይደንቅ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፡ ዳግመኛም ፤ እሱ ፡ አልበደለም ፤ በአንደበቱም ሐሰት ፡ አልተገኘበትም ፡ አለ ፤ ሐዋርያ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ እንዲሁ ፡ ኢሳይያስ ፡ ደግሞ ፤ አስቀድሞ ፡ ተናግሮአል ፤ ሰው ፡ ባይሆን ፡ እንደምን ፡ በታመመ ፡ ነበር ? ባይታመምም ፡ ኖሮም ፡ ክቡር ፡ጽኑ አምላክ ፡ እሱ ፡ ባልሞተም ፡ ነበር ፤ ካልሞተማ ፡ድኅነታችን ፡ እንደምን ፡ በተደረገ ፡ ነበር ፤ የሐዋርያት ፡ አለቃ ፡ ጴጥሮስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አስተማረ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ አምላክም ፡ ሰው ፡ እንዳልሆነ ፡ ቢያስተምር ፡ ኖሮስ ፡ ቀድሞ ፡ ሥጋ ፡ ያልነበረው ፤ ሕማም ፡ አይስማማው ፡ የነበረ ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ ባላለም፡ነበር ፤ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ታመመ ፤ በመለኮቱ ፡ ግን ፡ አልታመመም ፡ አለ ፤ እንጂ ፡ ሥጋንም ፡ ከመለኮት ፡ ለይቶ ፡ አልተናገረም ፤ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ መለየት ፡ የተዋሐደ ፡ የመለኮትን ፡ ተዋሕዶ ፡ አስረዳ ፡ እንጂ ፤ በማይከፈል ፡ ተዋሕዶ ፡ የታመመው ፡ እሱ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ ነውና ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፬—፲፩ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፳፬—፳፭ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፯ ፤ ስለዚህ ፤ ጽኑ ፡ ዐምድ ፡ ብሩህ ፡ ማኅቶት ፤ አርቶዶክሳዊ ፡ መምህር ፤ በወንጌላዊው ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ የተቀመጠው ፤ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተማረ ፡ ደገኛው ፡ አትናቴዎስ ፡ አስተምሮናል ፤ በድርሳኑም ፡ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ከእኛ ፡ የነሣውን ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፤ በነሣው ፡ ሥጋም ፡ ታመመ ፤ ሞተ ፤ በመለኮቱ ፡ ግን ፤ ሕማም ፤ ሞት ፡ የለበትም ፤ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ቢዋሐድ ፡ ለዘላለም ፡ ከሥጋ ፡ ሳይለይ ፡ ተራበ ፤ ተጠማ ፡ አለ ፡ በመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ ግን ፤ ሞት ፡ የለበትም ፤ እሱስ ፤ ሥጋ ፡ ከእሱ ፡ ሳይለይ ፡ ታመመ ፡ አለ ፤ ሥጋም ፤ የምታውቅ ፡የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ፍጹም ፡ ነው ፤ ለሥጋ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ለእሱ ፡ ተገባ ።

፲፰ ፤ ተአምራትን ፡ ያደርግ ፡ በነበረ ፡ ጊዜም ፤ ሥጋ ፡ ከእሱ ፡ አልተለየም ፤ የአምላክነትንም ፤ የሰውን ትንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ በሆነ ፡ በእሱ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ በዚህም ፤ በማይነገር ፡ ተዋሕዶ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽም ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በጴጥሮስ ፡ አማትነ በዕውሩ ፤ በለምጻሙ ፡ እንዲሁ ፡ በአልዓዛርም ፡ እንደ ፡ አደረገ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በእጅ ፡ በመዳሠሥ ፤ ምራቅን ፡ እንትፍ ፡ በማለት ፤ በቃልም ፡ በመናገር ፡ ተደረገ ፤ ይህም ፡ መለኮት ፡ ሥጋን ፡ መዋሐዱን ፡ ያስረዳል ፤ በአንድ ፡ ሥልጣን ፤ በአንዲት ፡ መንግሥት ፤ በአንድ ፡ ፈቃድ ፤ በአንዲት ፡ ውድ ፡ ተአምራትን ፡ ያደርጋል ፤ መከራንም ፡ ሁሉ ፡ ይቀበላል ፤ ሥጋ ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ። ማር ፡ ፭ ፡ ፳፱ና ፡ ፵ ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፭ —፰ ፡ ፲፭ ፡ ፵፫ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

፲፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኢይደሉ ፡ ይክፍልዎ ፡ ለጎበ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ወኢጎበ ፡ ፪ቱ ፡ አካላት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ወኢያስተርአየ ፡ በምትህት ፡ ሕስው ፡ ወኢበመለኮት ፡ ዘኢይትገሥሥ ፡ ወባሕቱ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ብርሃናዊ ፡ መምህር ፡ ዐቢይ ፡ ቄርሎስ ፡ ይቤ ፡ እመቦ ፡ ዘይፈልጦ ፡ ለዐማኑኤል ፡ አምላክነ ፡ ለጎበ ፡ ፪ቱ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ አው ፡ ዘይሔሊ ፡ ሕማማተ ፡ ለመለኮት ፡ እንከሰ ፡ ፈርሀ ፡ ጎበ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ፍርሃት ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይፌስዩ ፡ ስግደቶሙ ፡ ለሰብእ ፡ ሶበ ፡ ይክፍልዎ ፡ ለአምላክ ፡ ቃል ፡ ይከውኑ ፡ ከመ ፡ አይሁድ ፡ ዐላውያን ፡ ወንሕነሰ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ህልዋን ፡ ላዕለ ፡ ዐቅምነ ፡ ወነሐውር ፡ ላዕለ ፡ ፍኖት ፡ ርትዕት ፡ ወንተሱ ፡ አሠረ ፡ አበው ፡ ብፁዓን ፡ ወንትአመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በተዋሕዶ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወነአምን ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ በእንቲአነ ።

፳ ፤ ወአግናጥዮስኒ ፡ ለባሴ ፡ አምላክ ፡ ይቤ ፡ በመል እክቱ ፡ ሊተሰ ፡ ይደልወኒ ፡ ከመ ፡ እትመሰሎ ፡ በከመ ፡ ሕማማቲሁ ፡ ለአምላኪየ ፡ ወቅዱስኒ ፡ ባስልዮስ ፡ ዐምደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይቤ፡ በድርሳኑ ፡ ዘነበበ ፡ ባቲ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱጣ ፡ ሰማዕት ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአነ ፡ ኮነ ፡ አምላክ ፡ ሰብአ ፡ ወአንሶሰወ ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡ ወግፉዕ ፡ ምስለ ፡ ግፉዓን ፡ ወዘንተ ፡ ሠሎ ፡ ገብረ ፡ ከመ ፡ ያድኅን ፡ ዚውዋነ ፡ ወይኩን ፡ ረዳኤ ፡ ለእለ ፡ አልቦሙ ፡ ረድኤት ፡ ወዘአልቦቱ ፡ ቀዲሙ ፡ ሥጋ ፡ ተሰቅለ ፡ ይእዜ ፡ በለቢሰ ፡ ሥጋ ፡ ወሕይወት ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወብርሃን ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ሲየል ፡ ወዝንቱ ፡ ሠሎ ፡ በእንተ ፡ ድቀቱ ፡ ለአዳም ፡ ወለዘርዐ ።

፳፩ ፤ ወንርኅርዮስኒ ፡ ዘሀገረ ፡ እንዚናዙ ፡ ይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ ዘፈነዋ ፡ ኀበ ፡ አቅላንድዮስ ፡ እመቦ ፡ ዘኢይሰግድ ፡ ለዘተሰቅለ ፡ ውጉዝ ፡ ለይኩን ፡ ወይኩን ፡ ጉሉቀ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ሰቀልዎ ፡ ወብዙኃንሂ ፡ ዓዲ ፡ እምመህራን ፡ ኅሩያን ፡ እለ ፡ ነበቡ ፡ ፭ደ ፡ ቃለ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኀደግነ ፡ በአኀጽሮ ፡ ወኢዘከርነ ፡ ዘዘከርዎ ፡ ወመፍቅድነሰ ፡ ዘኮነ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ አዘከሮተ ፡ ቃሉ ፡ ለሳዊሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሠርዐ ፡ ሃይማኖተ ፡ አርቶዶክሳዌ ፡ ይቤ ፡ ከመዝ ፡ ኢትክፍሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እምሥጋ ፡ ወኢታዕትቶ ፡ ለሥጋሂ ፡ በባሕቲቱ ፡ ወኢትረስዮ ፡ ዕሩቀ ፡ እመለኮት ፡ ወዳእሙ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ተሠገወ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢውላጤ ።

፳፪ ፤ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ለቡ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ አምላክ ፡ ዘኢይትገሥሥ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ዘይትገሥሥ ፡ ወቦቱ ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ ፡ ከመ ፡ ያድኅነነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፭ ።

፲፱ ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡ አካል ፤ ሊከፍሉት ፡ አይገባም ፤ መስሎ ፡ በመታየት ፤ ወይም ፡ በማይዳሠሥ ፡ መለኮት ፡ አል ተገለጠም ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ይህ ፡ ዐዋቂ ፡ ታላቅ ፡ መምህር ፡ ቄርሎስም ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ዐማኑኤልን ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ የሚከፍል ፤ ወይም ፡ ሕማምን ፡ ለመለኮት ፡ ሰጥቶ ፡ የሚናገር ፡ ቢኖር ፤ እንኪያስ ፡ ሊፈራ ፡ የማይገባውን ፡ ፈርታል ፤ ስለ ዚህም ፡ አምላክ ፡ ቃልን ፡ ከከፈሉት ፡ ስግደታቸውን ፡ ለፍጡራን ፡ ማድረጋቸው ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ከሐድያን ፡ አይሁድም ፡ ይሆናሉ ፡ አለ ፤ እኛ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ግን ፤ በተወሰነልን ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፤ በቀናች ፡ ጕዳናም ፡ እንሔዳለን ፤ የብፁዓን ፡ አባቶቻችንን ፡ ፍለጋም ፡ እንከተላለን ፤ ያለመለየት ፡ አንድ ፡ በመሆን ፡ እንዳለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እናምናለን ፤ ደግሞም ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በሥጋ ፡ እንደታመመ ፡ እናምናለን ።

፳ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያደረበት ፡ አግናጥዮስም ፡ በመለኮቱ ፡ ለእኔ ፡ ፈጣሪዬን ፡ በመከራው ፡ እመስለው ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ አለ ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዐምድ ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ ስለ ፡ ኢየሱጣ ፡ ሰማዕት ፡ በተናገረው ፡ ድርሳኑ ፡ አምላክ ፤ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ በሰው ፡ መካከል ፡ ተመላለሰ ፤ ከተገፉት ፡ ጋር ፡ የሚገፋ ፡ ሆነ ፤ የተጎዱትን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፤ ረዳት ፡ ለሌላቸውም ፡ ረዳት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሠራቅድሞ ፡ ሥጋ ፡ ያልነበረው ፡ ዛሬ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕደ ፤ ተሰቀለ ፤ ሕይወት ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፤ ብርሃን ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ ሲያል ፡ ገባ ፤ ይህም ፡ ሁሉ ፡ የሆነ ፡ አዳምና ፡ ልጆቹም ፡ ስለ ፡ ተጎዱ ፡ ነው ፡ አለ ።

፳፩ ፤ ጎርጎርዮስ ፡ ዘእንዚናዙም ፡ ወደ ፡ አቅላንድዮስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ ለተሰቀለው ፡ የማይሰግድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይሁን ፤ ከሰቀሉት ፡ ጋርም ፡ የተቈጠረ ፡ ይሁን ፡ አለ ፤ ዳግመኛም ፡ ከተመረጡ ፡ መምህራን ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ የተናገሩ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ ነገራችንን ፡ በማሳጠር ፡ ተውን ፡ የተናገሩትንም ፡ ሁሉ ፡ አልተናገርንም ፤ ከእነሱ ፡ የምንሻው ፡ የነበረ ፡ ፈቃዳችን ፡ አርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖትን ፡ የወሰነ ፤ የጳጳሳት ፡ አለቃ ፡ ሳዊሮስ ፡ የተናገረውን ፡ ማስታወስ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃልን ፡ እንዲህ ፡ ከሥጋው ፡ አትለየው ፤ ሥጋንም ፡ በብቻው ፡ ለይተህ ፡ አምላክነት ፡ የሌለው ፡ አታድርገው ፤ አምላክ ፡ ቃል ፡ ያለመለወጥ ፡ ያለመለየት ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብለህ ፡ እመን ፡ እንጂ ፡ ብሏልና ።

፳፪ ፤ የቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ይህች ፡ ናት ፤ የማይዳሠሥ ፡ አምላክ ፡ በሚዳሠሥ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ ያድነንም ፡ ዘንድ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ዛሬ ፡ ዕወቅ ፤ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ አሜን ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፩፫ ፤ እመልእከተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ዘተፈነወ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ አክርስቶዶሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ጳጳስ ፡ ዘቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘተንበት ፡ በመዐልቃ ፡ ወአቡ ፡ ሻርዝ ፡ በወርኀ ፡ የካቲት ፡ በ፮ቱ፻፹ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ እም ዐመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ንጹሐን ፡ ንሕነሰ ፡ ርቱዐነ ፡ ሃይማኖት ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘሀሎ ፡ አምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወዘአኮ ፡ ፍጡር ፡ ዘተፈጥረ ፡ አምላክ ፡ ዘእምአምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘዕሩይ ፡ በመለኮቱ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘበእንቲአነ ፡ ለሰብእ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወረደ ፡ እምሰማያት ፡ ወተሠገወ ፡ በሥጋ ፡ ዘከማነ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ እንዘ ፡ ኢየዐርቅ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ።

፩፬ ፤ ወሥጋሂ ፡ ዘተዋሐደ ፡ ቦቱ ፡ ኢተፈልጠ ፡ ለግሙራ ፡ ወኢምንትኒ ፡ እምኔሁ ፡ ወነዋ ፡ አስተዋሐደ ፡ ህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ በኢተፈልጦ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ወኢኀበ ፡ ፪ቱ ፡ አካላት ፡ ዘውእቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡ ፍጹማን ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ አስማት ፡ ዘቦአ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ዐማኑኤል ፡ አምላክነ ፡ ዘነአምሮ ፡ ወነአምን ፡ ቦቱ ፡ ፩ደ ፡ አካለ ፡ ወ፩ደ ፡ እግዚአ ፡ ወ፩ደ ፡ ገጸ ፡ ዘበአማን ፡ ወ፩ደ ፡ ህላዌ ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ፡ህላዌያት፡እምድኅረ፡ተዋሐዶ፡ ተዋሕዶ ፡ዘኢይትረከብ ፡ ወይትአዶ ፡ እምልቡና ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢውላጤ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘያዴምም ፡ አልባበ ፡ ወኢይረክቦ ፡ ሕሊና ፡ ሰብእ ፡ ዕጹብ ፡ ወመድምም ፡ ወመንክር ፡ ውእቱ ፡ መዋኤ ፡ ልቡና ፡ ወንባብ ።

፩፭ ፤ ወዓዲ ፡ ናርሕቅ ፡ ጐልቋተ ፡ ዘህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወንፍልጥ ፡ አካላት ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወንዕቀብ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ እንተ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ ወተመሰለነ ፡ በሥሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ እንዘ ፡ ኢይርሕቅ ፡ እምሥሉ ፡ ሥርዐታቲነ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢይትዌለጥ ፡ ወለሊሁ ፡ ህልው ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወሐመ ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ ወአኮ ፡ በሠርህ ፡ ርኅበ ፡ ወጸምዐ ፡ ደከመ ፡ እምሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ ተጸፍዐ ፡ ወተቀሥፈ ፡ ወተቀነወ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ክቡር ፡ በደሙ ፡ ወሀቤ ፡ ሕይወት ፡ ወለሊሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘኢሐማሚ ፡ ወኢመዋቲ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ሐማሚ ፡ ወመዋቲ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፩፫ ፤ የአንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፤ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ጳጳስ ፡ በነበረው ፡ በጢሞቴዎስ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አክርስቶዶሎስ ፡ ከተላከች ፤ ንጹሐን ፡ ሰማዕታት ፡ መከራ ፡ በተቀበሉ ፡ በሰባት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ በመዐልቃ ፡በአቡ ሻርዝ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ከእነ ፡ አርድእቱ ፡ በተጎንበት ፡ ከተነበበችው ፡ መልእክት ፤ ሃይማኖታችን ፡ የቀና ፡ እኛ ፡ ግን ፤ የተፈጠረ ፡ ፍጡር ፡ ያይደለ ፤ ከአምላክ ፡ የተገኘ ፡ አምላክ ፤ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ትክክል ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፤ እኛንም ፡ ስለማዳን ፡ ከሰማያት ፡ ወርዶ ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ሳይለይ ፡ ለባዊት ፡ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሥጋን ፡ እንደ ፡ ተዋሐደ ፡ ፈጽመን ፡ እናምናለን ።

፩፬ ፤ የተዋሐደው ፡ ሥጋም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ፈጽሞ ፡ ከእሱ ፡ አልተለየም ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፤ወደ ፡ ሁለት ፡ አካላት ፡ ባለመለየት ፡ እነሆ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱን ፡ ከሥጋ ፡ አዋሐደ ፤ እነዚህም ፡ ፍጹማን ፡ የሚሆኑ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ናቸው ፤ ኋላ ፡ እንደ ፡ ተጠራጣቸው ፡ ስሞች ፡ አይደሉም ፤ የምናውቀው ፡ ፈጣሪያችን ፡ ዐማኑኤል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሳይለወጥ ፤ ሳይከፈል ፤ ከሰው ፡ ልቡና ፡ የራቀ ፤ የማይመረመር ፡ ተዋሕዶን ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡ አካላት ፡ ያለ ፤ መለየት ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ በውነት ፡ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ ገዥ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ እንደሆነ ፡ በእሱ ፡ እናምናለን ፤ ልቡናን ፡ ከሚያስደንቅ ፤ የሰው ፡ ሕሊና ፡ ከማይመረምረው ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ የድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ በልብ ፡ ከመመርመር ፤ በአንደበት ፡ ከመነገር ፡ የራቀ ፡ ነው ።

፩፭ ፤ ዳግመኛ ፤ የመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ፈጽመን ፡ እናርቅ ፤ አካላትን ፡ ግን ፡ በየራሳቸው ፡ ለይተን ፡ እንወቅ ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያደረገውን ፡ የባሕርይ ፡ ተዋሕዶንም ፡ እንጠብቅ ፤ ከእኛ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሳይርቅ ፤ ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በሥራ ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ፡ እሱስ ፡ አይለወጥም ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፤ በግድ ፡ ያይደለ ፡ በፈቃዱ ፡ ከእኛ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ታመመ ፤ ተራበ ፡ ተጠማ ፤ መንገድ ፡ በመሔድ ፡ ደከመ ፤ በጥፊ ፡ ተመታ ፡ ተገረፈ ፤ ድኅነትን ፡ በሚያድል ፤ በደሙ ፡ በከበረ ፡ መስቀል ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ተቸነከረ ፤ ሕማም ፤ ሞት ፡ የሌለበት ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፤ በሚታመም ፡ በሚሞት ፡ ሥጋ ፡ ታመመ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

ኖኗ ፤ ዘሀሎ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወፈጣሪ ፡ ዓለም ፡ ወእፍኑ ፡ ኮነ ፡ ይደሉ ፡ ይሕምም ፡ እመ ፡ መጽአ ፡ በካልእ ፡ አርአያ ፡ ጎበ ፡ ሕማምነ ፡ ወድካምነ ፡ እመ ፡ ኢተሠገወ ፡ በሥጋ ፡ ዘከማነ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ወኢሐመ ፡ በመለኮት ፡ ወለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ እምቅድመ ፡ ይሠነ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተሠገወሂ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ንትሜካሕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዘአግዐዘነ ፡ እምቅኔ ፡ ሞት፡ መሪር ፡ መጽአ ፡ ወአድኀነነ ፡ እምእደ ፡ አጽራር ፡ ዘውእቶሙ ፡ ሰይጣን ፡ ወሞት ፡ ወኢሐመ ፡ በምትሀት ፡ ዳእሙ ፡ ሐመ ፡ እሙነ ፡ ዘበአማን ።

ኖኗ ፤ ዝንቱ ፡ እምከርሠ ፡ እሙ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ እሙነ ፡ ተዋሐደ ፡ በሥጋ ፡ ሐማሚ፡ ዘኢ የሐምም ፡ ሐመ ፡ ወዘኢይመውት ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በፈቃዱ ፡ ሶበሰ ፡ አመነ ፡ ካልአ ፡ እምዝንቱ ፡ እም ኢኮነ ፡ ግውዛነ ፡ እምሕማም ፡ ወእማእሰረ ፡ ሞት ፡ ከመ ፡ ነኪራን ፡ ወርሑቃን ፡ እምጽድቀ ፡ ትንሣኤ ፡ ወክርስቶስ ፡ ተመሰለነ ፡ በኵሉ ፡ ሕማምነ ።

ኖኗ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተንሥአ ፡ እሙነ ፡ እሙታን ፡ ወሰበረ ፡ ጎይሎ ፡ ለጸላኢ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይትናገር ፡ በጥበብ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ተሳተፍዎሙ ፡ በሥጋ ፡ ወደምሙ ፡ ወውእቱኒ ፡ በዝ ንቱ ፡ ፍናት ፡ ወበዝንቱ ፡ አምሳል ፡ ተመሰለ ፡ ከመ ፡ ያብጥል ፡ በሞቱ ፡ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ ዘውእቱ ፡ ሰይጣን ፡ ኢነሥአ ፡ እመላእክት ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ ዘይትዔረየነ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወዝንቱ ፡ ዘእምእግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ማርያም ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ እምኔሃ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ከመ ፡ ይትወከፍ ፡ ቦቱ ፡ ሕማማተ ፡ ሰብአዊ ፡ በፈ ቃዱ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያጌብሮ ፡ ወኅብረ ፡ ሥርዓተ ፡ መለኮታዊ ፡ ወምኅባረ ፡ ሰብአዊ ፡ ወኮነ ፡ ይነብብ ፡ ዘይደሉ፡ለመለኮቱ፡ ወለትስብእቱ፡ እንበለ፡ ተፈልጦ።

ኖ፱ ፤ ወአኮ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ወተናግሮ ፡ ወኀቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወጎይላት ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሁ ፡ ወሚመ ፡ በእንተ ፡ ሕማማት ፡ ዘቦአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወድካማት ፡ ዘተወክፎሙ ፡ በእንቲአነ ፡ ዘንበውእ ፡ ለከፊለ ፡ ህላዌያት፡ እምትስብእት፡ እምድኀረ፡ ተዋሕዶ፡ ዘኢ ይትረከብ፡ ወዘኢይትነገር፡ ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ ኢን ከፍል ፡ ቃላተ ፡ ወሕማማተ ፡ በዘሐመ ፡ ቦቱ ፡ እግ ዚእነ ፡ እስመ ፡ ሎቱ ፡ እሙነ ፡ በኢተፈልጦ ፡ ወተ አምራት ፡ ወመንክራት ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ወሕማም ፡ ወመዊት ፡ ዘይደሉ ፡ ለህላዌ ፡ ትስብእቱ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፬ ።

ኖኗ ፤ ዓለምን ፡ የፈጠረ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ ሕማማችን ፤ ወደ ፡ ድካማችን ፡ በሌላ ፡ መልክ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችውን ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ሥጋን ፡ ባይዋሐድ ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሊታመም ፡ በተገባው ፡ ነበር ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ በመለኮት ፡ ግን ፡ እንዳል ታመመ ፡ እናውቃለን ፤ ሰው ፡ ከመሆኑ ፡ አስቀድሞ ፤ ሰው ፡ ከሆነ ፡ በኋላም ፡ እሱ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፤ ለመራራ ፡ ሞት ፡ ከመገዛት፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ አደረገን ፤ ከጠላቶቻችን ፡ ከሰይጣንና ፡ ከሞት እጅ ፡ ስለ ፡ አዳነን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንመካለን ፡ በእውነት ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እሱ ፡ በእውነት ፡ ታመመ፡ እንጂ ፤ በሐሰት ፡ አልታመመም ፤

ኖኗ ፤ እሱ ፡ በእናቱ ፡ በእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ በድን ግል ፡ ማሕፀን ፡ የሚታመም ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፤ የማይታመመው ፡ ታመመ ፤ የማይሞተው ፡ በፈቃዱ፡ ሞተ ፤ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ብናምንስ ፡ ከእውነተኛ፡ ትን ሣኤ ፡ እንደ ፡ ተለዩ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ከሞት ፡ ቁራ ኝነትና ፡ ከሕማም ፡ ነጻ ፡ ባልሆንም ፡ ነበር ፤ ክር ስቶስስ ፡ በመከራችን ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ።

ኖኗ ፤ ስለዚህ ፤ በእውነት ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ ፤ የጠላት ፡ የዲያብሎስን ፡ ሥልጣን ፡ አጠፋ ፤ ልጆች ፡ ሥጋ ፤ ደም ፡ በመሆን ፡ መሰሉት ፤ እሱም ፡ ሰይ ጣን ፡ የተባለ ፡ የሞትን ፡ ሥልጣን ፡ በሞቱ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ፡ሥራ፡በዚህ፡መንገድ፡መሰለን፡ ብሎ ፡ በጥበብ ፡ የሚናገር ፡ ሐዋርያ ፡ እንደ፡ ተናገረ፡ ከእኛ ፡ የነሣውን ፡ ከመላእክት ፡ አልነሣም ፤ የም ታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፤ በሥራ ፡ሁሉ እኛን ፡ የሚመስለን ፡ ሥጋን ፡ ከአብርሃም ፡ ባሕርይ ነሣ ፡ እንጂ ፤ ይህም ፡ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ ድንግል ፡ ከምትሆን ፤ አምላክን ፡ ከወለደች ፡ ከእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ ግድ ፡ ያለው ፡ ሳይኖር ፡ በፈቃዱ ፡ የሰውን ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ፡ ወልድ ዋሕድ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ከእሷ ፡ ነሣ ፤ መለኮታዊ ፡ ሥርዓትን ፤ ሰብአዊ ፡ ሥራን ፡ ሠራ ፤ ሳይለይ ፡ ለአምላክነቱ ፡ ለሰውነቱ ፡ የሚገባውን ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

ኖ፱ ፤ በእሱ ፡ የተፈጸመውን ፡ ተአምራትና ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ ማድረጉን ፤ አነጋገሩን ፤ ሥራውን ፤ ወይም በእሱ ፡ የተፈጸሙ ፡ ሕማማትን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የተቀ በላቸውን ፡ ድካማትን ፡ ምክንያት ፡ አድርገን ፡ ከማ ይነገር ፤ ከማይመረመር ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላ ፤ ባሕር ያትን ፡ ወደ ፡ መከፈል ፤ መለኮትን ፡ ከትስብእት ፡ ወደ ፡ መለየት ፡ የምንገባ ፡ አይደለም ፤ ስለዚህም ፡ ጌታችን ፡ የተቀበለውን ፡ መከራና ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አንከፍልም ፤ ለመለኮት ፡ የሚቻል ፡ ተአም ራት ፡ ማድረግ ፤ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ መሥራትም ፡ ቢሆን ፡ ለሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ የሚስማማ ፡ ሕማም ፤ ሞትም ፡ ቢሆን ፡ ባለመለየት ፡ በእውነት ፡ ለእሱ ፡ ገንዘቡቹ ፡ ናቸውና ።

ምዕራፍ ፡ ፤፤፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ይቤ ፡ ሐቢብ ፡ ዘውእቱ ፡ ፍቁር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ተክሪት ፡ ወወይከኒ ፡ ወአበሪዳ ፡ በውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ጎበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ በደቡብ ፡ ወበምዕራብ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ በሀላዌሁ ፡ እንዘ ፡ ፩ዱ ፡ ፫ቱ፡ ወእንዘ ፡ ፫ቱ ፡ ፩ዱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወልድ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበቡ ፡ ወጸዳለ ፡ ብርሃኑ ፡ አመ ፡ አልጸቀ ፡ ዘመን ፡ ወረደ ፡ እም ሰማይ ፡ በሥምረተ ፡ አቡሁ ፡ ወበፈቃዶ ፡ ርእሱ ፡ ወተሠገወ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ ሥጋ ፡ ወአስተርአየ ፡ ቡቱ ፡ ማእከሌነ ፡ ተፈጸመ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ ውስቴቱ ፡ ወተነብየቶሙ ፡ በእንቲአሁ ።

፪ ፤ ወሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ አኮ ፡ በምትሀት ፡ ወአኮ ፡ በተዐርቆ ፡ እምኔሁ ፡ ዘከመ ፡ ይብሉ ፡ ስብእ ፡ ስሑታን ፡ ወባሕቱ ፡ ነሥአ ፡ ሥጋ ፡ ፍጹመ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ መሀረነ ፡ መምህረ ፡ ጽድቅ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ጎበ ፡ ይብል ፡ በጥንተ ፡ መጽሐፉ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኅደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ወርኢነ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ስብሐተ ፡ ፩ዱ ፡ ዋሕድ ፡ ለአቡሁ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፫ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በዝንቱ ፡ ድርሳን ፡ እምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስሰ ፡ መንጦላዕተ፡ መለኮት፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋሁ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፬ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ ሣልሲት ፡ እም፪ቱ ፡ መልእክታት ፡ ዘተናገረ ፡ ባቲ ፡ በእንተ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወትሥጉት ፡ ንሕነሰ ፡ ተናገርነ ፡ በካልእ ፡ መካን ፡ እምዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ተሰብአ ፡ ወባሕቱ ፡ ተብህለ ፡ ሞተ ፡ በሥጋሁ ፡ ወአኮ ፡ በመለኮቱ ። ወሞቱሰ ፡ በሥጋሁ ፡ ተፈልጦተ ፡ ነፍሱ ፡ እምሥጋሁ ፡ ዘተፈጥረት ፡ ወመለኮትሰ ፡ ኢተፈልጠ ፡ እምነፍሱ ፡ ወኢእምሥጋሁ ፡ አላ ፡ ይትዋሐድ ፡ ዘልፈ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በከመ ፡ ነገርነ ፡ ወንቤ ።

ምዕራፍ ፡ ፤፤፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ይኸውም ፡ የተወደደ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በተክሪት ፡ በወይኪኒና ፤ በአበሪዳ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ የተሾመ ፡ ሐቢብ ፡ ለደቡብና ፡ ለምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ሦስት ሦስት ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፤ ጥበቡ ፤ የባሕርዩ ፡ መታወቂያ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፤ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ በአባቱ ፡ ፈቃድ ፤ በራሱ ፡ ፈቃድ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ነፍስን ፤ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ በነሣው ፡ ሥጋም ፡ በመካከላችን፡ ተገለጠ ፤ ስለ ፡ እሱ ፡ የተናገሩት ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፡ በእሱ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ተፈጸመ ።

፪ ፤ ከእሷ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ግን ፤ በሐሰት ፡ አይደለም ፤ የካዱ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ በጎድረት ፡ አይደለም ፤ እሱ ፡ ፍጹም ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ፡ እንጂ ፤ የውነት ፡ መምህር ፡ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ በመጽሐፉ ፡ መጀመሪያ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፤ በእኛም ፡ አደረ ፤ ለአባቱ ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ልጅ ፡ ያለ ፡ ክብሩን ፡ አየንለት ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አስተማረን ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

ክፍል ፡ ፪ ።

፫ ፤ ዳግመኛ ፤ በዚህ ፡ ድርሳን ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፤ ብሎ ፡ ክርስቶስስ ፡ መለኮትን ፡ ተገልጠ ፡ አየን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ከእኛ ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤

ክፍል ፡ ፫ ።

፬ ፤ ዳግመኛም ፤ ከሦስቱ ፡ መልእክታት ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴንና ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ በተናገረበት ፡ በሦስተኛው ፡ መልእክት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኛ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ፡ መጽሐፍ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ተናግረናል ፤ ነገር ፡ ግን ፤ በመለኮቱ ፡ ያይደለ ፡ በሥጋው ፡ ሞተ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፤ በሥጋው ፡ ሞተ ፡ መባሉም ፡ ነፍሱ ፡ ከተፈጠረች ፡ ከሥጋው ፤ መለየቷ ፡ ነው ፤ መለኮት ፡ ግን፡ ከሥጋውም ፤ ከነፍሱም ፡ አልተለየም ፤ እንደ ፡ ተናገርን ፤ ከሥጋ ፤ ከነፍስ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ ይኖራል ፤ እንጂ ።

ዘዘካርያስ ፡ ይህያ ፡ ም ፡ ፻፲፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፲፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩፤ ይቤ ፡ አቡ ፡ ዘካርያስ ፡ ይህያ ፡ ወልደ ፡ ዐደይ ፡ ወልደ ፡ ውዱስ ፡ ወልደ ፡ ዘካርያስ ፡ በመልእክቱ ፡ ጎበ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ ፍቁር ፡ አውሥአተ ፡ በእንተ ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ ወሃይማኖትነሰ ፡ ለነ ፡ ለያዕቆባውያን ፡ በእንተ ፡ ትስብእተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለሊሁ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ ወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ወተሠገወ ፡ ወተሰብአ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ንጽሕት ፡ ተወልደ ፡ ወተሰቅለ ፡ ለቤዛ ፡ ዙሉ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወተቀብረ ፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ ወዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፫—፭ ።

፪፤ ወፍካሬ ፡ ተሰብአሰ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወነሥአ ፡ ሥጋ ፡ ዘይትዔረየነ ፡ ለነ ፡ ለዕጓለእመሕያው ፡ በዙሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢተፋልሶ ፡ ህላዌ ፡ ወኢትድምርተ ፡ እካላት ወኢቁሳሔያት ፡ ወባሕቱ ፡ ንሌብዎ ፡ ከመ ፡ ሀልዎተ ፡ ሥጋ ፡ ምስለ ፡ ነፍስ ፡ ወለሊሁ ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ።

፫፤ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወተወልደ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ፈጣሬ ፡ ዙሉ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘህልው ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ወኮነ ፡ በግዐ ፡ በከርሠ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ዘኢይትገሠሥ ፡ በመለኮቱ ፡ ተገሠ ፡ ይእዜ ፡ በለቢሰ ፡ ሥጋ ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምልቡና ፡ ወኢይረክቦ ፡ ሕሊና ፡ ተሠገወ ፡ ወተሰብአ ፡ ወቦቱ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወመለኮቱሰ ፡ ኢሐማሚ ፡ ወኢመዋቲ ፡ ውእቱ ፡ ወኢይረክቦ ፡ ተፋልሶ ፡ ወኢሚጠት ፡ ወለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ወሰብእ ፡ ፍጹም ፡ ዓዲ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደልዎ ፡ ይትበሀል ፡ ፩ደ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ደ ፡ አካለ ፡ ወ፩ደ ፡ ገጸ ።

፬፤ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶሰ ፡ ኢይትበሀል ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያተ ፡ ወኢ፪ቱ ፡ አካላተ ፡ ፍሉጣተ ፡ ወዝንቱሰ ፡ ፩ዱ ፡ ባሕርይ ፡ ውእቱ ፡ ዘንትአመን ፡ ቦቱ ፡ በላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ወሰመ ፡ ክርስቶሰሰ ፡ በኀበ ፡ ያዕቆባውያን ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካለ ፡ ፩ዱ ፡ ገጽ ፡ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ እምነቶሙ ፡ ለያዕቆባውያን ፡ ርቱዕነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወሰብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ዘዘካርያስ ፡ ይህያ ፡ ፻፲፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፲፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩፤ የተመሰገነ ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የዐደይ ፡ ልጅ ፡ አባታችን ፡ ይህያ ፡ ዘካርያስ ፡ ስለ ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ መልስ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ተወደደ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቸር ፡ አባት ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፤ እኛ ፡ የያዕቆብ ፡ ወገኖች ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ የምናምነው ፡ ሃይማኖታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እሱ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብለን ፡ ነው ፡ አለ ፤ ተወልዶም ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ ሆኖ ፡ ተሰቀለ ፡ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረ ፤ ከሙታንም ፡ ተለይቶ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፫—፭ ።

፪፤ ሰው ፡ ሆነ ፡ የማለትም ፡ ትርጓሜው ፡ የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የባሕርይ ፡ መፋለስ ፤ መለወጥ ፡ ሳይኖር ፤ በአካላትም ፡ መደባለቅ ፤ መቀላቀል ፡ ሳይኖር ፤ ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ እኛን ፡ የሚመስል ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ፤ ሥጋም ፡ ከነፍስ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፤ እሱም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሆነ ፡ እናውቀዋለን ።

፫፤ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፤ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ በቅድምና ፡ የነበረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ተወለደ ፤ መሥዋዕት ፡ እሱ ፡ በድንግል ፡ ማሕፀን ፡ አደረ ፤ በመለኮቱ ፡ አይዳሠሥ ፡ የነበረ ፤ ዛሬ ፡ ሥጋን ፡ ለብሶ ተዳሠሠ ፤ በልቡና ፡ ከመመርመር ፡ የራቀ ፤ ሕሊና ፡ የማይመረምረው ፡ ድንቅ ፡ በሚሆን ፡ ተዋሕዶ ፡ ነፍስን ፤ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ በሥጋ ፡ ታመመ ፤ ሞተ ፤ መለኮቱ ፡ ግን ፡ የማይታመም ፡ የማይሞት ፡ ነው ፤ መለወጥ ፤ መፋለስ ፡ የለበትም ፡ እሱ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፤ እሱ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ሊባል ፡ ይገባዋል ።

፬፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ግን ፤ የተለያዩ ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፤ ሁለት ፡ አካላት ፡ አይባልም ፤ በፈጣሪያችን ፡ በክርስቶስ ፡ የምናምነው ፡ እምነት ፡ ይህ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ክርስቶስም ፡ ማለት ፡ በያዕቆባውያን ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ የያዕቆባውያን ፡ እምነት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ዘላለሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ አሜን ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፲፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፲፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ፲ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ እንተ ፡ ዘቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ገባሬ ፡ መንክራት ፡ ዘተናገረ ፡ በእንተ ፡ ትሥጉተ ፡ ክርስቶስ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፤ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንእመን ፡ በእንተ ፡ ትሥጉቱ ወተሰብእቱ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ።

፪ ፤ ወወጠኑ ፡ ዜንምተነ ፡ አሪት ፡ ወነቢያት ፡ ወኮኑ ፡ ስምዐ ፡ ሐዋርያትኒ ፡ ሰበኩ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተርአየ ፡ በአማን ፡ እንዘ ፡ ይነብብ ፡ ወይጌሥጽ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ እመቦ ፡ ዘይብል ፡ አው ፡ ዘይሔሊ ፡ ወይትዐቀፍ ፡ በዘአስተርአየ ፡ ክርስቶስ ፡ በውስተ ፡ ዓለም ፡ ወኢየአምን ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ አስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ። ዘዳግ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ። መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ (፻፲፯) ፳፯ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

፫ ፤ ፍካሬ ፡ ወእፎኑ ፡ ይብል ፡ ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ አስተርአየ ፡ በውስተ ፡ ዓለም ፡ አስተርእዮተ ፡ ምትሀታዊ ፡ ዝኩ ፡ ዘተወልደ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ወሰበ ፡ ተፈጸመ ፡ ሰሙን ፡ መዋዕል ፡ መጽአ ፡ ለተገዝሮ ፡ ወተጸውረ ፡ ላዕለ ፡ መዝራዕተ ፡ ስምዖን ፡ ወገረረ ፡ ለእዝማዲሁ ፡ ወነነየ ፡ ለሰብዑ ፡ ወተጠምቀ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወተቀነወ ፡ በቅንዋት ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ። ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፩ ። ፳፪ ፡ ፳፰—፶፪ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፱ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ የሚመሰ ክሩ ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ ከጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ የተውጣጣ ፤ ክፍል ፤ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ክርስቶስ ፡ በኋላ ዘመን ፡ ሀ ልጊዜ ፡ ድንግል ፡ ከምትሆን ፡ ከማርያም በማኅፀ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ ሰው ኾነ ፤ እኛን ፡ የሚመስል ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ሥጋን ፡ ከእሷ ፡ ነሣ ፤ እግዚአብ ሔር ፡ ቃል ፡ በድንግል ፡ ማሕፀን ፡ ሳይዋሐደው ፡ አስቀድሞ ፡ ሥጋ ፡ አልተቀረጸም ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ እንዴት ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፤ ይባል ፡ ነበር ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፸፬ ።

፩ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እፎኑ ፡ ይጸንዕ ፡ ሥጋ ፡ ዘተፈጥረ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ንቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ እሙነ፡ ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ በውስተ ፡ ከርሠ ፡ ድንግል ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ሥጋሰ ፡ ሥጋ ፡ ውእቱ ፡ ወኢኮነ ፡ መለኮተ፡ ወቃልሂ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ሥጋ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወለእመሂ ፡ ረሰየ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ በሥርዓት ፡ ዘሠርዐ ፡ ለርእሱ ፡ ውእቱሰ ፡ አምላክ ።

፪ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ ፲ቱ ፡ ወፂቱ ፡ ግዘት ፡እመ ዘኢይትአመን ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ወተሰቅለ ፡ በሥጋ ፡ ወጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወኮነ ፡ በሰረ ፡ ለዘተንሥኤ ፡ እሙታን ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ዘሐመሰ ፡ መድኀነ ፡ ዓለም ፡ ውእቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ይሕምም ፡ ውእቱ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ባሕቲቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ቃል ፡ ዘተወልደ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወሐመ ፡ ቦቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ረሰየ ፡ ምግባራተ ፡ ሥርዓተ ፡ ሥጋ ፡ በምግባር ፡ ዘይሜኒ ፡ ወይእዜኒ ፡ ደለዎ ፡ ከመ ፡ ይሕምም ፡ በሥጋ ፡ ዘረሰየ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ።

፫ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኢሐመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወህላዌ ፡ መለኮቱ ፤ በተቀሥፎሂ ፡ ወበተቀንዎ ፡ ቅንዋት ፡ ወእለ ፡ ተርፋ ፡ ሕማማት ፡ እስመ ፡ መለኮትሰ ፡ ኢሐማሚ ፡ ወኢመዋቲ ፡ ወኢኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወባሕቱ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ዘሐመ ፡ በእንቲአነ ፡ ወዓዲ ፡ ንሕነሰ ፡ መሲሐውያን ፡ ንብል ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ እንተ ፡ ዘለብሶ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ መለኮትሰ ፡ ኢሐማሚ ውእቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ዐላውያን ፡ ቀደምት ፡ ኮኑ ፡ ይብሉ ፡ በዕበዶሙ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምህላዌሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘውእቱ ፡ ፈጠረ ፡ ሎቱ፡ ሥጋ ፡ እመለኮቱ ፡ ወንሕነሰ ፡ ንተሉ ፡ በሰሉ ፡ ጊዜ ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ንባበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአግሀዱ ፡ ለነ ፡ ወንብል ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

፭ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ከመዝ ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢሐማሚ ወኢመዋቲ ፡ ውእቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ተኖለቄ ፡ ሎቱ፡ ሕማመ ፡ ትስብእት ፤ ወበከመ ፡ ንሕነ ፡ ነአምር ፡ ተፈልጦተ ፡ ህላዌያት ፡ እሉ ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ክርስቶስ ፡ እንተ ፡ ዘትስብእት ፡ ወዘመለኮት ፡ ኢንፈልጠሙ ፡ ለግሙራ ፡ ወኢንቤ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዓዲ ፡ ይቤ ፡ ኢፈጠረ፡ ሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ነሥአ ፡ ፈድፋደ ፡ እምድንግል ፡ ንጽሕት ፡ ወእመ ፡ እኮሰ ፡ እፎ ፡ ኮነ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ለሊሁ ፡ ለብሰ ፡ ሥጋ ፡ ሰብእ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፸፭ ።

፩ ፤ ዳግመኛ ም ፤ ፍጡር ፡ ሥጋ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደምን ይቀረጻል ? አለ ፤ ዳግመኛም ፡ እኛስ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ በድንግል ፡ ማሕፀን ፡ ሊዋሐደው ፡ ሥጋን ፡ ፈጠረ ፡ እንላለን ፡ አለ ፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሥጋ ሥጋ ፡ ነው ፤ መለኮት ፡ አይደለም ፤ ቃልም ፡ አምላክ ነው ፤ ሥጋ ፡ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ለራሱ ፡ በአደረገው ፡ ተዋሕዶ ፡ ሥጋን ፡ ገንዘብ ፡ ቢያደርግም ፡ እሱስ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፪ ፤ ዳግመኛም ፤ በዐሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ግዘት ፤ በሥጋ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ በሥጋም እንደ ፡ ሞተ ፡ እንደ ፡ ተጸፈም ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ አስቀድሞ ፡ የተነሣ ፡ በሰር ፡ እንደሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሚያምን ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን አለ ፤ የታመመውስ ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ነው፤ ግን ፡ ሥጋን ፡ ሳይዋሐድ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ታመመ ፡ ሊሉ ፡ አይገባም ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብ፡ የተወለደ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ እንጂ ፡ ስለዚህም ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ተዋሕዶ ፤ ሰው ፡ ለኾነበት ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፤ አሁንም ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ገንዘብ ፡ በአደረገው ፡ በሥጋ ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ተገባው።

፫ ፤ ዳግመኛም ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ በመገረፍም ፡ ቢኾን ፤ በችንካር ፡ መቸንከርም ቢኾን ፤ በቀሩት ፡ ሕማማትም ፡ አልታመመም ፡ አለመለኮት ፤ ሕማም ፤ ሞት ፡ የለበትምና ፡ ፍጡርም ፡ አይደለምና ፤ ስለ ፡ እኛ ፡ የታመመው ፡ በነሣው፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ዳግመኛ ፡ እኛ ፡ ክርስቲያንም፡ ክርስቶስ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ታመመ ፡ እንላለን ፤ መለኮት ፡ የማይታመም ፡ ነውና ፤ ዳግመኛ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ መናፍቃን ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ በድን ቁርናቸው እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከባሕርዩ ፡ ሥጋን ፡ ሊዋሐደው ፡ ፈጠረ ፡ ይኸውም ፡ ሊዋሐደው ፡ ከመለኮቱ ፡ የፈጠረው ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ እኛ ፡ ግን በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ የገለጡልንን ፤ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ የቅዱሳን ፡ መጻሕፍትን ፡ ቃል ፡ ተከትለን ፡ አምላክን ፡ ከወለደች፡ ከቅድስት፡ ድንግል ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ፈጥሮ ፡ ተዋሐደ ፡ እንላለን ፡ አለ።

፬ ፤ ዳግመኛም ፤ የማይታመም ፤ የማይሞት ፡ እንደኾነ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ እናምናለን ፡ እንታመናለን ፡ የሥጋ ፡ ሕማም ፡ ተነገረለት ፡ እንጂ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ የኾነላቸው ፡ የእነዚህን ፡ የመለኮትና ፡ የትስብእትን ፡ ባሕርያት ፡ አለመቀላቀል ፡ እንደምናውቅ ፡ መጠን ፡ ፊጽሞ ፡ አንከፍላቸውም ፤ ከተዋሕዶም ፡ በኋላ ፡ ሀ ለት ፡ ባሕርያት ፡ አንልም ፤ ዳግመኛም ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ያደረገው ፡ ሥጋውንም ፡ ከመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ አልፈጠረውም ፤ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ነሣው ፡ እንጂ ፡ የሰውን ፡ ሥጋ፡ ቢዋሐድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያለዚያማ ፡ እንደምን ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ነበር ? ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

፩ ፤ ንሕነሰ ፡ ንሴብኮ ፡ አምላሊሁ ፡ ለትስብእት ፡ ወንብል ፡ ለእመሂ ፡ ኮነ ፡ ክርስቶስ ፡ እም፪ቱ ፡ ህላዌ ፡ ያት ፡ እንከሰኬ ፡ ናሁ ፡ ተዋሐዱ ፡ በበይናቲሆሙ፡ ወኮነ ፡ ፩ደ ፡ ህላዌ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ወኢት ድምርት ፡ ወኢውላጤ ፡ እስመ ፡ ሥጋሰ ፡ ሥጋ ፡ ውእቱ ፡ ወኢኮነ ፡ መለኮተ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ እግዚአብሔር ፡ ቃልሂ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወእኩ፡ ሥጋ ፡ ወረሰየ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ ዘሎቱ ፡ ውእቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ኢንቤ ፡ ከመ፡ ሥጋ ፡ ቅዱስ ፡ እንተ ፡ ዘክርስቶስ ፡ ተወለጠ ፡ እም ቅድመ ፡ ትንግኤ ፡ ወኢእምድኅረ ፡ ትንግኤ ፡ ወኢ ንብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመዝ ፡ ለማሙራ ።

፪ ፤ ወዓዲ ፡ ኢንብል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ነፍስ ወኢልቡና ፡ ወባሕቱ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ ህላዌ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ ወካዕበ ይቤ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መድኃኔ ፡ ሙሉ ፡ ፍጥረት ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወውእቱ ፡ ክመ ፡ ውእቱ ፡ ወኢተወለጠ ፡ መለኮት ፡ ምንተኒ ፡ ፍጹመ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ወባሕቱ ፡ እስመ ግብርሰ ፡ ክሡት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ክመ ውእቱ ፡ ዘይነብር ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ መንበር ፡ ምስለ አቡሁ ፡ በ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወተቀብዐ ፡ ምስሌነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ሶበ ፡ ተሠገወ ፡ ወኮነ ፡ ፩ደ ፡ ምስለ፡ ሥጋ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ።

፫ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ሰ ፡ ኢሐማሚ ወኢመዋቲ ፡ ውእቱ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ በክመ ፡ አቅደምኩ ፡ ወእቤ ፡ ወባሕቱ ፡ እብል ፡ ሐመ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ በክመ ፡ ጽሑፍ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ በክመ ፡ አቅደምነ ፡ ወንቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ሐመ ፡ በሥጋሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘነሥአ እምኔነ ፡ በክመ ፡ ይቤላ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ወለሊሁ ፡ ህልው ፡ በሥጋ ፡ ዘየሐምም ፤ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ወኢሐመ ፡ በመለኮት ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ኢሐማሚ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ ወለሊሁ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ።

፬ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ንብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ኮነ ፡ ፩ደ ፡ ምስሌነ ፡ ወፈጸመ ፡ ሙሉ ፡ ዘዚእነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ወእመሰ ፡ ኮኑ ፡ ተምያጠ ፡ ወተውላጠ ፡ ህላዌያት ፡ ብዙኃን ፡ እንተ ፡ ኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ፡ ወተዋሕዶሰ ፡ ያሴስል ፡ እሙንተ ፡ ተፈልጦተ ፡ እንተ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ዘውእቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡ በክመ ፡ ንብል ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ያተ ፡ ዓዲ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ንቤ ፡ በእንተ ፡ ተዋሕዶተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘአሰሰለ ፡ ተፈልጦተ ፡ ህላዌያት ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዐማኑኤል ፡ ወባሕቱ ፡ አሰሰለ ፡ ፍልጠተ ፡ ከመ ኢይኩን ፡ ፪ተ ፡ ህላዌያተ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ፡ ዘኢይትነገር ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

፩ ፤ እኛ ፡ የሥጋን ፡ ነገር ፡ እናውቃለን ፤ ክርስቶስ ፤ ከሁለቱ ፡ ባሕርያት ፡ አንድ ፡ ቢኾንም ፡ እንኪያስ ፡ እነሆ ፡ ባሕርያት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተዋሐዱ ፤ ያለ ፡ መለወጥ ፡ ያለ ፡ መቀላቀል ፤ ያለ ፡ መለየት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኑ ፡ እንላለን ፤ ሥጋም ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተለውጦ ፡ መለኮትን ፡ አልኾነምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥጋ ፡ ቢሆንም ፡ ቃል ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ተለውጦ ፡ ሥጋን ፡ የኾነ ፡ አይደለም፡ ኀንዘቡ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ሥጋን ፡ በተዋሕዶ ፡ ኀን ዘብ ፡ አደረገ ፡ እንጂ ፤ ዳግመኛም ፤ እኛስ ፡ ክርስቶስ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ከትንሣኤ ፡ በፊት ፡ ከትንሣኤም ፤ በኋላ ፡ ተለወጠ ፡ እንልም ፡ አለ ፤ ስለ ፡ እርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዲህ ፡ ብለን ፡ አንናገርም ።

፪ ፤ ዳግመኛም ፤ ነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ የለውም ፡ አንልም ፤ ሰው ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ አካል፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደኾነ ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፤ ዳግመኛ ፤ የፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መድኃኒት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ታመመ ፡ ሞተ ፤ እሱ ግን ፤ መቸም ፡ መች ፡ እሱ ፡ ነው ፤ መለኮት ፡ ፈጽሞ ምንም ፡ ምን ፡ አልተለወጠም ፡ አለ ፤ እሱ ፡ መቸም መች ፡ በአንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ በአንድ ዙፋን ፡ የሚኖር ፡ እንደኾነ ፡ የምታወቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሰው በኾነ ፡ ጊዜም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ ነገሩ ፡የታወቀ ፡ የተረዳ ፡ ነው ፡ አለ ።

፫ ፤ ዳግመኛም ፤ አስቀድሜ ፡ እንደ ፡ ተናገርኩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ የማይታመም የማይሞት ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ተጻፈም ፤ ክርስቶስ ፡በሥጋ ታመመ ፡ እላለሁ ፡ እንጂ ፤ አለ ፡ ዳግመኛ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ የማይታመም ፤ የማይሞት ፡ ነው ፤ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ተናገሩ፡ ከእኛ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ ታመመ ፤ እሱም ፡ ከሚታመም፡ሥጋ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ፡ይኖራል ፡ አለ ፡ ዳግመኛ፡ በሥጋ፡ ታመመ ፡ በመለኮት ፡ አልታመመም ፡ አለ ፤ እግዚአብሔርስ ፡ በመለኮት ፡ ባሕርይ የማይታመም፡ የማይሞት፡ ነው፤ ከእኛ ፡በነሣው፡ሥጋ ታመመ ፡ እንጂ ፡ እሱ ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር፡ ነፍስ ፡ ከአለችው ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ አለ።

፬ ፤ ዳግመኛም ፡ እሱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንደኾነ፡ ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀርም ፡ የእኛን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ እንደሠራ ፤ ስለእሱ ፡ እንናገራለን ፡ አለ ፡ ባሕርያት፡ የሚፋለሱ ፡ የሚናዋወጡ ፡ ከኾኑ ፤ የመድኃኒታችን የክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ከእሳቸው ፡ የተደረገላቸው፡ ባሕርያት ፡ ብዙዎች ፡ መኾናቸው ፡ ነው ፤ ተዋሕዶ ግን ፡ መላልሰን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ መፋለስን ፤ መለዋወጥን ፤ የሁለቱ ፡ ባሕርያት ፡ መለያየትን ፡ ያጠፋል ፤ እነዚህም ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ናቸው ፤ እኛስ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተዋሕዶ፡ ዐማኑኤል ፡ ከእነርሱ ፡ አንድ ፡ የኾነላቸውን ፡ የባሕርያትን መለያየት ፡ ያራቀ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከማይመረመር፡ተዋሕዶም፡ በኋላ፡ ሁለት፡ አካል ፤ ሁለት፡ ባሕርይ፡ እንዳይባል ፡መለያየትን፡ አራቀ ፡ ብለን ፡ እንናገራለን ፡ አለ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፸፬ ።

፩ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ወኢሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ በመለኮት ፤ ውእቱሰ ፡ ይትገመር ፡ በሥጋ ወለሊሁ ፡ ኢይትገመር ፡ በመለኮት ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ እምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመኒ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ኮነ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢይትዌለጥ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወእመኒ ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ፍጡራን ፡ ውእቱ ፡ ይትሌዐል ፡ እም ዙሉ ፡ ፍጥረት ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ ሐጋጌ ፡ ሕግ ፡ ወሠራዒሃ ፡ ውእቱሰ ፡ ቦአ ፡ ታሕተ ፡ ሕግ ፡ ወእንዘ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአምላክ ፡ ነሥአ ሎቱ ፡ አርአያ ፡ ገብር ፡ ወቦቱ ፡ ማዕርግ ፡ ዘመንግሥት

፪ ፤ ዓዲ ፡ ይቤ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ ወእፎኑ ፡ ኮነ ፡ በዝንቱ ፡ ማዕርግ ፡ አሐደ ፡ ዘኢተፈጥረ ምስለ ፡ ፍጡራን ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወእኮ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ አብድ ፡ ከመዝ ፡ ዘይቤ ፡ እስመ ፡ ባሕርይ ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምዙሉ ፡ ፍጥረት ፡ ባሕርያት ፡ ሐመ ፡ ወይሬስዮ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘይትሌዐል ፡ እምዙሉ ፡ ግብር ፡ ለኅበ ፡ ድካመ ፡ ፍጡራን ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ መሲሐውያን ፡ ነአምሮ ፡ በዝንቱ ፡ አርአያ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ሐመ ፡ በሥጋሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወኢሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ በመለኮቱ ።

፫ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ወኢንበ ፡ አውረደ ፡ ሥጋሁ ፡ እምሰማይ ፡ ምስሌሁ ፡ ውእቱ ፡ አስተርአየ ፡ በምትህት ፡ ሐሰ ፡ ሎቱ ፡ እምዝንቱ ፡ አላ ፡ ነአምን ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ነሥአ ፡ ሥጋ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወጸረቶ ፡ በከርሣ ፡ ፱ተ ፡ አውራኁ ፡ ወወለደቶ ፡ ወተፀንሰቱኒ ፡ ኮነ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእኮ ፡ እምዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ወባሕቱ ፡ ንሕነሰ ፡ ኢንበ ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ዘተወልደ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ተወለጠ ፡ በከዊነ ፡ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ እስመ ፡ ኢይትከሀል ፡ ይትወለጥ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ለከዊነ ፡ መለኮቱ ፡ ዘኢተፈጥረ ።

፬ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዘፍሉጥ ፡ እምዙሉ ፡ ዓለም ፡ በህላዌሁ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይትማሰሎ ፡ ወእሙር ፡ ውእቱ ለሊሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ቦአ ፡ ኀቢሃ ፡ ወኮነ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ ወኢዐረቀ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንሕነ ፡ ንሰግድ ፡ ሎቱ ፡ ምስለ ሥጋሁ ፡ አሐተ ፡ ስግደተ ፡ እስመ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ውእቱ ፡ ለአቡሁ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኢሐመ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ በአካል ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ወዘይመውት ፡ ወባሕቱ ፡ ዘተወልደ ፡ እምድንግል ፡ ቅድስት ፡ ዘተፈጥረ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳል ፡ ዘኢይትነገር ፡ ቦቱ ፡ ተርእየ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ተሰምየ ፡ ወልደ ፡ ዋሕደ ፡ ነአምን ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ወልድ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ወውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘበአማን ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፸፭ ።

፩ ፤ ዳግመኛ ፤ በሥጋ ፡ ታመመ ፤ በመለኮት ፡ ግን ፡ ሕማም ፡ የሌለበት ፡ ነው ፤ እሱ ፡ በሥጋ ፡ በአጭር ፡ ቁመት ፤ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ይወሰናል ፤ በመለኮት ፡ ግን ፡ አይወሰንም ፤ እሱ ፡ በሰማይ ፤ በምድር ፡ ምሉ ነው ፡ አለ ፤ አምላክ ፡ እሱ ፡ ሰውም ፡ ቢሆን ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አይለወጥም ፤ እሱ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰውም ፡ ቢኾን ፡ እሱስ ፤ ከፍጡራን በላይ ፡ ነው ፤ ሕግን ፡ የሠራ ፤ የወሰነ ፡ ሲኾን ፤ እሱ ድኀረ ፡ ዘመን ፡ ተገኘ ፡ ፈጻሚ ፡ ሕግ ፡ ተባለ ፤ ገዥ ፡ ፈጣሪ ፡ ሲኾን ፤ እሱ ፡ የተገዥ ፡ የአዳምን፡ ባሕርይ ፡ ተዋሐደ ፤ የባሕርይ ፡ መንግሥት ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፡ አለ ።

፪ ፤ ዳግመኛ ፤ እሱስ ፡ የማይታመም ፡ ነው ፡ አለ ፤ ፈጣሪ ከፍጡራን ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡ ማዕርግ ፡ (ሕማም ፡ ሞት) እንደምን ፡ አንድ ፡ ኾነ ? አለ ፡ ዳግመኛም ፤ ክርስቶስ ስስ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ያይደለ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ አለ ፤ ዳግመኛም ፤ እንዲህ ፡ ከባሕርያት ፡ ሁሉ፡ በላይ የኾነ ፡ ባሕርይ ፡ ታመመ ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ፤ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ቀዳማዊ ፡ እሱን ፡ እንደ፡ ፍጡራን ፡ ደካማ ፡ ያደረገው ፤ ይህ ፡ ዐላዋቂ ፡ ማነው ? አለ ፡ እኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፤ በሥጋው ፡ ብቻ እንጂ ፡ ታመመ ፤ በመለኮቱ ፡ ግን ፡ ሕማም ፡ እንደሌለበት ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ እናውቀዋለን ፡ አለ ።

፫ ፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ የተዋሐደውን ፡ ሥጋ' ከሰማይ ፡ ይዞ ፡ መጣ ፤ እሱም ፡ በሐሰት ፡ ታየ ፡ እንልም ፤ እንዲህ ፡ አይባልም ፤ አምላክን ፡ ከወለደች ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ እንደነሣ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከአምስት ፡ ቀን በማሕፀኗ ፡ እንደ ፡ ወሰነችው ፤ እንደ ፡ ወለደችው፤ መፀነሱም ፡ በዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ያይደለ ፤ በግብረ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደኾነ ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፡ እኛም ፡ ከእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ የተገኘ ፡ ሥጋ፡ የመለኮትን ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ተለወጠ ፡ አንልም ፤ የተፈጠረ ፡ ሥጋ ፤ ያልተፈጠረ ፡ የመለኮትን ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ሊለወጥ ፡ አይቻልምና

፬ ፤ ዳግመኛም ፤ በባሕርይ ፡ ከዓለም ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ የሚኾን ፤ የሚመስለው ፡ የሌለ ፤ የታወቀ ፡ እሱ ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ባሕርይዋን ፡ ባሕርይ ፡ አድርጎ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱም፡ አልተለየም ፤ ስለዚህም ፤ እኛ ፡ ለአባቱ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ ሥጋውን ፡ ሳንለይ ፡ አንዲት ፡ ስግደትን ፡ እንሰግድለታለን ፡ አለ ፡ ዳግመኛም ፤ ሥጋን ፡ ሳይዋሐድ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አልታመመም ፤ ፍጡር ፤ ፍዋቴ ፡ ከኾነ ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በማይመረመር ፡ ተዋሕዶ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ የተወለደው ፡ እሱ ፡ በሥጋ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተገለጠ ፤ አንድ ፡ ወልድ ፡ ተባለ ፤ እሱ ፡ ወልድ ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር አንድ ፡ እንደሆነ ፡ በውነት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ፡ እንደኾነ ፡ በእርሱ ፡ እናምናለን ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፪፭፬ ።

ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

፲፬ ፤ እመልእክተ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ጎበ ፡ ነገሥት ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ብእሲ ፡ ዕሩቅ ፡ በባሕቲቱ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ረድኡ ፡ በጥበብ ፡ ወበለብዎ ፡ ልብ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ በፈቃዱ ፡ ወኢሐመ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወለሊሁ ፡ ርሑቅ ፡ እምኵሉ ፡ ሕማም ፡ ወነኪር ፡ እምኔሁ ፡ ሕማም ፡ ወባሕቲቱ ፡ ሐመ ፡ ይእዜ ፡ በሥጋሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ በከመ ፡ ተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ወወእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡ በህላዌሁ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወከመዝ ፡ ነአምሮ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ተቀብዐ ፡ ከመ ፡ ሥርዓተ ፡ ትስብእት ፡ ወዳእሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቀብዕ ፡ ርእሶ ፡ በመንፈሱ ፡ ባሕቲቱ ።

፲፭ ፤ ይቤ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ፡ በመልእክቱ ፡ ጎበ ፡ አቅላንድዮስ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐማሚ ውእቱ ፡ በሥጋ ፡ ወኢሐማሚ ፡ በመለኮት ፡ ለሊሁ ፡ ይትገመር ፡ በሥጋ ፡ ወኢይትገመር ፡ በመንፈስ ፡ ወውቱሰ ፡ ክመ ፡ ሰማያዊ ፡ ወውእቱ ፡ ምድራዊ ፡ ያስተርኢ ፡ ወኢያስተርኢ ፡ ይትሌበው ፡ ወኢይትሌበው ፡ ወባሕቲ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ፍጹም ፡ ብእሲ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውእቱ ፡ ሐደሰ ፡ ፍጥረቶ ለብእሲ ፡ ዳግመ ፡ ዝንቱ ፡ ዘወድቀ ፡ በኃጢአት ።

፲፮ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ መምህር ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ወርእሰ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ዐምደ ፡ ሃይማኖት ፡ በድርሳኑ ፡ እንዘ ፡ ያወሥእ ፡ ለአቡሊናርዮስ ፡ ዓላዊ እስመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ኢይትዌለጥ ፡ ወኢይትመየጥ ፡ እምህላዌሁ ፡ እስመ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወቦቱ ፡ አካል ፡ ፍጹም ፡ ከመ ፡ አቡሁ ፡ ወኢፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘከነ ፡ ፩ደ ምስሌሁ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምኔነ ፡ እሙነ ፡ ወኢኮነ ፡ ልደቱ ፡ እምዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ በአስተሐውዞ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ አላ ዳእሙ ፡ ተወልደ ፡ እምድንግል ፡ ቅድስት ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወይትሌዐል ፡ እምልቡና ፡ ወፍሉጥ ፡ እምሕገ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፲፯ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እንዘ ፡ ያወሥእ ፡ ለአቡሊናርዮስ ረሲዕ ፡ ረስዮ ፡ ለሥጋ ፡ ይልህቅ ፡ በበሕቅ ፡ በከመ ሥርዓተ ፡ ሰብእ ፡ በዘይደሉ ፡ ለሥጋ ፡ ከመ ፡ ኢይረስይዎ ፡ ለዐማኑኤል ፡ አምላክነ ፡ ውዑአ ፡ እምልማደ ፡ ሰብእ ፡ በካልእ ፡ ምግባር ፡ ወተመሰለ ፡ በሁሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኢርሕቀ ፡ መለኮት፡ ወኢተፈልጠ ፡ እምእሱ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ በከመ ፡ ሥርዓት ፡ እንተ ፡ ዘሥጋዌ ፡ መፍቅድ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ተሠግዎቱ ፡ ለመድኀን ፡ ከመ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፪፭፬ ።

ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

፲፬ ፤ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ እንደሆነ ፤ በብቻው ፡ ያለ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እንዳይደለ ፡ ሲያስረዳ ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ወደ ፡ ነገሥት ፡ (አርቃደዮስና ፡ ቴዎዶስዮስ) ከላከው ፡ መልእክት፤ ደቀ፡ መዝሙሩ ፡ ጴጥሮስ በሃይማኖት ፡ በማስተዋል ፡ ክርስቶስ ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡እንዳልታመመ ፡ስለ ፡ እሱ ፡ ተናገረ ፡ እሱ ፡ ከሕማም፡ሁሉ የራቀ ፡ ነው ፤ ሕማምም ፡ ከእሱ ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ ግን ፤ በሥጋ ፡ ብቻ ፡ ታመመ ፤ ሰው ፡ እንደ መኾኑ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፤ አምላክ ፡ እንደ ፡ መሆኑ በባሕርዩ ፡ ሕማም ፡ የሌለበት ፡ ነው ፤ ተብሎ ፡ ስለ እሱ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፤ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ እናውቀዋለን ፤ ግን ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ራሱን ፡ የሚያከብር ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲፭ ፤ አንድነትን ፤ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ወደ አቅላንድዮስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ የሚታመም ፤ በመለኮቱ ፡ የማይታመም ፤ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ይወሰናል ፤ በመለኮት፡ አይወሰንም ፤ እሱስ ፡ መቸም ፡ መች ፡ ሰማያዊ ፡ ነው ፤ ምድራዊም ፡ ነው ፤ ይታያል ፤ አይታይም ፤ ይመረመራል ፤ አይመረመርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሲኾን ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ በኃጢአት ፡ ወድቆ ፡ የነበረ ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ እንደገና ፡ አደሰ ።

፲፮ ፤ ዳግመኛም ፤ የሃይማኖት ፡ ዐምድ ፡ መምህር ፡ ሊቀ ጳጳሳት ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ከሐዲው ፡ አቡሊናርዮስን ፡ ሲከራከረው ፡ በተናገረው ፡ ድርሳኑ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃልስ ፡ ሕማም ፤ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ነው ፤ ከባሕርዩም ፡ አይለወጥም ፤ አይፋለስም ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ እንደ፡ አባቱ ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ አለው ፤ ከእሱ ፡ ጋር አንድ ፡ የኾነ ፡ ሥጋንም ፡ ሊዋሐደው ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አልፈጠረም ፤ በውነት ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ነሣ ፡ እንጂ ፤ ከሰው ፡ ወገን ፡ መወለዱም ፡ ሰው ፡ ደስ ብሎት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፤ በማይመረመር ፤ ከልቡና ፡ በራቀ ፡ ከሰው ፡ ባሕርይ ፡ ልማድ ፡ ልዩ ፤ ድንቅ ፡ በኾነ ፡ ሥራ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ተወለደ ፡ እንጂ ።

፲፯ ፤ ዳግመኛም ፡ ከሐዲው ፤ አቡሊናርዮስን ፡ ሲከራከረው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ በሥጋ ፡ በሚገባ ፡ መጠን ፡ ሥጋን ፡ በየጥቂቱ እንዲያድግ ፡ አደረገው ፡ ፈጣሪያችን ፡ ዐማኑኤልን ምትሃት ፤ ጎድረት ፡ በማለት ፡ ከሰውነት ፡ ሥርዓት ፡ የወጣ ፡ እንዳያደርጉት ፤ ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ዳግመኛ ፡ የተወደደ ፡ የሥጋዌ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ መኾኑ መለኮት ፡ ከእነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ ባሕርያት ፡ ከነ ፍሱ ፤ ከሥጋው ፡ አልተለየም ፤ አልራቀም ፡ ብሎ ስለ ፡ እርሱ ፡ ተናገረ ፤ ዳግመኛም ፤ መድኀን ፡ ሰው፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ሲናገር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተናገረ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

፲፰ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንዘ ፡ ይትዋ ሥኦ ፡ ለታኦድሪዎስ ፡ ነአምን ፡ ከመዝ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ህላዌያዊ ፡ ወሎቱ ፡ እዘዘ ፡ ኵሉ ፍጥረት ፡ በባሕርይሁ ፡ ወለሊሁ ፡ ነሥኦ ፡ አርአያ፡ ገብር ፡ ወተለዐለ ፡ መልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወከነ ፡ ፩ደ ፡ ምስለ ፡ ፍጡራን ፡ ሰበ ፡ ኮነ ፡ ብእሴ ፡ ፍጹመ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ሶበሰ ፡ ኢተዋሐደ ፡ ምን ትኑ ፡ ውእቱ ፡ አርአያ ፡ ገብር ፡ ምስለ ፡ እግዚእ ፡ ወምንትኑ ፡ ዘዕጓለ ፡ እመሕያውሂ ፡ ምስለ ፡ መለ ኮት ፡ አው ፡ በግዕሂ ፡ ምስለ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አበው ፈጣሪ ፡ ምስለ ፡ ፍጡር ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ንሕነሰ ፡ ንረክቦ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አምላክ ፡ ወው እቱ ፡ ሰብእ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚእ ፤ ወለሊሁ ፡ ገብር ፡ ለሊሁ ፡ በግዕ ፡ ወለሊሁ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወውእ ቱሰ ፡ ፍጡር ፡ ወፈጣሪ ፡ ውእቱ ፡ ኢይደሌመር ፡ ወኢይቶሳሕ ፡ ዘሀለወ ፡ ቦቱ ፡ ዐማኑኤል ፡ አምላ ክነ ፡ አላ ፡ ባሕቲቱ ፡ ነአምሮ ፡ ገሀደ ፡ ፩ደ ፡ ወውእቱ ፡ ክመ ፡ እምፍና ፡ መለኮት ፡ ወት ስብእት ።

፲፱ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ተሰምየ ፡ ገብረ ፡ ወውእቱ ፡ እግ ዚአ ፡ ኵሉ ፡ ከመ ፡ እምላክ ፤ ለሊሁ ፡ በግዕ ፡ ወለ ሊሁ ፡ ካህን ፡ ዓዲ ፡ ኅቡረ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሦበ ርእሶ ፡ ባሕቲቱ ፡ በከመ ፡ ንቤ ፡ ቅድመ ፡ አዕረገ ፡ ሥጋሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ በፈቃዱ ፡ መሥዋዕተ ፡ ውኩፈ ወዕጣን ፡ ምዑዘ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አበሁ ፡ በእን ቲአነ ፡ ለሊሁ ፡ ፍጡር ፡ ወለሊሁ ፡ ፈጣሪ ፡ ንብሎ፡ ፈጣሪ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ወእግ ዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወዓዲመ ፡ ንብሎ ፡ ፍጡረ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተወልደ ፡ በሥጋ ፡ እምብእሲት፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ዓምደ ፡ ሃይማኖት ፡ በእን ቲአሁ ፡ ትብልኑ ፡ እስመ ፡ ዘተፀንሰ ፡ ካልዕ ፡ ውእቱ ዘምስለ ፡ ፈጣሪ ፡ በከመ ፡ በውስተ ፡ መለኮት ፡ ወት ስብእት ፡ ወፈጣሪ ፡ ወፍጡር ፡ ፍልጣን ፡ ሐሰ ፡ ለነ ፡ እምዝንቱ ፡ ንባብ ፡ ሙሱን ፡ ወርኩስ ።

፳ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርቄስ ፡ እምቃለ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ቴዎንሎስ ፡ ወውእቱሰ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ወኢሐመ ፡ በመለኮት ፡ ይትገመር ፡ በሥጋ ፤ ወኢ ይትገመር ፡ በመንፈስ ፡ ወውእቱ ፡ ክመ ፡ ሰማያዊ ፡ ወውእቱ ፡ ምድራዊ ፡ ያስተርኢ ፡ ወኢያስተርኢ ፡ ይጸወር ፡ ውእቱ ፡ ወውእቱ ፡ ኢይጸወር ፡ ወባሕቱ፡ እንዘ ፡ ኵለንታሁ ፡ ብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ወለሊሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ይፈጥር ፡ ብእሴ ፡ ፍጹመ ምዕረ ፡ ዳግመ ፡ ዘወድቀ ፡ በኃጢአት ፡ ወአግ ብእ ፡ ውስተ ፡ ርስቱ ፡ ዘቀዳሚ ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በዝንቱ ፡ ክፍል ፡ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ፈጠረ ፡ ሰብእ ፡ ወእምዝ ፡ ዐአ ፡ ውስቴቱ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ዝንቱሰ ፡ ኢኮነ ፡ ተወላዴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳእሙ ፡ ገዐያዩ ፡ እምልደት ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፭ ።

፲፰ ፤ ዳግመኛ ም ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ታኦድሪዎስን ፡ ሲከ ራከረው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እሱ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ እንደሆነ ፤ በባሕርዩ ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጥሮ ፡ መግዛት ፡ ገንዘቡ ፡ እንደሆነ ፤ የተገዥ ፡ የአዳምን፡ ባሕርይ ፡ ቢነሣም ፡ ከፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ እን ደሆነ ፤ ፍጹም ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲህ ፡ እናምናለን ፡ አለ ፤ ዳግመኛም ፤ ካልተዋሐደማ ፡ ተገዥ ፡ ከተ ገዥ ፡ ጋር ፡ የሰው ፡ ባሕርይ ፡ ከመለኮት ፡ የሚሠ ዋው ፡ ከሠዋዒው ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ፈጣሪ ፡ ከፍጡር ጋር ፡ ምን ፡ አንድነት ፡ ነበረው ? እኛስ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ወልድን ፤ አምላክ ፡ ሰው ፤ ገዥ ፤ ተገዥ ፤ ሠዋዒ ፤ ተሠዋዒ ፤ ፍጡር ፤ ፈጣሪ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘ ዋለን ፤ ፈጣሪያችን ፤ አማኑኤል ፡ የተባለበት ፡ ምሥ ጢር ፡ አይደባለቅም ፤ አይቀላቀልም ፤ ብቻ ፡ እሱ ፡ አንድ ፡ እነደሆነ ፡ በጉላ ፡ በተረዳ ፡ ነገር ፡ እናው ቀዋለን ፡ እንጂ ፤ እሱ ፡ ከመለኮትና ፡ ከትስብእት ፡ ተዋሕዶ ፡ የተነሣ ፡ መቸም ፡ መች ፡ አንድ ፡ ነው ።

፲፱ ፤ ዳግመኛም ፡ አገለገለ ፡ ተባለ ፤ ግን ፡ እሱ ፡ አምላክ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ ነው ፤ እሱ መሥዋዕት ፡ ነው ፤ ወዲህም ፡ ከመሥ ዋዕቱ ፡ የማይ ለይ ፡ ካህን ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ብቻ ፡ ሥጋውን ፡ በፈቃዱ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ የተወደደ ፡ ዕጣን ፡ አድርጎ ስለ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀ ረበ ፡ ብለን ፡ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ እሱ ፡ ራሱን ፡ ብቻ ፡ ሠውቶዓልና፡ እሱ፡ ሰው፡ ነው፤ እሱ፡ አምላክ ፡ ነው፤አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ስለሆነ፡ፈጣሪ እንለዋለን ፤ ወዲህም ፡ ከድንግል ። በሥጋ ፡ ስለተወ ለደ ፡ ሰው ፡ እንለዋለን ፤ ዳግመኛ ፡ ይህ ፡ ዐምደ ፡ ሃይማኖት ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ ስት ናገሩ ፡ በመለኮትና ፡ በትስብእት ፤ በፈጣሪና ፡ በፍ ጡር ፡ መካከል ፡ መከፋፈል ፡ እንዳለ ፡ አድርጋችሁ የተፀነሰው ፤ ከፈጣሪ ፡ ጋር ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ትላ ላችሁን ፡ ሌላ፡ አይደለም፡ እኛ፡ ግን፤ እንዲህ፡ ያለ፡የተ ጠላ ፡ የተነቀፈ፡ አነጋገር፡ልንናገር፡አይገባንም፡አለ።

፳ ፤ ዳግመኛም ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አንድነትን ፡ ሦስ ትነትን ፡ ከተናገረ ፡ ከጎርጎርዮስ ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ ሲ ናገር፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፤ በመለ ኮት ፡ አልታመመም ፤ በሥጋ ፡ ይወሰናል ፤ በመለ ኮት ፡ አይወሰንም ፤ እሱ ፡ መቸም ፡ መች ፡ በሰማይ፡ ያለ ፡ ነው ፤ በምድርም ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ይታያል ፤ አይ ታይም ፤ ይቻላል ፤ አይቻልም ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ሁለተ ናው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሲኾን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ፍጹም አምላክ ፡ ነው ፡ በኃጢአት ፡ ወድቆ ፡ የነበረ ፡ አዳ ምን ፡ በፍጹም ፡ ሰውነት ፡ እንደገና ፡ አድሶ ፡ ወደ ቀደመ ፡ ርስቱ ፡ መለሰው ፡ ዳግመኛም ፡ በዚህ ፡አን ቀጽ ፡ ሰው ፡ ፈጥሮ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር አደረበት፡ የሚል፡ ቢኖር፡ ይህ፡ ሰው ፡ከእግዚአብሔር የተወለደ ፡ አይደለም ፡ክልጅነት፡ የተለየ፡ ነው፡እንጂ

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፬ ።

፭፻፭ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እመሰ ፡ ኮነ ፡ ንብል ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ ቃል ፡ እም ቀዲሙ ፡ ይደሉኬ ፡ ከመ ፡ ይትበሀል ፡ እሙን ፡ ከመ ፡ ይትለዓል ፡ ኀበ ፡ ዘይትሌዐል ፡ ህላዌሁ ፡ ወኢተርፈ ፡ እንከ ፡ ወውእቱሰ ፡ ህልው ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወሶበሂ ፡ ንቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተርፈ ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ባሕቲቱ ፡ ወኢኮነ ፡ ምግባረ ፡ ሕሙመ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኢኀደጎ ፡ ለሥጋ ፡ እምኔሁ ከመ ፡ ይኩን ፡ ህልወ ፡ ወፍጡረ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወይትግሠሥ ፡ ወገዚፈ ፡ ወሶበሂ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ኢተፈልጠ ፡ እምኔሁ ፡ ቃል ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘኢተፈጥረ ፡ ወዘኢያስተርኢ ፡ ወዘኢይ ትግሥሥ ።

፭፻፮ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ እም፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ኮነ ፡ ፩ደ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ደ ፡ አካለ ፡ ወ፩ደ ፡ ገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሠገወ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይገብር ፡ ምግባራተ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮት ፡ ወትሰ ብእት ፡ ከመ ፡ ይትወሐድ ፡ በዝንቱ ፡ ወይኩን ፡ ፩ደ ፡ ኅቡረ ፡ ፈጣሪ ፡ ምስለ ፡ ፍጡር ፡ ዘኢይትግ ሠሥ ፡ ምስለ ፡ ዘይትግሠሥ ፡ ወዘኢያስተርኢ ፡ ምስለ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመ ለኮቱ ፡ ወለነኒ ፡ ይትዔረየነ ፡ በትስብእቱ ፡ ወዝ ውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ።

፭፻፯ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመኒ ፡ ወልድ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወህላዌ ፡ ልዑላዊ ፡ ውእቱ ፡ በልዕልና ፡ መለኮት ፡ ኮነ ፡ ትሑተ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ በእንቲአነ ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ወዘ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ህልው ፡ ዓዲ ፡ በአምላክናሁ ፡ ወኢይትቄለጥ ፡ ወበዝንቱ ፡ አርአያ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ወውእቱ ፡ ኢፍጡር ፡ በህላዌ ፡ መለ ኮቱ ፡ ወዳእሙ ፡ ተሰምየ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይባልሐነ ፡ እምአርዑተ ፡ ቅኔ ፡ መሪር ፡ ዘውእቱ ፡ አግዚ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ።

፭፻፰ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ብዙዕ ፡ ቄርሎስ ፡ መም ህረ ፡ ሃይማኖት ፡ እመሰ ፡ ይቤ ፡ ክርስቶስ ፡ አቡየ ፡ የዐቢ ፡ እምኔየ ፡ ወዝንቱሰ ፡ ቃል ፡ ይደሉ ፡ ለት ስብእቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዘኢተፈጥረ ፡ ወዘአልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፤ ወከመዝ ፡ ተሰምየ ፡ ፍጡረ ፡ በዝንቱ ፡ አርአያ ፡ በከዊኖቱ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ እሙነ ፡ ይሰምዮ ፡ ለአቡሁ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኔሁ ፡ ዝንቱ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ውእቱ ፡ ሕቀ ፡ ተትሕተ ፡ እመላእክት ፡ በእንተ ፡ ሕማመ ፡ ሞቱ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ይቤ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚአ ፡ መላእክት ፡ ወፈጣሪሆሙ ፡ በእንተ ፡ መቅደሱ ፡ አልቦ ፡ ምንትኒ ፡ ሱታፌ ፡ በውስተ ፡ ፍጡራን ፡ ለመቅደሱ ፡ ከመዝ ፡ ቅድመ እግዚአብሔር ፡ ዘኀደረ ፡ ውስቴቱ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፬ ።

፭፻፭ ፤ ዳግመኛ ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ሥጋ ፡ ከቃል ፡ ጋር ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የነበረ ፡ ነው ፡ የምንል ፡ ከኾነ ፡ ባሕርዩ ፡ ከፍከፍ ፡ ወደሚልበት ፡ ኹኔታ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡ በውነት ፡ ሊነገር ፡ ይገባል ፤ እንኪያስ ፡ አል ቀረም ፤ ግን ፡ እሱ ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ነው ፤ ቀረ ፤ የምንል ፡ ከኾነ ፡ ደግሞ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ነው ፤ የሚያስነቅፈን ፡ አይደለም ፡ አለ ፤ ዳግመ ኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ በፍጡርነት ፡ ነዋሪ ፡ የሚታይ ፡ የሚዳሠሥ ፤ ግዙፍ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሥጋን ፡ ከእሱ ፡ አልለየውም ፤ ሥጋም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፤ ያልተፈጠረ ፤ የማይታይ ፡ የማይዳ ሠሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ከሥጋ ፡ አልተለየም ።

፭፻፮ ፤ ዳግመኛም ፤ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ሰው ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሁለት ፡ ባሕርያት ፤ ከሁ ለት ፤ አካላት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ኾነ ፡ አለ ፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ሰው ፡ የኾነው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ፈጣሪ ፡ ከፍጡር ፡ ጋር ፡ የማይዳሠሠው ፡ ከሚዳሠሠው ፤ የማይታየው ፤ ከሚታየው ፡ ጋር ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ፡ ስለኾነ ፤ በዚህ ፡ አንድ ፡ መኾኑ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፤ ስለዚህ ፡ ለመለኮትና ፡ ትስብእት ፡ የሚገባውን ፡ ይሠራል ፤ በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ እኛንም ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፡ ይመስለናል ፤ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾነው ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፭፻፯ ፤ ዳግመኛም ፤ ወልድ ፡ ጥንት ፡ የሌለው ፡ በመለኮት ፡ ከብር ፤ ልዑል ፡ ባሕርይ ፡ ቢኾንም ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ ያለ ፡ መለወጥ ፡ ያለ ፡ ዘርዓ ፡ ብእሲ ፡ ሰው ፡ ቢኾንም ፡ በአምላክነቱ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ አይለወጥም ፤ በዚህም ፡ በሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ሰውን ፡ መሰለ ፡ እሱ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ፍጡር ፡ አይደ ለም ፤ ግን ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ መገዛት ፡ የሌለ በት ፡ እሱ ፡ ከመራራ ፡ የኃጢአት ፡ መገዛት ፡ ያድ ነን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተባለ ።

፭፻፰ ፤ ዳግመኛ ፡ ይህ ፡ የሃይማኖት ፡ መምህር ፡ ብዙዕ ቄርሎስ ፤ ክርስቶስ ፡ አባቴ ፡ ከእኔ ፡ ይበልጣል፡ ቢል ይህ ፡ አነጋገር ፡ ሰው ፡ ለመኾኑ ፡ የሚስማማ ፡ ነው ፡ አለ ፤ ያልተፈጠረ ፤ ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊትም ፡ ሥጋ ፡ ያልነበረው ፡ እሱ ፤ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ሥጋ ፡ ባሕርዩ ፡ ኾነ ፤ ፍጹም ፡ ሰው ፡ በመኾኑም ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ሰው ፡ ተባለ ፤ ስለዚህም ፡ በውነት ፡ አባቱን ከእሱ ፡ የሚበልጥ ፡ ይለዋል ፤ ስለ ፡ መታመሙ ፤ ስለመሞቱ ፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አነሰ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረለት ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እሱ ፡ አባቱን ፡ በውነት ፡ ከእኔ ፡ ይበልጣል ፡ ይለዋል ፤ እሱ ፡ መላእክትን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ ሲኾን ፡ ስለ ፡ ተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ቢናገርም ፤ በተዋሐደው ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አምላክ ፡ የተዋሐደው ፡ ሥጋን ፡ ከፍጡራን ፡ መካከል ፡ የሚተካከል ፡ ምንም ፡ የለም ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፪፩፬ ፤

፩፩ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመጽሐፈ ፡ ቢሶርስ ፡ ዘውእቱ ፡ ከሣቴ ፡ ጎቡዕ ፡ ብሂል ፡ ውእቱሰ ፡ ብየ ፡ ይትፈሣሕ ፡ ምስሌየ ፡ ወአነሂ ፡ ኮንኩ ፡ እትሐሠይ ፡ ምስሌሁ ፡ ወለሊሁ ፡ ወለደኒ ፡ እምቅድመ ፡ ዅሎሙ ፡ ፍጡራን ፡ ወከመዝ ፡ ዓዲ ፡ አመ ፡ ለብሰ ፡ አርአያ ፡ ሰብእ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒተ ፡ ዅልነ ፡ ይብል ፡ እሙነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኒ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኢፈጠረ ፡ ሥጋ ፡ ዘኮነ ፡ ምስሌሁ ፡ እምህላዌሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ነፍአ ፡ እምኔነ ፡ አኮ ፡ ውእቱ ፡ ልደቱ ፡ እምዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ተወልደ ፡ እምድንግል ፡ ቅድስት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ እንዘ ፡ ኢያርኁ ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልናሃ ።

፩፪ ፤ ወካዕበ ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ፩ዱ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘሰመዮ ፡ መዝገብ ፡ ተርጎመ ፡ ለነ ፡ ሀልዎቶ ፡ ባሕቲቱ ፡ በውስተ ፡ ገጸ ፡ መካናት ፡ ብዙኃት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘእንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወለሊሁ ፡ ፈጠረ ፡ ሥጋሁ ፡ ለርእሱ ፡ ወዝንቱ ፡ ቃል ፡ ያግሀድ ፡ ለነ ፡ ተዋሕዶ ፡ አካል ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመሰ ፡ ተአምኑ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ እሙነ ፡ እፎኑ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይበል ፡ ዘይደልዎ ፡ ለሰብእ ፡ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይበል ፡ ቀዳሚሁሰ ፡ ኢኮንኩ ፡ ሰብአ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይደልዎ ፡ ለህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወይዕቀብ ፡ ዓዲ ፡ ዘይደሉ ፡ ለህላዌሁ ፡ ዘፈጠረ ፡ እስመ ፡ ሰብእሰ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ይብል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኒ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወባሕቱ ፡ እስመ ፡ ሐልዎሰ ፡ በዅሉ ፡ ጊዜ ፡ ዘኢየኀልቅ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባሕቲቱ ።

፩፫ ፤ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ምግባራተ ፡ ወይኩን ፡ ቅድመ ፡ በውስተ ፡ ፍናዋት ፡ ወከመዝ ፡ ዓዲ ፡ ንሕነኒ ፡ ንብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኒ ፡ መቅድመ ፡ ተግባሩ ፡ እስመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ኢተፈጥረ ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ውእቱሰ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ በዅሉ ፡ ጊዜ ፡ ወህልው ፡ ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ በእንተ ፡ ምክንያት ፡ ቀዳሚት ፡ ዘተወጥነት ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ዘውእቱ ፡ ፈጠረ፡ሰብአ ፡ በእንተ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ያድኅኖ ፡ እመርገም ፡ ዘኀደረት ፡ ላዕሌሁ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፪፩፬ ።

፩፩ ፤ ዳግመኛም ፤ ቢሶርስ ፡ በተባለ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሶርስ ፡ ማለትም ፡ የተሰወረውን ፡ የሚገልጽ ማለት ፡ ነው ፤ እሱ ፡ በእኔ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ እኔም ፡ በእሱ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ እሱም ፡ ከፍጡራን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ወለደኝ ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ እኛን ፡ ሁላችንን ፡ ለማዳን ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፤ በውነት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኝ ፤ ይላል ፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ከእሱ ፡ ጋር ፡ የተዋሐደ ፡ ሥጋን ፡ ከብቻ ፡ ባሕርዩ ፡ ፈጥሮ ፡ አልተዋሐደም ፤ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ ነሣ ፡ እንጂ ፤ ልደቱም ፡ በዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ አይደለም ፤ ማኅተመ ፡ ድንግልናዋን ፡ ሳይለውጥ ፡ ያለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ተወለደ ፡ እንጂ ፡ አለ ።

፩፪ ፤ ዳግመኛም ፤ መዝገብ ፡ ባለው ፡ በዚህ ፡ አንድ ፡ መጽሐፉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሳይለወጥ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ ሥጋንም ፡ ሊዋሐደው ፡ ፈጠረ ፡ ብሎ ፡ በብዙ ፡ አንቀጽ ፡ ቅድምናውን ፡ አስረዳ ፤ ይህ ፡ ቃል ፡ የእካልን ፡ ተዋሕዶ ፡ ያስረዳናል ፤ ዳግመኛም ፤ ክርስቶስ ፡ በውነት ፡ ሰው ፡ እንደኾነ ፡ ካመናችሁ ፡ ለሰው ፡ የሚገባውን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እንደምን ፡ አይገባውምን ቀድሞስ ፡ ሰው ፡ አልነበርኩም ፡ ሊልም ፡ ይገባዋል ፤ ይህም ፡ የሚገባው ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፡ ለፈጠረው ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋ ፡ የሚገባውን ፡ ሊጠብቅ ፡ ይገባዋል ፤ ሰው ፡ ፍጡር ፡ ነውና ፡ ስለዚህም ፡ እሱ ፡ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኝ ፡ ይላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዘመን ፡ ሁሉ ፡ መኖር ፡ የማይፈጸም ፡ ነውና ፡ ለእግዚአብሔር፡ብቻ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ አለ ።

፩፫ ፤ ዳግመኛም ፤ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ለትሩፋትም ፡ መምህር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ አለ ፤ እንዲሁ፡ ደግሞ ፤ እኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ አድርጎ ፡ ፈጠረኝ ፡ ማለትን ፡ ሰው ፡ ስለኾነው ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ እንናገራለን፡የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ የነበረ ፡የሚኖር ፡ ቀዳማዊ ፤ ደኃራዊ ፡ ነው ፤ እንጂ ፡ ፍጡር ፡ አይደለምና ፤ ቀድሞ ፡ ተሰጥታ ፡ የነበረች ፡ ልጅነትን ለማምጣት ፡ ሥጋን ፡ ፈጥሮ ፡ ተዋሐደ ፡ እንላለን ፤ ዳግመኛም ፤ አዳምን ፡ ጸንታበት ፡ ከነበረች ፡ ፍዳ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፍጡር ፡ ሥጋን፡ ኾነ፡ ይሸውም፡ ሰውን ፡ የፈጠረ ፡ነው፡አለ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

ፍ፳ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ እንተ ፡ ፈነዋ ፡ ጎበ ፡ ሶክሲስ ፡ ወኢፈጠረ ፡ ዘንተ ፡ ሥጋ ፡ ቅዱሰ ፡ እም ህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምድንግል ፡ ወእመ አኮ ፡ እፎኑ ፡ እምኮነ ፡ ሰብአ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ፡ ለብሰ ፡ ሥጋ ፡ ሰብእ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመጽሐፈ ፡ ቢሶርስ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይቤዘወነ ፡ ወሶበ ፡ ሞተ ፡ ወልድ ፡ ይትበህል ፡ በእንቲአሁ ፡ ውእቱሰ ፡ ተወክፈ ፡ ዘንተ ፡ ወውእቱሰ ፡ ኢይመውት ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወከመዝ ፡ እንከ ፡ ሶበ ፡ ፈጠረ ፡ ሥጋሁ ፡ በእንቲአሁ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ፍጡር ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ረሰየ ፡ ሎቱ ፡ ወህላዌ ፡ መለኮቱሰ ፡ ኢፍጡር ፡ ውእቱ ።

ፍ፳፩ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ንብል ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ዋሕድ ፡ ቃል ፡ ፩ዱ ፡ ጎቡረ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ፍጡር ፡ ወመዋቲ ፡ በሥጋ ፡ ኢፍጡር ፡ ወኢመዋቲ ፡ በመለኮት ፡ ወባሕቱ ፡ እስመ ፡ ሞትሰ ፡ ወተፈጥሮ ፡ ለሥጋ ፡ ውእቱ ፡ ወህላዌ ፡ መለኮትሰ ፡ ነኪር ፡ ውእቱ ፡ እምእሉ ፡ ወባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ዘተዋሐደ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ንብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ወመዋቲ ፡ ኢፍጡር ፡ እንከ ፡ ወኢመዋቲ ፡ በህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመሰ ፡ ተወልደ ፡ ወተፈጥረ ፡ ንሬሲ ፡ እሎንተ ፡ ፻ተ፡ለዘይደሉ ፡ ቦሙ ፡ ተወልደ ፡ ቃል ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡ ዙሉ ፡ ዓለም ፡ በከመ ፡ ንቤ ፡ ንሕነ ፡ ወዘፈጠረ ፡ ሰብአ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ በእንቲአነ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ወንጌላዊ ፡ ብፁዕ ።

ፍ፪ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መፍትው ፡ እንከ ፡ ይልበሶ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ለብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንብል ፡ ለሊሁ ፡ ተፈጥረ ፡ ለተግባሩ ፡ ከመ ፡ ይረስዮሙ ፡ ፍጹማነ ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ በዝንቱ ፡ ቃል ፡ ዘተብህለ ፡ አንሰ ፡ ተፈጠርኩ ፡ ኢያጤይቅ ፡ በእንተ ፡ ባሕርየ ፡ ቃል ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ያሌቡ ፡ ፈድፋደ ፡ እንበይነ ፡ ምጽአቱ ፡ ጎቤነ ፡ ወለቢሶቱ ፡ ሥጋ ፡ ፍጡረ ፡ ከማነ ፡ ዝንቱ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ተፈጥረ ፡ ውእቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ ደለዎ ፡ እሙነ ፡ ይበል ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኒ ፡ ቅድመ ፡ ለፍኖተ ፡ ተግባሩ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

ፍ፳ ፤ ዳግመኛም ፤ ወደ ፡ ሶክሲስ ፡ በላካት ፡ መልእክቱ ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የኾነ ፡ ይህን ፡ ሥጋ ፡ ከድንግል ነሣ ፡ እንጂ ፤ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ፈጥሮ ፡ አልተዋሐደውም ፤ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ ቢዋሐድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ያለዚያማ ፡ እንዴት ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ነበርነአለ ዳግመኛም ፤ ቢሶርስ ፡ በሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ ክርስቶስ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሞተ ፤ ወልድ ፡ በሞት ፡ ጊዜ ፡ ሞትን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፡ ተብሎ ፡ ስለርሱ ፡ ይነገራል ፤ እሱ ፡ ግን ፡ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አይሞትም ፤ እንዲህ ፡ ሥጋን ፡ ፈጥሮ፡ ስለ ፡ ተዋሐደም ፡ እሱ ፡ ሰው ፤ ኾነ ፡ ይባላል ፤ የተፈጠረ ፡ ሥጋን ፡ ለእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓልና ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ግን ፡ ፍጡር ፡ አይደለም ።

ፍ፳፩ ፤ ዳግመኛም ፤ ስለዚህ ፡ ተቀዳሚ ፤ ተከታይ ፡ ስለ ፡ ሌለው ፤ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ስለኾነ ፡ ቃል ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ፍጡር ፤ መዋቲ ፡ ነው ፤ በመለኮት ፡ ግን ፡ ፍጡር ፡ መዋቲ ፡ አይደለም ፡ እንላለን ፤ መፈጠርና ፡ ሞት ፡ ለሥጋ ፡ ነው ፤ መለኮት ፡ ግን ፡ ከመፈጠርና ፡ ከመሞት ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፤ ሥጋን ፡ ስለ ፡ ተዋሐደ ፡ ፍጡር ፡ መዋቲ ፡ ነው ፡ እንላለን ፤ በባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ግን ፤ ያልተፈጠረ ፤ የማይሞት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንናገራለን ፡ ከተወለደ ፡ ሰው ፡ ከኾነ ፤ እነዚህን ፡ ሁሉን ፡ ለሚገባቸው ፡ እናደርጋለን ፤ እኛ ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ከአብ ፡ ተወለደ ፤ ወንጌላዊ ፡ ብፁዕ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ሰውን ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ አለ ።

ፍ፪ ፤ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፡ ፍጹም ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹም ፡ ሥጋን ፡ ሊዋሐድ ፡ ይገባዋል ፤ ስለዚህም ፡ ፍጥረቶቹን ፡ ፍጹማን ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ እንላለን ፤ ዳግመኛም ፤ እኔ ፡ ተፈጠርኩ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፤ ስለ ፡ ቃል ፡ ባሕርይ ፡ አያመለክትም ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ፍጡር ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ ተፈጠረ ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ የተነገረለት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ፡ ዳግመኛም ፤ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ ፍጥረቶቹ ፡ ሊድኑበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኝ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ተገባው ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

፴፩ ፤ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ ካልኣ ፡ ክፍል ፡ እመጽሐፍ ፡ ቀዳማዊ ፡ እንተ ፡ ዘቢሶርስ ፡ ወአኮ ፡ ዘይፈክር ፡ ለነ ፡ ሐዋርያ ፡ ህላዌ ፡ ቃል ፡ እስከ ፡ ይብል ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ ከመዝ ፡ አላ ፡ ሥጋሁ ፡ ውእቱ ፡ ማዕዜኑ ፡ ኮነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እምነትነ ፡ ወኮነ ፡ ሐዋርያ ፡ ወማእዜኑ ፡ ኮነ ፡ ምእመነ ፡ በኀበ ፡ ዘገብሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ እምጊዜ ፡ ኮነ ፡ ባቲ ፤ ሰብእ ፡ በእንቲአነ ፡ ወኮነ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ በሥርዓት ፡ ኦሪሃ ፡ ኮነ ፡ ምእመነ ፡ በኀበ ፡ ዘገብሮ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈጽም ፡ ግብረ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ለሊሁ ፡ እሜሃ ፡ ኮነ ፡ ሐዋርያ ፡ ሶበ ፡ ተፈነወ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይቡዝወነ ፡ እሜሃ ፡ ኮነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናተ ፡ እምነትነ ፡ እንዘ ፡ ይስእሎ ፡ ለአቡሁ ፡ እምነተ ፡ ሃይማኖትነ ፡ ወያዐርግ ፡ ሥጋሁ ፡ በፈቃዱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ከመ ፡ ዕፍረት ፡ ምዑዝ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ደነስ ፡ ከመ ፡ ያን ጽሐነ ፡ ለኵልነ ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ ፩ና ፡ ፲፯ ።

፴፪ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ አአምን ፡ ወእትአመን ፡ ኀሀዱ ፡ በቃል ፡ ዘእምእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተሠገወ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወኢንከፍሎ ፡ ጎበ ፡ ጌቱ ፡ ክፍል ፡ ለዘውእቱ ፡ ለክሰ ፡ እምነ ፡ ለባሲሁ ፡ አው ለመቅደስ ፡ እምዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ ወለእርአያ ፡ ኀብር ፡ እምአርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወለበግዕኒ ፡ እምነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወለነሣኢ ፡ እምነ ፡ ዘነሥአ ፡ ወለዘተፈጥረ ፡ ውስተ ፡ ማሕፀነ ፡ ድንግል ፡ እምነ ፡ ፈጣሪ ፡ ወባሕቱ ፡ እስመ ፡ ብሂልሰ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ረሰየ ፡ ፭ደ ፡ ምስሌሁ ፡ እመሰ ፡ ትፈቅድ ፡ ተሐልዮ ፡ በህላዌ ፡ ሠናይኬ ፡ ሐልዮትክ ፡ በእንተ ፡ ሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም ።

፴፫ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እለሰ ፡ ይብሉ ፡ እስመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢተፈጥረ ፡ ኮነ ፡ ፭ደ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተፈጥረ ፡ አው ፡ ተገብረ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ሥጋ ፡ ዘውእቱ ፡ ኮነ ፡ ብእሴ ፡ ፍጹመ ፡ ዘእንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወለሊሁ ፡ ዓዲ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይትዌለጥ ፡ ወኢይሑሩ ፡ እንከ ፡ ካልኣ ፡ እምፍኖት ፡ ርትዕት ።

፴፬ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢተቀብዐ ፡ በእንተ ፡ መፍቅድ ፡ ዘቦቱ ፡ አላ ፡ ለሊሁ ፡ ቀባዒ ፡ ውእቱ ፡ ወዐርገ ፡ ጎበ ፡ ሥልጣኑ ፡ መለኮቱ ፡ እንዘ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ወለሊሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተለዐለ ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ ትሕትና ፡ ወሕጸጽ ፡ እንተ ፡ ዘትስብእት ፡ ወንዴት ፡ ወለሊሁ ፡ ጸገዎ ፡ ስመ ፡ ዘላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዝንቱ ፡ ዘኮነ ፡ በህላዌ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ከመ ፡ ያልዕለነ ፡ ለነሂ ፡ ዓዲ ፡ ጎበ ፡ ሀሎ ፡ ዝኩ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

፴፩ ፤ ዳግመኛ ፤ ቢሶርስ ፡ ከተባለው ፡ ከመጀመሪያው ፡ መጽሐፍ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሐዋርያ ፡ ይህን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ መናገር ፡ ደርሶ ፤ ስለ ፡ ቃል ፡ ባሕርይ ፡ የሚናገር ፡ አይደለም ፤ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ሲያመለክት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምናምንበት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የኾነ ፡ ሐዋርያስ ፡ የኾነ ፡ መቼ ፡ ነውን በፈጠረው ፡ ዘንድ ፡ ምእመን ፡ የኾነ ፡ መቼ ፡ ነውን ቃል ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በተዋሕዶ ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ በኾነበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የተላከበትን ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በአብ ፡ ዘንድ ፡ የታመነ ፡ ኾነ ፤ እሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያ ፡ ኾነ ፤ ሃይማኖታችን ፡ እንዲጸና ፡ አብን ፡ ሊለምነው ፤ ሁላችንንም ፡ ከኃጢአት ፡ ያነጻን ፡ ዘንድ ፤ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ራሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሥጋውን ፡ ሲያቀርብ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያመንበት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኾነ ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ ፩ና ፡ ፲፯ ።

፴፪ ፤ ዳግመኛም ፤ እንዲህ ፡ አለ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ቃል ፡ እሱ ፡ ሰው ፡ እንዶኾነ ፡ በነላ ፡ በተረዳ ፡ ነገር ፡ አምናለሁ ፤ እታመናለሁ ፤ ወደ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ አንከፍለውም ፤ የለበሰውን ፡ ሥጋ ፡ ከለባሹ ፤ የተዋሐደውን ፡ ሥጋ ፡ ከተዋሐጁ ፤ አርአያ ፡ ኀብርን ፡ ከአርአያ ፡ እግዚአብሔር — መሥዋዕትን ፡ ከሠዋዒ ፤ ነግኢውን ፡ ከተነግኢ ፤ በድንግልና ፡ ማሕፀን ፡ የተፈጠረ ፡ ሥጋን ፡ ከፈጠረው ፡ ከቃል ፡ አንለየውም ፤ እሱ ፤ ከእሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፤ እንደ ፡ አደረገው ፡ ስለ ፡ መናገር ፡ ግን ፤ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ አደረገው ፡ ልታውቅ ፡ ብትወድ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከማርያም ፡ ስለ ፡ ነሣው ፡ ሥጋ ፡ መመርመር ፡ ማወቅህ ፡ መልካም ፡ ነው ።

፴፫ ፤ ዳግመኛ ፤ እንዲህ ፡ አለ ፡ ያልተፈጠረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የምታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ከአለችው ፡ ከተፈጠረ ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፤ ስለዚህም ፤ ሥጋ ፡ ስለኾነ ፤ ስለ ፡ እርሱ ፡ ተፈጠረ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፤ ይኸውም ፡ ያለ ፤ መለወጥ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እሱስ ፡ ዘላለም ፡ የማይለወጥ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፤ እንግዲህ ፡ ከቀናችው ፡ ጎዳና ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ጎዳና ፡ አይሒዱ ።

፴፬ ፤ ዳግመኛ ፤ ክርስቶስስ ፡ ክብር ፡ መሻት ፡ ኖሮበት ፡ አልከበረም ፤ እሱ ፡ ራሱ ፡ አክባሪ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሰው ፡ ቢኾንም ፡ በባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ ከበረ ፤ እሱ ፡ ራሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ሥጋ ፤ ትሑት ፡ ሕጹጽ ፤ ነዳይ ፡ ስለኾነ ፡ ተለዐለ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረለት ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ስምንም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሰጠው ፡ ተባለ ፤ ይህም ፡ የኾነ ፡ በባሕርይ ፡ ተዋሕዶ ፡ ነው ፤ አምላክ ፡ እንደኾነ ፡ እኛንም ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ያቀርበን ፡ ዘንድ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፱ ።

፴፭፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመጽሐፈ ፡ መዝገብ ፡ ቃለ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወዘፈጠረ ፡ ሥጋ ፡ ፈጠረ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እግዚእ ፡ ለኵሉ ፡ አሐዱ ፡ ቀዳሚ ፡ ለፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተግባሩ ፡ እስመ ፡ ቀዳሚሁሰ ፡ እሳት ፡ ውእቱ ፡ ወሕይወት፡ ክርስቶስ ፡ ዘኢይጸወር ፡ ወእምድኅረ ፡ ጎዳጥ ፡ ይቤ ፡ እመሰ ፡ ሰብአ ፡ ኮነ ፡ ወይፈጽም ፡ ግብረ ፡ ይኩን፡ ፍኖተ ፡ ቀዳማየ ፡ ወከመዝ ፡ እሙን ፡ ንብል በእንቲአሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር፡ ፈጠረኒ ፡ ቀዳሚ ፡ ለፍኖተ ፡ ሠናይቱ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢፈጠረ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ ውስቴቱ ፡ አላ ፡ ውእቱሰ፡ ቀዳማዊ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወሀልው ፡ ዘልፈ ፡ ፈጠረ፡ ሥጋሁ ፡ በእንተ ፡ ምክንያት ፡ ዘተነግረ ።

፴፮፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመሰ ፡ ኮንከሙ ፡ ተአምኑ ፡ ከመ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ እሙነ ፡ ወእፍኑ ፡ ኢይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንበል ፡ ዘይደሉ ፡ ለሰብእ ፡ ዘእን በለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፤ ወይደሉ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ንበል ፡ አንሰ ፡ ኢሀሎኩ ፡ ቀዳሚ ፡ ሰብአ ፡ ዝኩ፡ ዘይደሉ ፡ ለህላዌ ፡ መለኮት ፡ ባሕቲቱ ፡ ወንዕቀብ ፡ ዓዲ ፡ ዘይደሉ ፡ ለህላዌ ፡ ዘበአማን ፡ ዘተፈጥረ ፡ እስመ ፡ ሰብእሰ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኒ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ።

፴፯፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመጽሐፍ ፡ እንተ ፡ ዘቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ በውስተ ፡ ቢሶርስ ፡ በከመ ፡ ጎይል ፡ ለሊሁ ፡ ጎይል ፡ ውእቱ ፡ ዙለንታሁ ፡ ወኢይደክም ፡ ኢይ ትበሀል ፡ በእንቲአሁ ፡ ርኅበ ፡ እስመ ፡ ለሊሁ ፡ መብልዕ ፡ ወሕይወተ ፡ ዙሉ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ረሰየ ፡ ሥጋሁ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘፍ ጥረቱ ፡ ይርኅብ ፡ ወይጸምዕ ፡ ወይደክም ፡ ወከመዝ፡ ኮነ፡ ይኅልቍዎ ፡ ምስለ ፡ ኃጥአን ፡ ዝንቱ ፡ ዘጸረ ፡ ኃጢአተነ ፡ ወተወገሠ ፡ ሕማመነ ፡ በፈቃዱ ፡ ወሞተ ቤዛነ ፡ ተሰቅለ ፡ ክርስቶስ ፡ አኮ ፡ ከዊኖ ፡ ርኁመ ፡ ዳእሙ ፡ ከመ ፡ ያሰስል ፡ መርገመ ፡ ዘቦአ ፡ ውስቴታ አቡነ ፡ አዳም ፡ ተወገሠ ፡ ለተሰቅሎ ፡ በእንቲ አነ ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ዘተዋሐደ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወተወገሠ ፡ ለተወልዶ ፡ ከማነ ፡ እምኢይቤ ዘንተ ፡ ይቤ ፡ አላ ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ ዘውእቱ ፡ እም ድንግል ፡ ቅድስት ፡ በእምሳል ፡ ዘይደሉ ፡ ለትሰ ብእት ።

፴፭፤ ዳግመኛም ፤ መዝገብ ፡ በሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፤ የፈጠረ፡ ለሁሉ ፡ ገዢ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ ፤ እግ ዚአብሔር ፡ ላሰበው ፤ ለፈጸመው ፡ ሥራ ፡ ጀማሪው አንድ ፡ ነው ፤ ክርስቶስ ፡ ጥንቱን ፡ የማይዳሰስ ፡ እሳት ፤ ሕይወትም ፡ ነው ፤ ጥቂትም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ሰው ፡ ቢኾንና ፡ መሪ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሥራን ፡ ቢሠራ ፡ ለቸርነቱ ፡ ሥራ ፡ ጀማሪ ፡ አድርጎ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ፈጠረኝ ፡ አለ ፡ ብለን ፡ እንዲህ ፡ ስለ ፡ እሱ ብቻ ፡ በእውነት ፡ እንናገራለን ፤ እሱስ ፡ ሊያድር በት ፡ አልፈጠረውም፤ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ በቅድምና፡ የነበረ ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ተነ ገረው ፡ ምክንያት ፡ ሥጋን ፡ ፈጠረ ፡ እንጂ ።

፴፮፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ እን ድኾን ፡ በውነት ፡ ካመናችሁ ፡ ከኃጢአት ፡ ብቻ በቀር ፡ ለሰው ፡ የሚገባውን ፡ ልንናገር ፡ እንደምን ፡ አይገባንም ? ዳግመኛም ፡ እሬ ፡ ቀድሞ ፡ ሰው ፡ አል ነበርኩም ፡ አለ ፡ ልንል ፡ ይገባናል ፤ ይህ ፡ የሚገባው ለባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፤ በው ነት ፡ ለተፈጠረ ፡ ለሥጋ ፡ ልንጠብቅ ፡ ይገባናል ፡ ሰው ፡ ፍጡር ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፤ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኝ ፡ ይላል ፡ አሰ ።

፴፯፤ ዳግመኛም ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ በጻፈው ፤ ቢሶርስ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እሱ ፡ ጎይል እንደ ፡ መኾኑ ፡ ሁለንተናው ፡ ጎይል ፡ ነው ፤ ድካም የለበትም ፤ እሱ ፡ ተራበ ፡ አይባልም ፤ እሱ ፡ የሁሉ ፡ ሕይወት ፤ የሁሉ ፡ ምግብ ፡ ነውና ፤ በተለየ ፡ አካሉም ሥጋን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ ባሕርዩ ፡ የሚራብ ፡ የሚ ጠማ ፤ የሚደክም ፡ ይህ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ከኃ ጥአን ፡ ጋር ፡ ይቈጥሩት ፡ ነበር ፤ ኃጢአታችንን ፡ የተሸከመ ፤ በፈቃዱ ፡ የእኛን ፡ መከራ ፡ የተቀበለ፤ ስለ ፡ እኛ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ የሞተ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ክርስ ቶስ ፡ ተሰቀለ ፤ ግን ፡ መርገም ፡ ኖሮበት ፡ አይደለም፤ አባታችን ፡ አዳም ፡ ተይዘበት ፡ የነበረ ፡ መርገምን፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ስለ ፡ እኛ ፡ መሰቀልን፤ ወደደ ፤ የተዋሐደ ፤ ሰው ፡ የኾነ ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ መሠ ለድን ፡ የወደደ ፤ ሥጋ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ባላ ለም ፡ ነበር ፤ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ሥጋ ለትስብእት ፡ በሚገባው ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ እንጂ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፬ ። ም ፡ ፻፭፭ ።

፴፰፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ልህቀትሰ ፡ ነቢር ፡ እም ጥበብ ፡ በከመ ፡ ለሊሁ ፡ ጥበብ ፡ ውእቱ ፡ ወለሊሁ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ በእንቲአነ ፡ ዘእንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወይ ደሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ልህቀተ ፡ እስመ ፡ ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ዘሎቱ ፡ ዘልማዱ ፡ ልህቀት ፡ ውእቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደሰ ፡ እምድንግል ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ሥጋሰ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ወዳእሙ ፡ ረሰዮ ፡ ቃል ፡ ዘኢፍጡር ፡ ፭ደ ፡ ምስሌሁ በ፭ዱ ፡ አካል ፡ ወ፭ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወ፭ዱ ፡ ገጽ ፡ ወአ ልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘቦቱ ፡ ልብ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ዘከልኤ ፡ ልቡ ፡ ይብል ፡ እንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌ ያት ፡ ወ፪ቱ ፡ አካላት ፡ ወዝንቱሰ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ፡ ተፀንሰ ፡ እምሥጋሃ ፡ ወእምአባላ ፡ ለድንግል ፡ ቅድስት ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዝንቱ ፡ ዘገብሮ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ወሶሎሙ ፡ ኄራን ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ።

፴፱፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ መቅደስ ፡ እስመ ፡ መንፈስ ቅዱስ ፡ ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ መቅደስ ፡ እምድንግል ፤ ወለሊሁ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ ሎቱ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋሂ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስሂ ፡ ወይደሉ ፡ በእንቲአሁ፡ልደት፡ ወተፈጥሮ ፡ ወቦቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ፭ደ ፡ እምነ ፡ ፍጡራን ፡ ወው እቱሰ ፡ ይትሌዐል ፡ እምኵሉ ፡ ፍጥረት ።

፵፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘፈጠሮ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እስመ፡ ቃል ፡ አምላክ ፡ ኮነ ፡ ታኅተ ፡ ሕግ ፡ በከመ ፡ ሥር ዓተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወተአዘዘ ፡ ለሕግ ፡ ዘሙሴ ፡ በዘዚአሁ ፡ ጾታ ፡ ብዙኅ ፡ ጊዜያተ ፡ ወተዐ ገሠ ፡ ለተገዝሮ ፡ ሥጋ ፡ ወውሂበ ፡ ጸባሕት ፡ ወነ በረ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ወይትመየጥ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ሰብእ ፤ ወይገንዩ ፡ ለሕገ ፡ አሪት ።

፵፩፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ወሶላ ፡ ብእሲት ፡ ዘትትዌከፍ፡ዘርዐ ወትወልድ ፡ ተባዕተ ፡ ትከውን ፡ ርኩሰተ ፡ ወባሕቱ እስመ ፡ ልደቱሰ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ኮነ ፡ እመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእግርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድን ግል ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ወበአምላል ፡ ዘኢይት ነገር ፡ ባቲ ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ውእቱሰ ፡ ኮነ ፡ ምእ መን ፡ በነበ ፡ ዘፈነዎ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፭፭ ።

፩፤ ይትዐቀቡ ፡ ምእመናን ፡ እምኵሉ ፡ ርስሐት ፡ ወያ እምሩ ፡ እስመ ፡ ሀለዎሙ ፡ ያውሥኡ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡ በእንተ ፡ ዘሰምዑ ፡ ወኢዐቀቡ ፡ ወእዘዘነ ፡ ከመ ፡ ንፈኑ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም፡ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ ለለ፭ዱ ፡ ፭ዱ ፡ እምኔነ ፡ በከመ ፡ አግሀደ ፡ ለነ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እምነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወንዘክር ፡ ቃሎ ፡ ከመ ፡ ነአዝዝ ከሙ ፡ ቦቱ ፡ ተዝካረ ፡ ወትምህርተ ፡ አበው ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፬ ። ም ፡ ፻፭፭ ።

፴፰፤ ዳግመኛም ፤ እንዲህ ፡ አለ ፤ እሱ ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ በየጥቂቱ ፡ ማደግ ፤ ከጥበብ ፡ የተ ለየ ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ያለ ፡ መለወጥ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰው፡ ኾነ፤ ሰው ፡ ስለኾነም ፡ በየጥቂቱ ፡ ማደግን ፡ ገንዘብ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ፤ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነውና የተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ በየጥቂቱ ፡ ማደግ ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ፤ ዳግመኛም ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋን ፡ ከድንግል ፡ ፈጠረለት ፡ አለ ፤ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ሥጋስ ፡ ለባዊት ፤ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፡ ፍጡር ፡ ነው ፤ ያልተፈጠረ ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ አካል፤ አንድ ፡ ባሕርይ ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ በመኾን ፡ ከእሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አደረገው ፡ እንጂ ፤ ዕውቀት ፡ ያለው ልቡ ፡ ሁለት ፡ ያልኾነ ፡ ማንም ፡ ማን ፡ ስለ ፡ እሱ፡ ሁለት ፡ አካል ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ አይ ልም ፤ ይህ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከሥጋዋ ፡ ሥጋ ፤ ከነ ፍሷ፡ ነፍስ ፡ ነሥቶ ፡ ተፀነሰ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ መኾን፡ ለፍጥረቱ ፡ ያደረገው ፡ ነው ፤ ምእመናንም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ያምናሉ ።

፴፱፤ ዳግመኛም ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከድንግል ፡ ሥጋን እንደ ፡ ፈጠረለት ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ተናገረ ፤ ነገር ፡ ግን፤ ሥጋም ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ገንዘቡ ፡ እንደኾነ ፡ እሱ ፡ ያውቃል ፤ ተወለደ ፤ ተፈጠረ ፡ መባል ፡ ይገ ባዋል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ምንም ፡ ከፍጡራን ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ቢኾን ፤ እሱስ ፡ ከፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ነው ።

፵፤ ዳግመኛም ፤ እግዚአብሔር ፡ አስታራቂ ፡ እንዲኾን፡ ሰው ፡ ያደረገው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፤ ለሰው የሚገባ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሕግን ፡ ፈጸመ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሚኾን ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ለሙሴ ፡ ሕግ ፡ ታዘዘ ፤ በሥጋ ፡ ለመገዘር ፤ ግብር ፡ ለመክፈል ፡ ፈቃደኛ ፡ ኾነ ፤ የአሪትን ፡ ሕግ ፡ ለመ ፈጸም ፡ ለበዓል ፡ ከሚወጡ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሲወጣ፡ ሲወርድ ፡ ኖረ ።

፵፩፤ በዘር ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የምትወልድ ፡ ሴት ፡ ሁሳ ትከለክል ፡ ነበር ፤ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ መወለዱ ፡ ግን ፤ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡ በማይመረመር ፡ ግብር ፤ በማይነገር ምሥጢር ፡ ኾነ ፡ አለ ፤ ዳግመኛም ፤ እሱስ ፡ ወደዚህ ዓለም ፡ በላከው ፡ በአብ ፡ ዘንድ ፡ የታመነ፡ ኾነ፡ አለ።

ምዕራፍ ፡ ፻፭፭ ።

፩፤ ምእመናን ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ይራቁ ፤ ሰምተው፡ ባለመጠበቃቸው ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ መልስ ፡ መስ ጠት ፡ እንዳለባቸው ፡ ይወቁ ፤ ይህን ፡ ቃል ፡ ጽፈን በዐራቱ ፡ ማዕዘን፡እንድንሰድ ፡ አዘዘን ፤ ክብር ፡ ይግ ባውና ፡ ጌታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ፈቃድ፤ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መምህርነት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ገለጠልን ፡ ከእኛ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሁሉም ፡ ጸንተን ልንኖር ፡ ይገባናል ፤ በእሱ ፡ የምታስቡበት ፡ የአበ ውን ፡ ትምህርት ፡ እናስተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ የጌ ታችንን ፡ ቃል ፡ ልናስብ ፡ ይገባናል ።

ስምዓት ። ም ፡ ፪ፀ፭ ።

፪፤ ይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ አ ፡ አኀውየ ፡ ንሕነ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ንትሐተት ፡ በእንተ ፡ ሙሉ ፡ ዘተውህበነ ፡ ወኢንንሣእ ፡ ገጸ ፡ ወኢመነኒ ፡ ዘህሎ ፡ ኀቤነ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ለፀዲ ፡ ዘህሎ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘይብል ፡ ዘኢመፍትው ፡ ይዝልፎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ።

፫፤ ወግብሩ ፡ ለዮሐንስ ፡ ይትናገር ፡ ቅድመ ፡ ይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ እስመ ፡ ፪ቲ ፡ መካናት ፡ ሀለዋ ፡ አሐቲ ፡ ለሕይወት ፡ ወአሐቲ ፡ ለሞት ፡ ውስተ ፡ ፪ቲ ፡ መካናት ፡ ፍልጠት ፡ ወመካነ ፡ ሕይወት ፡ ዘውእቱ ፡ ከመ ፡ ታፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ዘፈጠረከ ፡ በሙሉ ፡ ልብከ ፡ ወትሰብሖ ፡ ዘውእቱ ፡ አድኀነከ ፡ እሞት ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሚት ፡ ትእዛዝ ፡ ወካልእታሂ ፡ ትእዛዝ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ከመ ፡ ታፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ፡ በዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ወነቢያት ፡ ስቁላን ፡ ቦቱ ።

፬፤ ይቤ ፡ ማቴዎስ ፡ ሙሎ ፡ ዘኢትፈቅድ ፡ ይርከብከ ፡ ወአንተሂ ፡ ኢትግበር ፡ ለካልእከ ፡ ዝውእቱ ፡ ከመ ፡ ሙሎ ፡ ዘትጸልእ ፡ በርእስከ ፡ ኢትግበር ። ለባዕድ ፡ ወአንተ ፡ አ እጉየ ፡ ጴጥሮስ ፡ መሀሮሙ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢትቅትል ፡ ወኢትዘሙ ፡ ወኢታማስን ፡ ሕፃነ ፡ ንኡሰ ፡ ኢትስርቅ ፡ ወኢትኩን ፡ ማእምረ ፡ ወኢረዓዬ ፡ ኮከብ ፡ ወኢትኩን ፡ መሠርየ ፡ ወኢትቅትል ፡ ፃእፃእ ፡ ንኡሰ ፡ በውስተ ፡ ከርሠ ፡ እሙ ፡ ኢእምድኅረ ፡ ተወልደ ፡ ኢትቅትሎ ።

፭፤ ወኢትፍቱ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ንዋየ ፡ ካልእከ ፡ ወኢትጽላዕ ፡ መነሂ ፡ እምሰብእ ፡ ወኢትኩን ፡ ስምዐ በሐሰት ፡ ወኢትንብብ ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ መኑሂ ፡ ወኢተሐሊ ፡ ከመ ፡ ትግበር ፡ እኩየ ፡ ወኢትኩን ፡ ዘፀኤ ፡ ልቡ ፡ ወኢዘፀ ፡ ልሳኑ ፡ እስመ ፡ ዘፀኤ ፡ ልሳኑ መሥገርት ፡ ውእቱ ፡ ለሞት ፡ ወኢይኩን ፡ ነገርከ ፡ ከንቶ ፡ ወኢትኩን ፡ ሐሳዌ ፡ ወኢትኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ንዋይ ፡ ብዙኅ ፡ ወኢትኩን ፡ ተዐጋሌ ፡ ወኢመ ድለዌ ፡ ወኢዘእኩይ ፡ ልቡ ፡ ወኢዕቡየ ፡ ወኢትምክር ፡ ምክረ ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ ቢጸከ ፡ ኢትጽዐል ፡ መነሂ ፡ እምሰብእ ፡ አላ ፡ ገሥጾ ፡ ወለባዕዳንሂ ፡ ጸሊ ፡ ወትሜህሮሙ ፡ ወአፍቅሮሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምነፍስከ ።

፮፤ ይቤ ፡ እንድርያስ ፡ አ ወልድየ ፡ ጕየይ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፡ ወጽላዕ ፡ ሙሎ ፡ እኩየ ፡ ወኢትኩን ፡ መዓትመ ፡ እስመ ፡ መዓት ፡ ይስሕብ ፡ ኀበ ፡ ቀትል ፡ እስመ ፡ መዓት ፡ ጋኔን ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ፡ ወኢትኩን ፡ ቀናኤ ፡ ወኢቁጡዐ ፡ ቀትል ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ያማስን ፡ ወያወርስ ፡ እከየ ።

ስምዓት ። ም ፡ ፪ፀ፭ ።

፪፤ ዮሐንስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ወንድሞቼ ፤ ስለ ፡ ተሰጠን ሀብት ፡ እንድንጠየቅ ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ፤ ከእኛ ዘንድ ፡ ያለ ፡ የማንንም ፡ ፌት ፡ አይተን ፡ አናድላ ለአንድ ፡ ሰው ፤ የማይገባውን ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ በአጠገቡ ፡ ያለ ፡ ቢኾን ፤ መልካም ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ይገሥጸው ።

፫፤ የዮሐንስ ፡ ልማዱ ፡ በፊት ፡ ይናገራል ፤ ዮሐንስ ፡ ሁለት ፡ ቦታዎች ፡ አሉ ፡ አንዲቱ ፡ ለሞት ፤ አንዲቱ ለሕይወት ፡ ናት ፤ በሁለቱ ፡ ቦታዎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አለ ፤ የሕይወት ፡ ቦታስ ፡ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍጹም ፡ ልቡናህ ፡ መውደድ ፤ ማመስገን ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ከሞት ፡ ያዳነህ ፡ ነው ፤ መጀመሪያዪቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ሁለተኛዪቱም ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ወንድምህን ፡ እንደራስህ ፡ አድርገህ ፡ መውደድ ፤ በዚህ ፡ ሕገ ፡ አሪት ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ጸንተውበት ፡ ይኖራሉ ፡ አለ ።

፬፤ ማቴዎስ ፤ በአንተ ፡ ሊደረግብህ ፡ የማትወደውን ፡ ሁሉ ፤ አንተም ፡ በወንድምህ ፡ አታድርግ ፤ ይኸውም ፡ የምትጠላውን ፡ ሁሉ ፡ በሌላው ፡ አታድርግ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ወንድሜ ፡ ጴጥሮስ ! አንተም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አስተምራቸው ፡ አለ ፡ ጴጥሮስ ! አትግደል ፤ አትስሰን ፤ ታናሹን ፡ ሕፃን ፡ ሠርተህ ፡ ቀጥተህ ፡ አሳድግ ፤ አትስረቅ ፤ ዐውቃለሁ - ባይ ፤ ኮከብ ፡ ቆጣሪ ፡ አትኹን ፤ ሥር - ማሽ ፡ ቅጠል ፡ በጣሽ ፡ አትኹን ፤ ያልጸናውን ፡ ሕፃን ፡ (ፅንስ) ፡ በእናቱ ፡ ማሕፀን ፡ እንዲሞት ፡ አታድርግ ፤ ከተወለደም ፡ በኋላ ፡ አትግደለው ።

፭፤ የባልንጀራህ ፡ የኾነውን ፡ በምንም ፡ በምን ፡ አትመኝ ፤ ከሰውም ፡ ወገን ፡ ማንንም ፡ አትጥላ ፡ በሐሰት ፡ አትመስክር ፤ በማንም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አትናገር ፤ ክፉ ፡ ልሥራ ፡ አትበል ፤ ሁለት ፡ ልብ ፡ ሁለት ፡ አፍ ፡ አትኹን ፤ ሁለት ፡ የሚናገር ፡ የሞት ወጥመድ ፡ ነውና ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ አትናገር ፤ ሐሰተኛ ፡ አትኹን ፤ ገንዘብ ፡ ወዳድ ፡ አትኹን ፤ ቀማኛ አትኹን ፤ አድላዊ ፡ አትኹን ፡ ተጠራጣሪ ፤ ትዕቢተኛ ፤ አትኹን ፤ በባልንጀራህ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ አትምከር ፤ ከሰው ፡ ማነንም - ማነን ፡ አትስደብ ፡ ምክር ፤ አስተምር ፡ እንጂ ፤ ለሌሎች ፡ ጸልይላቸው ፤ አስተምራቸው ፡ ከራስህም ፡ ይልቅ ፡ ውደዳቸው ፡ አለ ።

፮፤ ልጄ ! ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተለይ ፤ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አትውደድ ፤ ቁጡ ፡ አትኹን ፤ ቁጣ ፡ ወደ መግደል ፡ ያደርሳልና ፤ ቁጣ ፡ ክፉ ፡ ጋኔን ፡ ነውና ቀናተኛ ፤ ጎሮ ፡ (አምባ - ጓሮ) ወዳጅ ፡ አትኹን፤ ይህ ፡ ይገዳል ፤ ፍዳንም ፡ ያመጣብናል ፡ አለ ፡ እንድርያስ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፪፭፩ ።

፯፤ ይቤ ፡ ፊልጶስ ፡ አ ወልድየ ፡ ኢትኩን ፡ ፈታዌ ፡ እስመ ፡ ፍትወት ፡ ትስሕብ ፡ ውስተ ፡ ዝሙት ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ትሬስዮ ፡ ለብእሲ ፡ ሠሐቀ ፡ ወሥላቀ ፡ ለሆሉ ፡ እስመ ፡ ፍትወት ፡ ጋኔን ፡ ይእቲ ፡ መስሕት ፡ እስመ ፡ ሶበ ፡ የኀብር ፡ ጋኔነ ፡ መዓት ፡ ምስለ ፡ ጋኔነ ፡ ፍትወት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሐጉል ፡ ለዘይገብሮ ፡ ወህበ ፡ ሀሎ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ ኃጢአት ፡ ውእቱ ፡ ለነፍስ ፡ ለእመ ፡ ረከበ ፡ ኀበ ፡ ይበውኢ ፡ ንስቲተ ፡ እስመ ፡ ያርሕቦ ፡ ለውእቱ ፡ መካን ፡ ወያነሥእ ፡ ምስሌሁ ፡ ሰቡዐ ፡ መናፍስተ ፡ ርኩሳነ ፡ ወያበውእ ፡ ላዕለ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ ወኢ የኀድጎ ፡ ለብእሲ ፡ ይትለዐል ፡ ግመራ ፡ ከመ ፡ ይር አይ ፡ ጽድቀ ፡ ለጎዲገ ፡ መዓትክሙኒ ፡ ቡቱ ፡ ዐቅም ፤ ከመ ፡ ታቁርሩ ፡ ወታስተድኅሩ ፡ መዓተ ክሙ ፡ ከመ ፡ ኢያውድቅሙ ፡ ውስተ ፡ ገቢረ ፡ እኩይ ፡ ወፈድፋደ ፡ መዓት ፡ ወፍትወት ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ፡ ሶበ ፡ ይነብሩ ፡ ጉንዱየ ፡ መዋዕለ ፡ ዘእን በለ ፡ ይቁርር ፡ መዓቶሙ ፡ ይከውኑ ፡ አጋንንተ ፡ ሶበ ፡ ይቀንይሙ ፡ ለሰብእ ፡ አጋንንት ፡ ፡ ያውዕዩ፡ ነፍሶሙ ፡ ወሶበ ፡ ያበጽሕዎ ፡ ለገቢረ ፡ ዓመፃ ፡ ይሣለቅዎ ፡ ወይትፌሥሑ ፡ በሐጕለ ፡ ነፍሱ ።

፰፤ ይቤ ፡ ስምዖን ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ኢትኩን ፡ ነባቤ ፡ እኩይ ፡ ወኢልዑለ ፡ ዓይን ፡ እስመ፡በዝንቱ ፡ ይከውን ፡ ዝሙት ።

፱፤ ይቤ ፡ ያዕቆብ፡ አ ወልድየ ፡ ኢትኩን ፡ ዘትብል ፡ በትእምርታት ፡ ወኢተጠያሬ ፡ በያፍ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ይመርሕ ፡ ኀበ ፡ አምልኮ ፡ ጣያት ፡ ወኢመዓንስበ ፡ ወኢረቃዬ ፡ ወኢእምሰብእ ፡ ወጎራዬ ፡ ሰዓታት ፡ ወኢጎራዬ ፡ ዕለታት ፡ ወኢረዓዬ ኮከብ ፡ ወኢመሠርየ ፡ ወኢእምነ ፡ ሰብእ ፡ ፋላት ፡ ወኢትፍቱ ፡ ከመ ፡ ታእምሮሙ ፡ እስመ ፡ በዝንቱ ፡ ይከውን ፡ አምልኮ ፡ ጣያት ።

፲፤ ይቤ ፡ ናትናኤል ፡ አ ወልድየ ፡ ኢትኩን ፡ ሐሳዌ ፡ እስመ ፡ ሐሰት ፡ ይወስድ ፡ ኀበ ፡ ስርቅ ፡ ወኢተኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ወርቅ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ተወድሶ ፡ በከንቱ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ይከውን ፡ ዘይስሕብ ፡ ኀበ ፡ ሰረቅ ።

፲፩፤ ይቤ ፡ ይሁዳ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ኢትኩን ፡ መንኰራኵረ እስመ ፡ ነኰርጓር ፡ ይስሕቦ ፡ ለሰብእ ፡ ኀበ ፡ ፅርፈት ፡ ወኢትኩን ፡ ጎያለ ፡ ወኢሐሳዬ ፡ እኩይ ፡ እስመ ፡ በዝንቱ ፡ ይከውን ፡ ክሕደት ፡ ኩን ፡ የዋህ እስመ ፡ የዋሃን ፡ ይወርሱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ኩን ፡ መስተሣህለ ፡ ወመሐሬ ፡ ሰላማዌ ፡ በንጹሕ፡ ልብ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ኩን ፡ ትሑተ ፡ ውኄረ ፡ ወተወቅብ ፡ በረዓድ ፡ እም ቃል ፡ ዘሰማዕኩ ፡ ኢትትዐበይ ፡ ወኢትረሲ ፡ ነፍሰከ ፡ ምስለ ፡ ዕቡያን ፡ አላ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ትሑታን ፡ ወጸድቃን ፡ ወሶሎ ፡ ዘይረክበከ ፡ ተወከፍ ፡ በአኰቴት ፡ ወአእምር ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይከውን ፡ ወኢምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፪፭፪ ።

፯፤ ልጂ ፡ ስስታም ፡ አትኩን ፤ ስስት ፡ ወደ ፡ ዝሙት ታደርሳለችና ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰውን ፤ መሳቂያ፡ መሣለቂያ ፡ ታደርጋዋለች ፤ ስስት ፡ የምታስት ፡ ጋኔን ፡ ናትና ፡ የሚያስቆጣ ፡ ጌኔን ፡ ከሚያሳሳ ፡ ጋኔን ጋር ፡ ሲተባበር ፡ እሱ ፡ ለሚያስቆጣ ፤ ለሚያሳሳ ፡ ጉዳት ፡ ነውና ፡ ቢስ ፡ ጋኔን ፡ ከአደረ ፡ ዘንድ ፡ ነፍስን ፡ ይጎዳታል ፤ የሚያድርበት ፤ የሚገባበት ፡ ጥቂት ፡ ምክንያት ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ እሱ ፡ ያስፋፋዋልና ፡ ርኩሳን ፡ አጋንንትንም ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ መጥቶ በዚያች ፡ ነፍስ ፡ ያድርባታልና ፡ እውነቱን ፡ ነገር ፡ ለማየት፡ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ አይተወውም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ መሥራት ፡ እንዳያደርሳችሁ ፡ ቁጣችሁን ፡ ለማብረድ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ቁጣችሁ ፡ መጠን ፡ ይኑረው ፤ ቁጣ ፤ ስስት ፡ እጅግ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ሳይታረቁ ፤ ቢውሉ ፤ ቢያድሩ ፡ እንደ፡ አጋንንት ፡ ይኾናሉ ፤ አጋንንት ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ በአደሩ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያበሳጫዋቸዋል ፤ ያናድዱዋቸዋል ፤ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ መሥራት ፡ በአደረሱት ፡ ጊዜ ፡ ይዘብቱበታል ፤ በነፍስ ፡ በመጐዳቱም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ አለ ፡ ፊልጶስ ።

፰፤ ልጂ ! ክፉ ፤ ተናጋሪ ፤ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ የምታይ ፡ አትኹን ፤ በዚህ ፡ ዝሙት ፡ ይመጣልና ፡ አለ ፡ ስምዖን ።

፱፤ ልጂ ፤ በምልክት ፡ የምትመራ ፤ በወፍ ፡ የምታመርት ፡ አትኹን፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጣያት ፡ ወደ ፡ ማምለክ ያደርሳልና ፡ ጋኔን ፡ ሳቢ ፤ የምትረጭ ፤ ሰዓት ፡ ከሚመርጡ ፤ ቀን ፡ ከሚያሻሽሉ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፤ ወይም ኮከብ ፡ ቆጣሪ - ሥር ፡ ማሽ ፤ ቅጠል ፡ በጣሽ ፤ ሚርተኛ ፡ አትኹን ፤ እነዚህን ፡ መማር ፡ አትሻ ፤ በዚህ ጣያት ፡ ማምለክ ፡ ይመጣልና ፡ አለ ፡ ያዕቆብ ።

፲፤ ልጂ ! ሐሰተኛ ፡ አትኹን ፤ ሐሰት ፡ ከስርቆት ፡ ያደርሳልና ፡ ወርቅ ፤ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ የምትወድ ፡ አትኹን ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከስርቆት ፡ ያደርሳልና ፡ አለ፡ ናትናኤል ።

፲፩፤ ልጂ ! አጕረምራሚ ፡ አትኹን ፤ ማጕረምረም፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ስድብ ፡ ያደርሰዋልና ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የምታስብ ፤ ተጋፊ ፡ አትኹን ፤ ክሕደት ፡ በዚህ ፡ ይመጣልና፡ ኃዳጌ- በቀል ፡ (ይቅር - ባይ) ኹን ፤ ቂም - በቀል የሌላቸው፡ ሰዎች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሳሉና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፤ ርኅሩኅ ፤ ኃጢአት ፡ በሌለበት በንጹሕ ፡ ልብ ፡ ሁሉን ፡ የምትወድ ፡ ኹን ፤ ትሑት ቸር ፡ ኹን ፤ ከሰማኸው ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ በመፍራት ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ተጠብቀህ ፡ ኑር ፤ አትታበይ ፤ ሰውነትህን ፡ ከትዕቢተኞች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አታድርግ፤ ከትሑታን ፤ ከደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ያገኘህን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ አመስግነህ ፡ ተቀበል ፤ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚ ደረግ ፡ እንደሌለ ፡ ዕወቅ ፡ አለ ፡ ይሁዳ ፤ (ታዴዎስ)።

ስምዓት ፡ ም ፡ ደ፩ኛ ።

፲፪፤ ይቤ ፡ ቶማስ ፡ አ ወልድየ ፡ ለዘይነግረከ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘኮነ ፡ ለከ ፡ ምክንያተ ፡ ሕይ ወት ፡ ወወሀበከ ፡ ሕልቀተ ፡ ክብር ፡ አፍቅሮ ፡ ከመ ብንተ ፡ ዓይንከ ፡ ወተዘከሮ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ፡ ወአክብሮ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ይዘክሩ ፡ መለኮተ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀሎ ፡ ህየ ፡ ሐውፅ ፡ ሙሉ ፡ አሚረ ፡ እለ፡ተርፉ፡ቅዱሳን ፡ ከመ ፡ ታዕርፍ፡ኀቤ፡ ቅዱሳን ፡ ይከውን፡ቅዱሰ።

፲፫፤ ወአክብሮ ፡ በአምጣነ ፡ ጎይልከ ፡ ወእምነ ፡ ጸማከ፡ ወግብረ ፡ እደዊከ ፡ ሀቦ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረሰየከ፡ድልወ ፡ ትርከብ ፡ በኀቤሁ ፡ ሲሳየ ፡ መን ፈሳዊተ ፡ ወሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡ ወይደልወከ ፡ ፈድፋደ ፡ ከመ ፡ ተሀቦ ፡ ሲሳየ ፡ ኀላፌ ፡ ዘዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ለዘይትቀነይ ፡ ይደልዎ ፡ ወስቡ ፡ ኢትፍዕሞ ለብዕራይ ፡ በኀበ ፡ ምክያድ ፡ መኑ፡ዘይተክል፡ወይነ ፡ ወኢይበልዕ ፡ ፍሬሁ ።

፲፬፤ ይቤ ፡ ኬፋስ ፡ ኢትግበር ፡ ፍልጠተ ፡ አላ ፡ አስተ ወርቅ ፡ ለእለ ፡ ተበዐሱ ፡ በሰላም ፡ ወፍታሕ ፡ በር ትዕ ፡ ኢትንግእ ፡ በገጸ ፡ ባዕል ፡ ላዕለ ፡ ኀጡአ ፡ እስመ ፡ ብዕል ፡ ኢይጸንእ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢታክብር ፡ ዕቡየ ፡ ወኢትሰአል ፡ ሎቱ ፡ መጽ ሐፈ ፡ አላ ፡ በኀቤሁ ፡ ዕሩየ ፡ ግበር ፡ ሎቱ ፡ ወኢት ኩን ፡ ናፋቂ ፡ እንዘ ፡ ትጼሊ ፡ ወሐሊ ፡ ዘተመነይክ፡ ወይፈጽም ፡ ለከ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፭፤ ወኢትኩን ፡ ዘትሔሊ ፡ እኩየ ፡ ሶበ ፡ ትስፍሕ ፡ እዴከ ፡ ወሶበ ፡ ትፈጽም ፡ ታገብእ ፡ ኀቤከ ፡ ለእመ፡ ብከ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ምንተኒ ፡ ዘወሀበከ ፡ ወተ ኀሥሥ ፡ መድኀኒተከ ፡ እምኀጢአትከ ፡ ወኢት ኩን ፡ ዘፀእኤ ፡ ልቡ ፡ ሶበ ፡ ትሁብ ፡ ዘትረክብ ፡ ወአእ ምር ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘየዐሥየከ ፡ ወኢታስተኀ ፍሮ ፡ ለዘሰአለከ ፡ አላ ፡ ተካፈል ፡ ምስለ ፡ ጽኑሳን፡ በሎሱ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ወኢትበል ፡ ሊተ ፡ ለባሕ ቲትየ ፡ ንዋይየ ፡ ለእመ ፡ ኮንከሙ ፡ ሱቱፋን ፡ በበ ይናቲከሙ ፡ በዘይማስን ፡ እፎኬ ፡ በዘኢይማስን ።

፲፮፤ ይቤ ፡ በርተሎሜዎስ ፡ አስተበቍዐከሙ፡ አኀውየ ፡ እንዘ ፡ ብክሙ ፡ መዋዕል ፤ ወእንትሙ ፡ ትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ምስሌሁ ፡ ወኢታስትቱ ፡ ውሂበ፡ እምዘ ፡ ብክሙ ፡ ዘትሁቡ ፡ እስመ ፡ ዕለተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ቅሩብ ፡ ወየኀልፍ ፡ ሙሉ ፡ ዘያስተርኢ ወዘኀቡዕ ፡ ወይመጽእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዕሤቱ፡ ምስሌሁ ፡ ኩኑ ፡ ገባርያነ ፡ ሕግ ፡ ለርእስከሙ ፡ ወኩኑ ፡ መምህራነ ፡ ለካልዓኒክሙ ፡ ከመ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ መሀረክሙ ፡ ዕቀቡ ፡ ዘተመሀርክሙ ወኢትወስኩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢታንትጉ ፡ እምኔሁ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ አ አኀው ፡ መጻሕፍት ፡ ይሜህራ ክሙ ፡ በእንተ ፡ ዘተርፈ ፡ ትእዛዝ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ደ፩ኛ ።

፲፪፤ ልጄ ! ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚነግርህን ፤ የሕይ ወት ፡ ምክንያት ፡ የኾነህን ፤ ለልጅነት ፡ ያበቃህ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ብሌን ፡ ውደደው ፤ በመዐል ትም ፡ በሌሊትም ፡ አስበው ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ አከበረው ፡ አክብረው ፤ እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ ከሚጠሩበት ፡ ቦታ ፡ ከዚያ ፡ ይኖራልና ፤ በትምህር ታቸው ፡ ትጽናና ፡ ዘንድ ፡ እየሔድክ ፡ ሌሎች ፡ ቅዱሳንን ፡ ጠይቅ ፤ ከቅዱሳን ፡ ጋር ፡ የሚውል ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናልና ።

፲፫፤ በሚቻል ፡ መጠን ፡ አክብረው ፡ ከደከምክበት ፡ ከሥራህ ፡ ፍሬ ፡ ስጠው ፤ እግዚአብሔር ፡ በእርሱ ምክንያት ፡ መንፈሳዊ ፡ ምግብን ፤ የዘለዓለም፡ሕይ ወትንም ፡ እንድታገኝ ፡ አድርጎኻልና ፤ የሚያልፈ ውን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ምግብ ፡ ልትሰጠው ፡ ይገ ባሃል ፤ ለሠራተኛ ፡ ዋጋው ፡ ይገባዋልና፤በዐውድማ የበሬውን ፡ አፉን ፡ አትሰረው ፤ ወይን ፡ ተክሎ፡ ፍሬውን ፡ የማይበላ ፡ ማነው ? አለ ፡ ቶማስ ።

፲፬፤ የተጣሉትን ፡ በፍቅር ፡ አንድ ፡ አድርግ ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ የሚለያይ ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ፤ በውነት ፡ ፍረድ ፤ ለባለጸጋ ፡ አድልተህ ፤በድኻው፡ አትፍረድ፡ ብዕል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቁም - ነገሩ ፡ አይደለምና ትዕቢተኛውን ፡ (መናፍቁን) ፡ አታክብረው ፤መጽሐ ፍም ፡ አትጥቀስለት ፤ እንደ ፡ አነጋገሩ ፡ መልስለት፡ እንጂ ፤ ስትጸልይ ፡ አትጠራጠር ፤ የምትለምነውን፡ አስተውል ፤ እግዚአብሔር ፡ ይፈጽምልኻል ።

፲፯፤ በምትመጸውትበት ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አታስብ፤ ከሰጠህ ፡ ዋጋህን ፡ ታገኛለህና ፡ የሰጠህ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ገንዘብ ፡ በእጅህ ፡ ቢኖርህ ፤ ከኃጢአትህ ፡ መዳንን ፡ ሻ ፡ ፈልግ ፤ ያገኘኸውን ፡ በምትሰጥበት ጊዜ ፡ ወላዋይ ፡ አትኹን ፤ ዋጋህን ፡ የሚሰጥህም፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ዕወቅ ፤ የለመንኸንም ፡ አታሳፍ ረው ፤ ማናቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ከነዳያን ፡ ጋር ፡ ተካ ፈል ፡ እንጂ ፡ ገንዘቤ ፡ የግሌ ፡ ነው ፡ አትበል ፤ በጎ ላፊው ፡ ገንዘብ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ አንድ ፡ ኮኾና ችሁ ፡ በማያልፈው ፡ እንደምን ፡ አንድ ፡ አትኾኑም።

፲፰፤ ወንድሞቼ ! እማልዳችኋለሁ ፤ ዕድሜ ፡ ሳላችሁ፤ ከዚህም ፡ ጋር ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ሲቻላችሁ የአላችሁን ፡ መስጠት ፡ ቸል ፡ አትበሉ ፤ እግዚአብ ሔር ፡ የሚመጣበት ፡ ቀን ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፡ የሚታ የው ፤ የማይታየው ፡ ሁሉ ፡ ያልፋል ፤ እግዚ አብሔር ፡ ይመጣል ፡ የሚሰጠው ፡ ዋጋም ፡ ከእሱ፡ ጋር ፡ ነው ፤ ለራሳችሁ ፡ ፈጸምያነ ፡ ሕግ፡ኹኑ፤ እግዚአብሔር፡እንደ፡አስተማራችሁ፡ሌሎችን፡ አስተ ምሩ፡ የተማራችሁትን፡ ጠብቁ፤ በተማራችሁት፡ላይ አትጨምሩ ፤ ከተማራችሁትም ፡ አታጉድሉ፡ አለ ፡ በርተሎሜዎስ ፤ ወንድሞቼ ! የቀሩትን ፡ ትእዛዛት መጻሕፍት፡ ያስተምሩዋችኋል፡ አለ ፡ ጴጥሮስ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፳፯ ። ክፍል ፡ ፩ ።

፩፤ እመጽሐፈ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ልሳነ ፡ ዕፍረት ፤ ዘንተ ፡ አብል ፡ ወአሰምዕ ፡ በእግዚ እነ ፡ በእንቲአክሙ ፡ ከመ ፡ ኢትሑሩ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በሙስና፡ ልቦሙ ፡ ወጽሉም ፡ ሕሊናሆሙ ፡ ወነኪራን ፡ እምሕይወተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕበዶሙ ፡ ወበ ጽላሌ ፡ ልቦሙ ፡ ቅቡጻን ፡ እለ ፡ መጠው ፡ ርእሶሙ ለሕርትምና ፡ ወለኵሉ ፡ ምግባር ፡ ርኩስ ፡ ወለም ርዓት ።

፪፤ ወአንትሙሰ ፡ አኮ ፡ ከማሁ ፡ ዘተምህርክምዎ፡ ለክርስቶስ ፡ እመሰ ፡ አማነ ፡ ትሰምዕዎ ፡ ወትት ሜህሩ ፡ በኀቤሁ ፡ ጽድቀ ፡ እስመ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዕትቱ ፡ እምኔክሙ ፡ ግዕ ዘክሙ ፡ ዘትካት ፡ አብል ፡ በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ብእሲ ዘይማስን ፡ በፍትወተ ፡ ስሒት ። ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፮ና ፰—፲፫ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፱ ።

፫፤ ሐድሱ ፡ መንፈሰ ፡ ልብክሙ ፡ ወልበስዎ ፡ ለሐዲስ፡ ብእሲ ፡ ዘመጽአ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽ ድቅ ፡ ወበርትዕ ፤ ወበየውሃት ፡ ወበእንተዝ ፡ ግድፍዎ ፡ ለሐሰት ፡ ወተናገሩ ፡ ጽድቀ ፡ ዙልክሙ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ እስመ ፡ አሐዱ ፡ አባል ፡ ንሕነ ፡ ተምዑ ፡ ወኢተአብሱ ፡ ወዘእንበለ ፡ ይዕ ርብ ፡ ፀሐይ ፡ አቁርሩ ፡ መዐተክሙ ። ዘፍ ፡ ፩፡ ፳፮ና ፳፯ ። መዝ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፱—፳ ።

፬፤ ወኢተሀብዎ ፡ ፍኖተ ፡ ለሰይጣን ፡ ዘይሰርቅኒ ፡ ኢይስርቅ ፡ እንከ ፡ ለይትገበር ፡ ወይጸሙ ፡ በእ ደዊሁ ፡ ለሠናይ ፡ በዘይረድኦ ፡ ለጽኑስ ፤ ኵሉ ፡ ነገር ፡ ሕሱም ፡ ኢይጸእ፡ እምአፉክሙ ፡ ዘእንበለ፡ ሠናይ ፡ በዘይትሐነጽ ፡ ትካዝክሙ ፡ ከመ ፡ ይርከቡ ሞገሰ ፡ እለ ፡ ይሰምዑክሙ ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። ቆላ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፭፤ ወኢታምዕዕዎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘቦቱ ፡ ዐተ ቡክሙ ፡ በዕለተ ፡ መድኃኒት ፡ ኵሉ ፡ መሪረ ፡ ወኵሉ ፡ መዐተ ፡ ወኵሉ ፡ ቁጥዓ ፡ ወገዓረ ፡ ወኵሉ፡ ጽርፈተ ፡ አዕትቱ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ እኩይ ። ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፲ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፰ ።

፮፤ ወኩኑ ፡ መሓርያነ ፡ ለቢጾክሙ ፡ ወተጸገው ፡ በበ ይናቲክሙ ፡ ወመሐሩ ፡ ወስረዩ ፡ በከመ ፡ ሰረየ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ። ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፴፫—፴፭ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፯፤ ተመሰሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ውሉደ ፡ ፍቁ ራን ፡ ወሑሩ ፡ በተፋቅሮ ፡ በከመ ፡ አፍቀረክሙ ፡ ክርስቶስ ፡ ወመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአክሙ ፡ መሥ ዋዕተ ፡ ወቁርባነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መዓዛ ፡ ሠናየ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፳፯ ። ክፍል ፡ ፩ ።

፩፤ ነገሩ ፡ የተወደደ ፤ የከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ከጸ ፈው ፡ ይህን ፡ እናገራለሁ ፤ ስለ ፡ እናንተም ፡ በጌታ ችን ፡ አዳኛለሁ ፤ በልባቸው ፡ አሳብ ፡ እንደሚኖሩ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ እንዳትኖሩ ፤ ልባቸውም ፡ የታ ወረ ፡ ነው ፤ በስንፍናቸውና ፡ በልባቸው፡ ድንቁርና ከእግዚአብሔር ፡ ሕይወት ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። ተስፋ ፡ ያጡ ፡ ናቸው ፤ ሰውነታቸውን፡ ለጕስቍልና ለዝሙትና ፡ ለመዳራትም ፡ ሰጥተዋልና ።

፪፤ እናንተ ፡ ግን ፤ ክርስቶስን ፡ የተማራችሁት ፡ እንዲህ አይደለም ፤ በእውነት ፡ ከሰማችሁት ፤ እውነት ፡ የሚ ገኝ ፡ በክርስቶስ ፡ ነውና ፡ እውነትን ፡ በእሱ ፡ ዘንድ ከተማራችሁ ፡ የቀደመ ፡ ሥራችሁን ፡ ከእናንተ ፡ አርቁ ፡ ስሕተትን ፡ በመውደድ ፡ ስለሚለወጥ ፡ አሮጌ ፡ ሰውነት ፡ እናገራለሁ ። ሮሜ ፡ ፮ና ፡ ፯—፲፫ ቆላ ፡ ፫ ፡ ፱ ።

፫፤ የልባችሁን ፡ ዕውቀት ፡ አድሱ ፡ ከእግዚአብሔር፡ ተወልዶ ፡ የመጣውን ፡ ክርስቶስን ፡ በዕውነት ፤ በቅንነት ፤ በየውሃት ፡ ምስሉት ፤ ስለዚህም ፡ ሁላ ችሁ ፡ ሐሰትን፡ትታችሁ ፡ ከባልንጀሮቻችሁ ፡ ጋር እውነትን ፡ ተናገሩ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ ነንና ፡ በተቁ ጣችሁም ፡ ጊዜ ፡ አትበድሉ ፤ ቁጣችሁንም ፡ ፀሐይ ሳይገባ ፡ አብርዱ ።ዘፍ፡ ፩ ፡ ፳፯ና ፡ ፳፯ ። መዝ ፡ ፬ ፡ ፭ ። ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፱—፳ ።

፬፤ ለሰይጣንም ፡ መንገድ ፡ አትስጡት ፤ ሊሰርቅ ፡ የነ በረም ፡ እንግዲህ ፡ አይስረቅ ፤ ድኻውን፡ በሚረዳው ገንዘብ፡ ለበጎ፡ ነገር፡ በእጁ ፡ ሥራ ፡ ይድከም ፡ እንጂ ክፉ ፡ ነገርም ፡ ሁሉ ፡ ከአፋችሁ ፡ አይውጣ ፤ በጎ ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ያዘናችሁበት ፡ ሥራ ፡ በሚፈጸም ፡ ገንዘብ ፤ የሚሰሟችሁ ፡ ሰዎች ፡ ክብርን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። ቆላ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፭፤ በአመናችሁበት ፡ ቀን ፡ እናንተን ፡ ያከበሩበት ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አታሳዝኑት፤ የሚያሳዝነውን፡ ነገር፡ ሁሉ ፡ ብስጭትንና ፡ መራገምን ፤ ጠብንና ፡ ስድብ ንም ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጋር፡ ከእናንተ፡ አርቁ። ኢሳ ፡ ፷፫ ፡ ፲ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፰ ።

፮፤ ለባልንጀሮቻችሁ ፡ የምትራሩ ፡ ኹኑ ፤ እርስ ፡ በርሳ ችሁ ፡ ተረዳዱ ፤ ይቅር ፡ ተባባሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ። ማቴ ፡ ፲፰፡ ፴፫—፴፭ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፯፤ እንደ ፡ ተወደዱ ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምስ ሉት፡በፍቅር፡ኑሩ ፤ ክርስቶስ፡እንደ፡ወደዳችሁ ፤ ራሱ ንም ፡ በጎ ፡ መዓዛነት ፡ ያለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ቍር ባን ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ለእግዚአብሔር፡ እንደ ፡ ሰጠላችሁ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፯ ።

፭፤ ወዝሙትሰ ፡ ወሶሉ ፡ ርሶስ ፡ ወትዕግልት ፡ ኢይሰማዕ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በከመ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ነገረ ፡ ከንቱ ፡ ወነገረ ፡ ሐሰት ፡ ወነገረ ፡ ጎፍረት ፡ ወነገረ ፡ እበድ ፡ ወሥላቅ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ለገቢር ፡ እንበለ ፡ ዳእሙ ፡ አዕዙቶ ፡ ዘንተ ፡ አእምሩ ፡ ወጠይቁ ፡ ከመ ፡ ሶሉ ፡ ዘማዊ ፡ ወርኩስ ፡ ወመስተዓግል ፡ ወዘያጣው ፡ አልቦ ፡ መክፈልት ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ፭ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱—፲፩ ።

፱፤ አልቦ ፡ ዘያስሕተክሙ ፡ በነገር ፡ ከንቱ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ይመጽእ ፡ መዐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ውሉደ ፡ ዐላውያን ፡ ኢትትመሰልዎሙኬ ፡ እስመ ፡ ትካት ፡ ጽልመት ፡ አንትሙ ፡ ወይእዜሰ ፡ ብርሃነ ፡ ክንክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ከመ ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ ሑሩ ፡ እስመ ፡ ፍሬሁ ፡ ለብርሃን ፡ ሶሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ፭ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ሉቃ ፲፮ ፡ ፭ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ።

፲፤ አመክሩ ፡ ዘያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኢትሑሩ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ፍሬ ፡ ምግባር ፡ ወጽልመት ፡ ሶለንታሆሙ ፡ ወዓዲ ፡ ገሥጹዎሙ ፡ እስመ ፡ ዘበጽሚት ፡ ይገብሩ ፡ ሐፍረት ፡ ለነጊር ፡ ወዘሰ ፡ ክሡት ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ፡ ይትዐወቅ ፡ እስመ ፡ ሶሉ ፡ ዘገሃድ ፡ ብርሃን ፡ ውእቱ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፳፬—፳፭ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳—፳፪ ።

፲፩፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ ንቃህ ፡ ዘትነውም ፡ ወተንሥእ ፡ እሙታን ፡ ወያበርህ ፡ ለከ ፡ ክርስቶስ ፡ ዑቁ ፡ አኀዊነ ፡ ጥዩቀ ፡ በዓይ ፡ ግዕዝ ፡ ተሐውሩ ፡ ከመ ፡ ጠቢባን ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ አብዳን ፡ እንዘ ፡ ታናሐስይዎ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ እስመ ፡ እኩይ ፡ መዋዕሊሁ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢትኩኑ ፡ አብዳነ ፡ አላ ፡ ሐልዩ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፭ ። ቆላ ፡ ፬ ፡ ፭ ።

፲፪፤ ወኢትስክሩ ፡ ወይን ፡ እስመ ፡ ምርዓት ፡ ውእቱ ፡ ወይከልዕ ፡ ርትዐ ፡ ውእቱ ፡ አላ ፡ ኩኑ ፡ ፍጹማነ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወአንብቡ ፡ መዝሙረ ፡ ወስብሐተ ፡ ወማኅሌተ ፡ ቅድሳት ፡ ሰብሑ ፡ ወዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በልብክሙ ፡ ወአዕዙቱ ፡ ሶሉ ፡ ጊዜ ፡ በእንተ ፡ ሶሉ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዕዙትዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ። በእንቲአሁ ፡ መዝ ፡ ፴፫ ፡ (፴፬) ፡ ፪ና ፡ ፫ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፮

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፯ ።

፭፤ ዝሙትና ፡ ኃጢአት ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ቅሚያም ፡ በእናንተ ፡ አይሰማ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሐሰት ፡ የሚያሳፍር ነገር ፡ የስንፍናም ፡ ነገር ፡ ሊሠሩት ፡ የማይገባ ፡ የቀልድና ፡ የስንፍና ፡ ሥራ ፡ ለቅዱሳን ፡ የማይገባ ቸው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማመስገን ፡ በቀር ፡ ይህንንም ፡ ዕወቁ ፡ ሴሰኛና ፡ ኃጢአተኛ ፡ ቀማኛም ፡ ጣዖትም ፡ የሚያመልክ ፡ ኹሉ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚያወርሳት ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ፭ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱—፲፩ ።

፱፤ በከንቱ ፡ ነገርም ፡ የሚያስታችሁ ፡ አይኑር ፡ በእሱ ፡ ምክንያት ፡ በዐመፀኞች ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍት ፡ የሚመጣበት ፡ ስለኾነ ፡ እንግዲህ ፡ አትምሰሏቸው ፡ ቀድሞ ፡ ዐላዋቆች ፡ ነበራችሁና ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ በጌታችን ፡ ዐዋቆች ፡ ኾናችኋል ፡ እንግዲህስ ፡ ዕውቀት ፡ እንዳላቸው ፡ ልጆች ፡ ኑሩ ፡ የዕውቀት ፡ ፍሬው ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ኹሉ ፡ እውነትና ፡ ቅንነት ፡ ነውና ። ፭ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፭ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ።

፲፤ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ነገር ፡ መርምሩ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ከሌላቸው ፡ ሥራቸውም ፡ ኹሉ ጨለማ ፡ ከኾነ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አትኹኑ ፡ ገሥጿቸው ፡ እንጂ ፡ በስውር ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ለመናገር ፡ የሚያሳፍር ፡ ነውና ፡ የተገለጠ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ በዕውቀት ፡ የሚሠራ ፡ እንደኾነ ፡ ይታወቃል ፡ ተገልጦ ፡ የሚሠራ ፡ ሁሉ ፡ የዕውቀት ፡ ሥራ ፡ ነውና ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፳፪— ፳፭ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፳—፳፪ ።

፲፩፤ የተኛህ ፡ ንቃ ፡ ከሙታንም ፡ ተነሣ ፡ ክርስቶስ ፡ ያበራልሃል ፡ ብሏልና ፡ ወንድሞቻችን ፡ እንደ ፡ ዐላዋቆች ፡ ያይደለ ፡ እንደ ፡ ዐዋቆች ፡ በምን ፡ ግብር ፡ እንታችሁ ፡ እንድትኖሩ ፡ ዕወቁ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ እየናቃችሁት ፡ ዘመኑ ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ዐላዋቆች ፡ አትኹኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ነገር ፡ አስቡ ፡ እንጂ ። ኢሳ ፡ ፳ ፡ ፩ ፡ ቆላ ፡ ፬ ፡ ፭ ።

፲፪፤ ወይን ፡ በመጠጣት ፡ አትስከሩ ፡ ዝሙት ፡ ነውና ፡ የቀናውንም ፡ ነገር ፡ ይከለክላልና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹማን ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ መዝሙርን ፡ አንቡ ፡ የሙሴንም ፡ ምስጋና ፡ የተለየ ፡ የሰሎሞን ፡ መኃልይን ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ድገሙ ፡ በልባችሁም ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ ስለ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ አመስግኑ ፡ መዝ ፡ ፴፫ ፡ (፴፬) ፡ ፪ና ፡ ፫ ፡ ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፭ ።

፲፫፤ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ለባልንጀሮቻችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ አዋርዱ ፤ ሴቶችም ፡ ለጌታችን ፡ እንደ ሚታዘዙ ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይታዘዙ ፤ ለሴት ፡ ገዥዋ ፡ ባሏ ፡ ነውና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገዥዋ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደኾነ ፤ የሥጋዋም ፡ መድኃኒት ፡ እንደኾነ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንድትታዘዝ ፡ እንደዚህም ፡ ሴቶች ፡ ለባሎቻቸው ፡ በሁሉ ፡ ይታዘዙ ፤ ወንዶችም ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ይውደዱ ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ወደዳት ፤ ስለ ፡ እርሷም ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፤ በውሃ ፡ በማጥመቅ ፤ በቃሉም ያነጻት ፡ ዘንድ ፤ ይቀድሳት ፡ ዘንድ ፤ የከበረችም ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ፤ ምስጋና ፡ ያቀርቡለት ፡ ዘንድ ፤ በላያቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ እድፍ ፤ ርኩሰት ፡ እንዳያገኝባቸው ፤ የነጻች ፤ የተቀደሰች ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ነው ፡ እንጂ ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። ፭ ፡ ፌጥ ፡ ፫ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፬፤ እንዲሁም ፡ ወንዶች ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ እንደራሳቸው ፡ ይውደዱ ፤ ሚስቱን ፡ የወደደ ፡ ራሱን ፡ ወደደ ኩዮ ፡ ሥጋውን ፡ መጥላት ፡ የሚቻለው ፡ የለም ፤ መግቡ ፤ ጠብቁ ፡ እንጂ ፤ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ጠበቃት ፤ እኛ ፡ ሕዋሳቶቹ ፡ ነንና ፡ ስለ ፡ ሚስቱም ፡ ወንድ ፡ አባትና ፡ እናቱን ፡ ትቶ ፡ ሚስቱን ፡ ይከተላል ፤ ሁለቱም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ይኾናሉ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ጥልቅ ፤ ረቂቅ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፤ እኔም ፡ ለክርስቶስና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሳሌ ፡ አድርጌ ፡ እናገረዋለሁ ፤ እንግዲያስ ፡ እናንተም ሁላችሁ ፡ እንደ ፡ ራሳችሁ ፡ አድርጋችሁ ፡ ሚስቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፤ ሴትም ፡ ባሏን ፡ ትፍራው ። ዘፍ ፪ ፡ ፳፬ ። ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፭ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።

፲፭፤ ልጆችም ፡ በጌታችን ፡ ትእዛዝ ፡ ለእናት ፡ ለአባታችሁ ፡ ታዘዙ ፤ ይህ ፡ የሚገባ ፡ ነውና ፡ በአሪትም ፡ ያዘዘው ፡ ደኅኖው ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እናት ፡ አባትህን ፡ እርዳ ፤ እውነተኛ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ይኾንልህ ፡ ዘንድ ፤ ዕድሜህም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፤ እናንተም ፡ አባቶች ፡ ልጆቻችሁን ፡ አታስቆጡ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲፈሩ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያውቁ ፡ ሠርታችሁ ፤ ቀጥታችሁ ፡ አሳድጉ ፡ እንጂ ። ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፩ ። መዝ ፡ ፫፫ ፡ (፫፯) ፡ ፬ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፮ ።

፲፫፤ ወአትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለቢጽክሙ ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአንስትኒ ፡ ይትአዘዛ ፡ ለአምታቲሆን ፡ ከመ ፡ ዘለእግዚእነ ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ርእሳ ፡ ለብእሲት ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ርእሳ ፡ ለቤተ ክርስቲያን ፡ ወመድኀኒ ፡ ሥጋሃ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትትኤዘዝ ፡ ለክርስቶስ ፡ ከማሁ አንስትኒ ፡ ይትአዘዛ ፡ በኵሉ ፡ ዕደውኒ ፡ ያፍቅሩ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ አፍቀራ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወመጠወ ፡ ርእሶ ፡ በእንቲአሃ ፡ ከመ ፡ ይቀድሳ ፡ ወያንጽሐ ፡ በጥምቀተ ፡ ማይ ፡ በቃሉ ፡ ወከመ ፡ ይረስያ ፡ ክብርተ ፡ ወያዕርጉ ፡ ልቱ ፡ ስብሓተ ፡ ከመ ፡ ኢይርከብ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ርስሐተ ፡ ወጥልቀተ ፡ ዘከመዝ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ንጽሕተ ፡ ወቅድስተ ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። ፭ ፡ ፌጥ ፡ ፫ ፡ ፭ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

፲፬፤ ከማሁ ፡ ዕደውኒ ፡ ያፍቅሩ ፡ አንስቲያሆሙ ፡ ከመ ፡ ነፍሶሙ ፡ ዘአፍቀረ ፡ ብእሲቶ ፡ ርእሶ ፡ አፍቀረ ፤ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ጸሊዓ ፡ ሥጋሁ ፡ ግሙራ ፡ አላ ፡ ሴስዩ ፡ ወተማኅፀኑ ፡ በከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ አባለ ፡ ሥጋሁ ፡ ንሕነ ወበእንተዝ ፡ የኀድግ ፡ ብእሲ ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ ወይተልዋ ፡ ለብእሲቱ ፡ ወይከውኑ ፡ ክልኤሆሙ ፡ አሐደ ፡ ሥጋ ። ዐቢይ ፡ ምሥጢር ፡ ውእቱ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ወአንሰ ፡ እብሎ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወላዕለ ቤተ ፡ ክርቲያኑ ፡ ወባሕቱ ፡ አንትሙኒ ፡ ከማሁ ፡ ኩልክሙ ፡ አፍቅሩ ፡ አንስቲያክሙ ፡ ወብእሲትኒ ፡ ከማሁ ፡ ትፍርሆ ፡ ለምታ ። ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፳፬ ። ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፭ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።

፲፭፤ ወውሉድኒ ፡ ተአዘዙ ፡ ለአዝማዲክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ እስመ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ወቀዳሚ ትእዛዝ ፡ ዘአሰፈወ ፡ በውስተ ፡ አሪት ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ከመ ፡ ይኩንከ ፡ ጽድቀ ፡ ወሠናየ ፡ ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ አበውኒ ፡ ኢታስተቁጥዑ ፡ ውሉደክሙ ፡ ሕፅኑ ፡ በተግሣጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበአእምሮ ፡ ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፳ ። መዝ ፡ (፫፫ ፡ ፫፯) ፡ ፬ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፮ ።

፲፮ ፤ ነባሪኒ ፡ ተአዘዙ ፡ ለአጋእዝቲከሙ ፡ እለ ፡ ይኳን ኑከሙ ፡ ሥጋከሙ ፡ በፍርሀት ፡ ወበረዓድ ፡ ወበ ልብ ፡ ስፉሕ ፡ ከመ ፡ ዘለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእኩ ፡ከመ ፡ ዘያደሉ ፡ ለዓይነ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ አግብርተ ፡ ክር ስቶስ ፡ እንዘ ፡ ትገብሩ ፡ ፈቃዶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሱሉ ፡ ነፍስክሙ ፡ በሕሊና ፡ ሠናይ ፡ ከመ ፡ ዘለ እግዚአብሔር ፡ ትትቀነዩ ፡ ወእኩ ፡ ከመ ፡ ዘለሰ ብእ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ሱሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሠናየ ፡ ይትዐሠይ ፡ በጎበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመኒ ፡ ነባሪ ፡ ወእመኒ ፡ አግዓዚ ፡ ወአጋዕዝትኒ ፡ ዕሩያ ፡ ግበሩ ፡ ሎሙ ፡ እንዘ ፡ ታቄርሩ ፡ መዓተክሙ ፡ ወተጎድጉ ፡ ሎሙ ፡ አበሳሆሙ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ለክሙ ፡ እግዚእ ፡ በሰማያት ፡ ዘኢያደሉ ፡ ለገጽ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፪ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ቈላ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፲፯ ፤ አኃዊነ ፡ ጽንዑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወበጽንዐ ፡ ኀይሉ ፡ ወልበሱ ፡ ወልታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘት ክሉ ፡ ተቃውሞቶ ፡ ለመናግንተ ፡ ሰይጣን ፡ እስመ ፡ ቀትልክሙኒ ፡ ኢኮነ ፡ ምስለ ፡ ዘሥጋ ፡ ወደም ፡ ዘእንበለ ፡ መኳንንት ፡ እለ ፡ ይመልኩ ፡ ዓለመ ፡ ጽልመት ፡ ወአጋንንት ፡ መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ መት ሕተ ፡ ሰማይ ፡ ወበእንተዝ ፡ ንሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትክህሉ ፡ ተቃውሞታ ፡ ለዕለት ፡ እኪት ፡ ወከመ ፡ ትክህሉ ፡ ሱሉ ፡ ገቢረ ፡ ወቋሙ ፡ እንከ ፡ ቀኒተክሙ ፡ ሐቂክሙ ፡ በጽድቅ ፡ ወልበሱ ፡ ወልታ ፡ ኀጺን ፡ ተስዒነክሙ ፡ ኀይለ ፡ ወንጌል ፡ ዘበሰላም ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ። ፭ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፪ ።

፲፰ ፤ ወምስለዝ ፡ ሱሉ ፡ ንሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ዘሃ ይማኖት ፡ በእደዊክሙ ፡ በዘትክሉ ፡ አጥፍዖተ ፡ ሱሉ ፡ አሕጻሁ ፡ ለእኩይ ፡ ርሱን ፡ ወንሥኡ ፡ ጌራ ፡ መድኃኒትክሙ ፡ ወሰይፈ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘውእቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሱሉ ፡ ጸሎት ፡ ወስእለት ፡ እንዘ ፡ ትጸልዩ ፡ በሱሉ ፡ ጊዜ ፡ በመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወምስሌሁ ፡ ትግሁ ፡ ወተጸመዱ ፡ በጸሎት ፡ በእንተ ፡ ሱሉ ፡ ቅዱሳን ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፮ ።

፲፮ ፤ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ በሥጋ ፡ ለሚገዝችሁ ፡ ጌቶቻችሁ ፡ በመፍራትና ፡ በመደንገጥ ፤ ልብንም ፡ በማስፋት ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደምትገዙ ፡ ተገዙ ፤ ለሰው ፡ ይም ሰል ፡ እንደሚገዛ ፡ ሰው ፡ አይደለም ፤ የእግዚአብ ሔርን ፡ ፈቃድ ፡ የምትሠሩ ፡ የክርስቶስ ፡ አገልጋ ዮች ፡ እንደ ፡ መኾናችሁ ፤ በፍጹም ፡ ሰውነታችሁ ፡ በበጎ ፡ ሕሊና ፡ ለሰው ፡ እንደሚገዛ ፡ ያይደለ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ እንደምትገዙ ፡ ተገዙላቸው ፡ ጌታም ፡ ቢኾን ፡ ቤተ ፡ ሰብም ፡ ቢኾን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ እን ዲያገኝ ፡ ዐውቃችሁ ፤ ጌቶችም ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቻ ችሁ ፡ የተካከለ ፡ ሥራ ፡ ሥሩላቸው ፤ ቁጣችሁን ፡ ትታችሁ ፡ የበደሏችሁንም ፡ ይቅር ፡ እያላችሁ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ የማያደላ ፡ ጌታ ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡ አላችሁ ፡ ታውቃላችሁና ። ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ቈላ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

፲፯ ፤ እንግዲህስ ፡ ወንድሞቻችን ፡ በእግዚአብሔር ፡አምና ችሁ ፡ በኀይሉ ፡ አጋዥነት ፡ ጽኑ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጋሻ ፡ ልበሱ ፤ የሰይጣንን ፡ ተንኮል ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ መቃወምን ፡ በምትችሉ ፡ ኀንዘብ ፤ ሰልፋችሁ ፡ከሥ ጋዊ ፤ ከደማዊ ፡ አርበኛ ፡ ጋር ፡ አይደለምና ፡ ዓለመ ፡ ጽልመትን ፡ ከሚገዙ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ካሉ ፡ ከር ኩሳን ፡ መናፍስት ፡ አጋንንት ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጋሻ ፡ ያዙ ፤ ክፉይ ቱን ፡ ቀን ፡ መቃወም ፡ ይቻላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ድል ፡ ትነሱ ፡ ዘንድ ፡ በሁሉ ፡ የተዘጋጃችሁ ፡ ኹኑ ፤ ወገባ ችሁን ፡ በጽድቅ ፡ ዝናር ፡ ታጥቃችሁ ፡ ቁሙ ፤የጽድ ቅንም ፡ ጥሩር ፡ ልበሱ ፤ ፍቅርን ፡ የምትናገር ፡ የወን ጌልን ፡ ኀይል ፡ ተጫምታችሁ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፭ ። ፭ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፪ ።

፲፰ ፤ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ የሃይማኖትን ፡ የጦር ፡ መሣ ሪያ ፡ በእጃችሁ ፡ ያዙ ፤ የጋለ ፤ የጋመ ፡ የክፉውን ፡ የሰይጣንን ፡ ፍላጻ ፡ ሁሉ ፡ ማጥፋት ፡ በሚቻላችሁ ፡ ኀንዘብ ፤ የሚያድናችሁን ፡ ራስ ፡ ቁር ፡ በራሳችሁ ፡ ጫኑ ፤ በእጃችሁም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሰይፍ ፡ ያዙ ፤ ይኸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ በጸሎትና ፡ በልመና ፤ ሁሉ ፡ ስትጸልዩ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በልቡና ፡ ትጉ ፤ ስለ ፡ ቅዱሳንም ፡ ሁሉ ፡ ጸሎትን ፡ አዘውትሩ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፳፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ እመጽሐፈ ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ እጉሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ እምአይቴ ፡ ለክሙ ፡ ጸብዕ ፡ ወቀትል ፡ አኮኑ ፡ እምዝየ ፡ እምአፍቅሮ ፡ ዝሙት ፡ ዘይትገበር ፡ እም ውስተ ፡ አንጦዕክሙ ፡ ትፈትዉሂ ፡ ወኢትረክቡ ፡ ትትቃተሉሂ ፡ ወትትቃንዉሂ ፡ ወኢትክሉ ፡ ረኪበ ።

፪ ፤ ትትበዐሉሂ ፡ ወትጸብዑሂ ፡ ወኢትረክቡ ፡ እስመ ፡ ኢትስእሉ ።

፫ ፤ ትስእሉሂ ፡ ወኢይሁቡክሙ ፡ እስመ ፡ ለእኩይ ፡ ትስእሉ ፡ ለዝሙትክሙ ፡ ከመ ፡ ተሀቡ ። መዝ፡ ፲፫ ፡ (፲፪) ፡ ፵፪ ።

፬ ፤ ኦ ዘማውያን ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ፍቁሩ ፡ ለዝ ዓለም ፡ ጸላኢሁ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ዘአፍቀሮ ፡ ወዘአብደሮ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ጸላኢሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይከውን ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፯ ።

፭ ፤ ወሚመ ፡ ይመስለክሙኑ ፡ ዘሐሰተ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ በእንተ ፡ ተቃንየ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ተወቢ ፡ ሞገሰ ፡ የሀብክሙ ፡ እግዚእነ ።

፮ ፤ በእንተዝ ፡ ይቤ ፡ ለዕቡያን ፡ ያጎሥሮሙ ፡ ወለ እለሰይቴሕቱ ፡ ርእሶሙ ፡ ይሁቦሙ ፡ ሞገሰ ፡ ኢዮ ፡ ፳፪ ፡ ፳፱ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

፯ ፤ አሆ ፡ በልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወእንብየ ፡ በልዎ ፡ ለጋኔን ፡ ወይጐይይ ፡ እምኔክሙ ፡ ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።

፰ ፤ ቅረብዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይቀርበክሙ ፡ አን ጽሑ ፡ ልበክሙ ፡ ኃጥኣን ፡ ወአንጽሑ ፡ እደዊ ክሙ ፡ እለ ፡ ትናፍቁ ። ዘካ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።

፱ ፤ ግኑዩ ፡ ወላህዉ ፡ ወብክዩ ፡ ወለሰሐቅክሙኒ ፡ ሚጥዎ ፡ ውስተ ፡ ላህ ፡ ወለትፍሥሕትክሙኒ ፡ ውስተ ፡ ትካዝ ፡ አግብእዎ ።

፲ ፤ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ወያሌዕለክሙ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

፲፩ ፤ ወኢትትሐመዩ ፡ በበይናቲክሙ ፡ አኃዊነ ፡ እስመ ፡ ዘሐመዮ ፡ ለካልዑ ፡ ሐመዮ ፡ ለሕገ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወእመሰ ፡ ሕጎ ፡ ትግዕዝ ፡ ኢኮንክ ፡ ገባሬ ፡ ሕግ ፡ ወኮንክ ፡ አንተ ፡ ገዓዚሃ ፡ ለሕግ ፡ መዝ ፡ ፲፩ ፡ (፲፩) ፡ ፫ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩ ።

፲፪ ፤ እስመ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ወሀቢሃ ፡ ለሕግ ፡ ወመኰ ንና ፡ ለሕግ ፡ ዘውእቱ ፡ ይክል ፡ አማስናሂ ፡ ወአ ድኅኖሂ ፡ አንተኬ ፡ ምንትኑ ፡ ዘትግዕዝ ፡ ቢጸከ ፡ ወዘተሐምዮ ፡ ለካልዕከ ። ማቴ ፡ ፯ ፡ ፩ ።

፲፫ ፤ ከመ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ዮም ፡ አው ፡ ጌሠመ ፡ ነሐ ውር ፡ ውስተ ፡ እንታክቲ ፡ ሀገር ፡ ወንነብር ፡ ውስ ቴታ ፡ ሕዳጠ ፡ ዓመተ ፡ ወንትጌበር ፡ ውስቴታ ፡ ወንረብሕ ፡ ወኢያአምሩ ፡ ዘይከውን ፡ ጌሠመ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፯ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፳፯ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፲፬ ፤ የጌታችን ፡ ወንድም ፡ ሐዋርያው ፡ ያዕቆብ ፡ ከጻፈው መጽሐፍ ፤ ጸብ ፤ ክርክር ፡ ከወዴት ፡ መጣባችሁ ? በቅልጥማችሁ ፡ የሚሠራ ፡ ዝሙትን ፡ ከመውደድ ፡ የተነሣ ፡ ከዚህ ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፤ ትመኛላችሁ ፡ የምትሹትን ፡ አታገኙም ፤ ትቃናላችሁ ፤ ትጋደ ላላችሁ ፤ ስለዚህም ፡ ማግኘት ፡ አይቻላችሁም ።

፲፭ ፤ ትጣላላችሁ ፡ ትዋጋላችሁ ፤ የምትሹትንም ፡ አታ ገኙም ፤ አትለምኑምና ።

፲፮ ፤ ብትለምኑም ፡ አይሰጣችሁም ፤ ሰውነታችሁን ፡ ለዝሙት ፡ ትሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ ትለምናላችሁና ። መዝ ፡ ፲፫ ፡ (፲፪) ፡ ፵፪ ።

፲፯ ፤ ዘማውያን ፡ ሆይ ፤ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ወዳጅ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ጠላት ፡ እንደሆነ ፡ አታውቁምን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የወደደው ፤ የመረጠው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላት ፡ ይኾናልና ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፯ ።

፲፰ ፤ ወይስ ፡ ስለመቃናት ፡ መጽሐፍ ፡ ሐሰት ፡ የሚናገር ፡ ይመስላችኋልን ፤ ጌታችን ፡ የምትበልጠውን ፡ ባለሟልነት ፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ።

፲፱ ፤ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዕቢተኞችን ፡ ያዋርዳ ቸዋል ፤ ትሑታንን ፡ ግን ፡ ያከብራቸዋል ፡ አለ ። ኢዮ ፡ ፳፪ ፡ ፳፱ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

፳ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እሽ ፡ በጅ ፡ በሉት ፤ ጋኔንን ፡ ግን ፡ እንቢ ፡ በሉት ፡ ከአናንተም ፡ ይሸሻል ። ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።

፳፩ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ቅረቡት ፤ እሱም ፡ ይቀርባችኋል ፡ ኃጥኣን ፡ እጃችሁን ፡ ከመግደል ፤ ልባችሁንም ፡ ክበደል ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ፡ የምትጠራጠሩም ፡ እመኑ ። ዘካ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፮ ።

፳፪ ፤ እዘኑ ፡ አልቅሱ ፤ ሳቃችሁን ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ ደስታ ችሁንም ፡ ወደ ፡ ኀዘን ፡ መልሱት ።

፳፫ ፤ ራሳችሁን ፡ አዋርዱ ፡ ።። እግዚአብሔር ፡ ያከብራ ችኋልና ። ፩ ፡ ጴ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

፳፬ ፤ ወንድሞቻችን ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ አትነቃቀፉ ፤ ወንድሙን ፡ የነቀፈ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ነቅ ፎአልና ፤ ሕጉንስ ፡ ከነቀፍክ ፡ ሕግን ፡ የምትፈጽም አይደለም ፤ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ነኽ ፡ እንጂ ። መዝ ፡ ፲፩ ፡ (፲፩) ፫ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩ ።

፳፭ ፤ ሕግን ፡ የሰጠ ፤ በሕግ ፡ አፍራሽም ፡ የሚፈርድ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ ማዳንም ፤ መግደልም ፡ የሚቻለው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ወንድምህን ፡ የምትነቅፍ ፤ ወዳጅህን ፡ የምታማ ፡ አንተ ፡ ምንድነህ ? ማቴ ፡ ፯ ፡ ፩ ።

፳፮ ፤ ዘንድሮ ፤ ወይም ፡ ከርሞ ፡ ወደዚያች ፡ ሀገር ፡ እን ሔዳለን ፤ በእሷም ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንኖራለን ፤ ሥራም ፡ ሠርተን ፡ እንጠቀማለን ፡ እንደሚሉ ፤ ከርሞ ፡ የሚኾነውንም ፡ እንደ ፡ ማያውቁ ፡ ሰዎች ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ያልኋ ።

፲፬ ፤ ምንትኑመ ፡ ሕይወትክሙ ፡ አኮኑ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ ዘለምዕር ፡ ያስተርኢ ፡ ወእምዝ ፡ ይማስን ።

፲፭ ፤ ዘእምትቤሉ ፡ እመ ፡ ሠምረ ፡ እግዚአብሔር፡ ወሐየውን ፡ ንገብር ፡ ዘንተ ፡ እው ፡ ዝክተ ።

፲፮ ፤ ወይእዜሰ ፡ ትትሜክሑ ፡ በምግባሪክሙ ፡ ዙላ ፡ ትምክሕት ፡ እንተ ፡ ከመዝ ፡ እኪት ፡ ይእቲ ።

፲፯ ፤ ወዘሰ ፡ የአምር ፡ ገቢረ ፡ ሠናይት ፡ ወኢይገብራ ፡ ኃጢአተ ፡ ትከውኖ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፵ ።

፲፰ ፤ ንዑ ፡ ይእዜኒ ፡ አብዕልት ፡ ብክዩ፡ እንዘ ፡ ትግዕሩ ፡ ላዕለ ፡ ሕርትምናክሙ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ትምጻእክሙ ።

፲፱ ፤ ብዕልክሙኒ ፡ ነቅዘ ፡ ወአልባሲክሙኒ ፡ ቆንቆን ፡ ወርቅክሙኒ ፡ ወብሩርክሙኒ ፡ ዝሕለ ፡ ወዛሕሉኒ ፡ ይዛለፈክሙ ፡ ወስምዓ ፡ ይክውን ፡ በላዕሌክሙ ፡ ወይበልዖ ፡ ለሥጋክሙ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ በእንተ ፡ ዘገበርክሙ ፡ ለደኃሪ ፡ መዋዕል ።

፳ ፤ ናሁ ፡ ዐስቦሙ ፡ ለገባር ፡ ለእለ ፡ ሐረስዋ ፡ ለምድርክሙ ፡ ወሄድክምዎሙ ፡ የዐወይው ፡ ወገዓርሙ ፡ ለዐጸድ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ እዘኒሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸባኦት ፡ ወበጽሐ ። ዘዳግ ፡ ፳፬ ፡ ፲፱ና ፲፭ ።

፳፩ ፤ ፈጋዕክሙ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወአስተትክሙ ፡ ወተ ደለውክሙ ፡ ወአስባሕክሙ ፡ ልበክሙ ፡ ከመ ፡ ዘያሰብሕ ፡ ላህመ ፡ ለዕለተ ፡ ጥብሐት ።

፳፪ ፤ ወተዐደውክሙ ፡ ወቀተልክምዎ ፡ ለጸድቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ይትቃወምክሙ ፡ ወአሆ ፡ ይብለክሙ ፡ ተዐገሡ ፡ እንክ ፡ አኃዊነ ፡ እስከ ፡ ደኃሪት ፡ ዕለት ፡ እመ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚእክሙ ፡ ከመ ፡ ሐረሳዊ ፡ ይጸንሕ ፡ ፍሬሃ ፡ ለምድር ፡ ክብርት ፡ ወይትዔገሣ ፡ ሠርክ ፡ ወነግሀ ፡ እስክ ፡ ትሰዊ ፡ ወትፈሪ ፡ ወትት ዐጸድ ።

፳፫ ፤ ተዐገሡኬ ፡ አንትሙኒ ፡ ወአጽንዑ ፡ ልበክሙ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእክሙ ፡ ከመ ፡ ትትፈሥሑ ፡ ወኢትግዕሩ ፡ አኃዊነ ፡ ዲበ ፡ ቢጽክሙ ከመ ፡ ኢትትኰነኑ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ መኰንን ፡ ጎበ ፡ መድረክ ፡ ኖኅትክሙ ፡ በጽሐ ፡ ወይጸንሕ ።

፳፬ ፤ አርአያሃሰ ፡ ለትዕግሥትክሙ ፡ ብክሙ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ተነበዩ ፡ ወተናገሩ ፡ በቃሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ ናስተበጽዖሙ ፡ ለእለ ፡ ተዐገሡ ፡ሰማዕክሙ ፡ እንክ ፡ ትዕግሥቶ ፤ ለኢዮብ ፡ ዘገብረ ፡ ወፈጸመ ፡ ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወርኢክሙ ፡ ከመ ፡ ብዙኅ ፡ ምሕረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወመስተሣህል ፡ ውእቱ ።

፳፭ ፤ ወእምኵሉሰ ፡ ዘይቀድም ፡ አኃዊነ ፡ ኢትምሐሉ ፡ ኢበሰማይ ፡ ወኢበምድር ፡ ወኢበካልዕ ፡ መሐላ ፡ ወኢበዘኮነ ፡ መሐላ ፡ ግሙራ ፡ ወኢበምንትኒ ፡ አላ ፡ ፭ደ ፡ ይኩን ፡ ቃልክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ ከመ ፡ ኢትትኰነኑ ፡ ወኢትባአኡ ፡ ውስተ ፡ ደይን ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ያልኋ ።

፲፱ ፤ አኍኍራችሁ ፡ ምንድርነው፣ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ታይቶ ፡ ኋላ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ጢስ ፡ አይደላችሁምን? ።

፲፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድ ፤ ብንኖርም ፡ ይኸንን ፡ ወይም ፡ ያንን ፡ እናደርጋለን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ።

፲፮ ፤ ዛሬ ፡ በሥራችሁ ፡ ትመካላችሁ ፡ እንዲህ ፡ ያለች ፡ መመካት ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ናት ።

፲፯ ፤ በጎዱቱን ፡ ሥራ ፡ ዐውቆ ፤ የማይሠራት ፤ ኃጢአት ፡ ትኾንበታለች ፡ ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፵ ።

፲፰ ፤ አሁን ፡ ባለጸጎች ፡ ትመጣባችሁ ፡ ዘንድ ፡ ባላት ፡ መከራ ፡ እየተጨነቃችሁ ፡ ኑ ፡ አልቅሱ ።

፲፱ ፤ አህላችሁ ፡ ነቀዘ ፤ ልብሳችሁንም ፡ ብል ፡ በልቶ ታል ፤ ወርቃችሁና ፡ ብራችሁም ፡ ዛገ ፤ ዝገቱም ፡ ይዘልፋችኋል ፤ ምስክርም ፡ ይኾንባችኋል ፤ በኋላ ዘመን ፡ ብላችሁ ፡ ስለ ፡ አከማቻችሁትም ፡ ሥጋ ችሁን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይበላዋል ።

፳ ፤ ምድራችሁን ፡ የሚያርሱ ፡ የገበሬዎችን ፡ ደመወዝ ፡ እነሆ ፡ ቀምታችኋቸው ፡ ይጮኻሉ ፤ የሠራተኞችም ፡ ጩኸታቸው ፡ አቸናፊ ፡ ወደሚኾን ፡ ወደ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ጆሮ፡ ደርሶ፡ተሰምቷል።ዘዳግ፡፳፬፡፲፭ና፲፭ ።

፳፩ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አላችሁ ፤ ሥርዐት ፡አንደላችሁ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደረጋችሁ ፤ ሰው ፤ ላምን፡ ለሚታረድበት ፡ ቀን ፡ እንዲያሰባ ፡ ልባችሁን ፡ አሰባችሁ ።

፳፪ ፤ ሕግ ፡ ተላለፋችሁ ፤ ጻድቁንም ፡ ሳይጣላችሁ ፤ አይኾንም ፡ ሳይላችሁ ፤ ገደላችሁት ፤ ወንድሞቻችን ፡ ጌታችሁ ፡ እስከሚመጣበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ መከራውን ፡ ታገሡ ፤ የከበረችውን ፡ የምድር ፡ ፍሬ ፡ እስክትሸትና ፤ እስክታፈራ ፤ እስክትታጨድም ፡ ድረስ ፡ ታግሦ ፡ ዒት ፡ ማታ ፡ ደጅ ፡ እንደ ጠና ፡ ገበሬ ።

፳፫ ፤ እናንተም ፡ ታግሣችሁ ፡ ልባችሁን ፡ አጽኑ ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፤ ጌታችሁ ፡ የሚመጣባት ፡ ቀን ፡ ቀርባለችና ፡ ወንድሞቻችን ! በባልንጀራችሁ ፡ አትጮኹ፤ እንዳይፈረድባችሁ ፡ እነሆ ፡ፈራጅ ፡ ከደጃችሁ ፡ መድረክ ፡ ቆሞ ፡ ይጠብቃልና ።

፳፬ ፤ ወንድሞቻችን ፡ መከራችሁን ፡ ለመታገሥ ፡ ምሳሌ የሚኾኗችሁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዘው ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩ ፡ ነቢያት ፡ አሉላችሁ ፤ መከራውን ፡ የታገሡትንም ፡ እነሆ ፡ እናመሰግናቸዋለን ፤ የኢዮብን ፡ ትዕግሥቱን ፡ ሰምታችኋል ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሠራለትን ፤ የፈጸመለትን ፡ አይታችኋል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ይቅር ፡ ባይም ፡ ነውና ።

፳፭ ፤ ወንድሞቻችን ! ከሁሉ ፡ የሚቀድም ፤ አትማሉ ፤ በሰማይም ፤ በምድር ፡ ቢኾን ፤ በሌላም ፡ መሐላ ፡ ቢኾነውም ፡ መሐላ ፡ ቢኾን ፤ ከቶ ፡ በምንም ፡በምን ፡ አትማሉ ፤ ቃላችሁ ፡ አንድ ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፤እውነት ቢኾን ፡ እውነት ፤ የሌለም ፤ ቢኾን ፡ የለም ፡ ማለት፡ ይኹን ፤ ተፈርዶባችሁ ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡ እንዳትገቡ፡

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፯ ። ም ፡ ፻፳፰ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፯ ፡ ም ፡ ፻፳፰

፳፯ ፤ እመቦ ፡ ዘይቴክዝ ፡ ለይጸሊ ፡ ወእመቦ ፡ ዘይትፌ ሣሕ ፡ ለይዘምር ፡ ወእመቦ ፡ ዘይደሚ ፡ ለይጸውዕ ፡ ቀሳውስተ ፡ እለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይጼልዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ቀቢያሙ ፡ ቅብዐ ፡ ጸሎት ፡ በስሙ ፡ ለእ ግዚእነ ።

፳፯ ፤ የሚያዝን ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይጸልይ ፤ ደስ ፡ ያለውም። ቢኖር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሉ ፡ ቀሳውስትን ፡ ጠርቶ ፡ ይጸልዩለት ፤ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ስም ፡ የጸለዩበትን ፡ ዘይት ፡ ይቅቡት ።

፳፯ ፤ ወጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ያሐይዎ ፡ ለድውይ ፡ ወያነ ሥእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእመኒ ፡ ቦቱ ፡ ኃጢአት ፡ ይትኀደግ ፡ ሎቱ ።

፳፯ ፤ አምኖ ፡ የሚጸልዩትም ፡ ጸሎት ፡ ድውዩን ፡ ያድ ነዋል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያሥነሣዋል ፤ ኃጢአ ትም ፡ ቢኖርበት ፡ ይሰረይለታል ።

፳፰ ፤ ተአመኑ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ኃጢአተክሙ ፡ ወጸ ልዩ ፡ ላዕለ ፡ ቢጽክሙ ፡ ከመ ፡ ትሕየው ፡ ብዙኀ ፡ ትረድእ ፡ ጸሎተ ፡ ጻድቅ ፡ ትክል ፡ ወታሠልጥ ።

፳፰ ፤ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ተናዘዙ ፤ ለባ ልንጀሮቻችሁ ፡ ጸልዩ ፤ በሕይወት ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ የጻድቅም ፡ ጸሎት ፡ እጅግ ፡ ትረዳለች ፤ ግዳጅም ፡ መፈጸም ፡ ይቻላታል ።

፳፱ ፤ ኢልያስ ፡ ዘከማነ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ወጸለየ ፡ ከመ ፡ ኢይዝ ንም ፡ ዝናም ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወኢዘንመ ፡ ፫ተ ፡ ዓመተ ወ፮ተ ፡ አውራኀ ። ፭ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ። ሎቃ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ።

፲፱ ፤ ኤልያስ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ እንድንታ መም ፡ ይታመግል ፤ ዝናም ፡ እንዳይዘንም ፡ ጸለየ ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናም ፡ አልዘነመም ። ፭ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፳፭ ።

፴ ፤ ወካዕበ ፡ ጸለየ ፡ ከመ ፡ ይዝንም ፡ ዝናም ፡ ወወ ሀበ ፡ ዝናሞ ፡ ሰማይ ፡ ወምድርኒ ፡ ወሀብት ፡ ፍሬሃ ፡ ፬ ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፵፪ ።

፴ ፤ ዳግመኛ ፡ ይዘንም ፡ ዘንድ ፡ ጸለየ ፤ ሰማይ ፡ ዝና ሙን ፡ ሰጠ ፤ ምድርም ፡ ፍሬዋን ፡ ሰጠች ፤ ፬ ፡ ነገ ፡ ፲፰ ፡ ፵፪ ።

፴፩ ፤ አኃዊነ ፡ እመቦ ፡ ዘስሕተ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ እምኔክሙ ፡ ወእመቦ ፡ ዘሜጠ ፡ እምጌጋዩ ፡ ለያ እምር ፡ እንከ ፡ ዘሜጠ ፡ ለኃጥእ ፡ ጊጉይ ፡ ሰበ ፡ ተሐጉለ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ከመ ፡ አድነነ ፡ ነፍሶ ፡ እምነ ፡ ሞት ፡ ወከደናን ፡ ለብዙኃት ፡ ኃጣውኢሁ ።

፴፩ ፤ ወንድሞቻችን ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ከእውነት ፡ መን ገድ ፡ የተሳሳተ ፡ ቢኖር ፡ ከኃጢአቱ ፡ የመለሰውም ፡ ቢኖር ፤ እንዲህ ፡ ያ ፡ ከጽድቅ ፡ ጐዳና ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በደለኛውን ፡ የመለሰው ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ከሞት ፡ እንደ ፡ አዳነ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአቱንም ፡ እንደ ፡ አስ ተሰረየ ፡ ይወቅ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፳፭ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፳፭ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ እመጽሐፈ ፡ ግብሮሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ንጹሓን ፡ ወሀሎ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘሀገረ ፡ ቂጣርያ ፡ ዘስሙ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ወሃቢ ፡ ውእቱ ፡ ለሕዝበ ፡ ሠዲረ ፡ እንተ ፡ ይብልዋ ፡ ኢጣሊቄ ፡ ጻድቅ ፡ ወፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ቤቱ ፡ ወይ ገብር ፡ ምጽዋተ ፡ ብዙኀ ፡ ለሕዝብ ፡ ወይጼሊ ፡ ወትረ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳን ፡ ፬ ፡ ፳፱ ።

፩ ፤ የንጹሓን ፡ ሐዋርያትን ፡ ሥራ ፡ ከሚናገር ፡ መጽ ሐፍ ፡ አንድ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚባል ፡ የቂጣርያ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ኢጣሊቄ ፡ ለሚሏትም ፡ የጭፍራ ፡ ወገን ፡ አለቃ ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ጻድቅና ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፤ ለሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ ምጽዋት ፡ የሚመጸውት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚጸልይ ፡ ነበር ። ዳን ፡ ፬ ፡ ፳፱ ።

፪ ፤ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሠተ ፡ ጊዜ ፡ ተሠዓት ፡ ሰዐት ፡ መዐልት ፡ ወቦአ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ወነጸረ ፡ ወፈርሀ ፡ ወይቤሎ ፡ ምንተ ፡ ትብል ፡ እግዚኦ ፡ ወይቤሎ ፡ ጸሎትከ ፡ ወምጽዋትከ ፡ ዐርገ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለተዝካርከ ፡ ወይእዜኒ ፡ ፈኑ ፡ ዕደወ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ለከ ፡ ለስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ ዘየኀ ድር ፡ ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ሰፋዬ ፡ ዘመንገለ ፡ ባሕር ፡ ወውእቱ ፡ ይነግረከ ፡ ዘሀለወከ ፡ ትግበር ።

፪ ፤ ከቀኑም ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ በግልጥ ፡ ታየው ፤ ወደ ፡ እርሱም ፡ ገብቶ ፡ ቆርኔሌ ዎስ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ እሱም ፡ አቤት! ምን ፡ አልክ ፤ አለው ፡ መልአኩም ፡ ጸሎትኽና ፡ ምጽዋትህ ፡ መታ ሰቢያ ፡ ሊኾንህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወረገ ፤ አሁንም ፡ ከባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ባለችው ፡ በኢዮጴ ፡ አገር ፡ በሰፈው ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስን ፡ ይጠሩልህ ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ ላክ ፤ ታደርገውም ፡ ዘንድ ፡ የሚገባህን ፡ እርሱ ፡ ይነ ግርሃል ፡ አለው ።

፫ ፤ ወጎሊፎ ፡ መልአክ ፡ ዘተናገሮ ፡ ወጸውዐ ፡ ፪ተ ፡ እምወዓልያኒሁ ፡ ወ፩ደ ፡ ሐራ ፡ ጐረ ፡ እምጸግዱ ፡ ወነገሮሙ ፡ ዅሎ ፡ ወለአኮሙ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ።

፫ ፤ ይናገረውም ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ከሎላቱ ፡ ሁለቱን ፤ ከማይለዩትም ፡ ጭፍሮቹ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ አንዱን ፡ ወታደር ፡ ጠራ ፤ ሁሉንም ፡ ነግሮ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ላካቸው ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፰ ።

፩ ፤ ወበሳኒታ ፡ እንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በጽሑ ፡ ኢዮጴ ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ ፡ ሀገር ፡ ወጴጥሮስኒ ፡ ዐርገ ፡ ናሕሰ ፡ ይጸሊ ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ፡ እስመ ፡ ርኀበ ፡ ወፈቀደ ፡ ይምሳህ ፡ ወእንዘ ፡ ያስተዳልዉ ፡ ሎቱ ፡ መጽአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ድንጋፄ ።

፪ ፤ ወርእየ ፡ ሰማየ ፡ ርኅወ ፡ ወይወርድ ፡ ከመ ፡ ዘሞ ጣሕት ፡ ዐቢይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወእጉዝ ፡ በ፬ቱ ፡ ጽንፈሁ ፤ ወቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ወአርዌ ፡ ገዳም ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወነበቦ ፡ ቃል ፡ ወይ ቤሎ ፡ አ ጴጥሮስ ፡ ተንሥእ ፡ ሕርድ ፡ ወብላዕ ።

፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ ግሙራ ፡ ኢቦአ ፡ ርኵስ ፡ ውስተ ፡ አፋየ ፡ ወኢበላዕኩ ፡ ዘኢ ኮን ፡ ንጹሐ ፡ ወነበቦ ፡ ዳግመ ፡ ወይቤሎ ፡ ዘእግዚ አብሔር ፡ አስተናጽሐ ፡ አንተ ፡ ኢታስተራኵስ ።

፬ ፤ ወከመዝ ፡ ይቤሎ ፡ ሥልሰ ፡ ወኵሉ ፡ ተመይጠ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወእንዘ ፡ ይሔሊ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምንት፡ ውእቱ ፡ ዘአስተርአየ ፡ ወበጽሑ ፡ ዕደው ፡ አለ ፡ ተፈንዉ ፡ እምኀበ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ወቆሙ ፡ ኀበ ፡ ዴዴ ፡ ወሐተቱ ፡ ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ወጸውኡ ፡ ለእ መሁ ፡ ስምዖን ፡ ዘተሰምየ ፡ ጴጥሮስ ፡ በህየ ፡ የኀድር ።

፭ ፤ ወእንዘ ፡ ይሔሊ ፡ ጴጥሮስ ፡ በእንተ ፡ ዘአስተርአየ ፡ ይቤሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናሁ ፡ ሠለስቱ ፡ ዕደው ፡ የኀሥሡከ ፡ ወተንሥእ ፡ ወረደ ፡ ወሑር ፡ ምስ ሌሆሙ ፡ እንዘ ፡ ኢትናፍቅ ፡ ወኢምንተኒ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ፈነውክዎሙ ።

፮ ፤ ወወረደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀበ ፡ እሙንቱ ፡ ዕደው ፡ ወይ ቤሎሙ ፡ ነየ ፡ አነ ፡ ዘተኀሥሡኒ ፡ ለምንት ፡ መጻ እክሙ ፡ ወይቤልዎ ፡ እሙንቱ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ሀቢ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ወፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወየአምርዎ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡ ወአስተ ርአየ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤሎ ፡ ከመ ፡ ይጸ ውዕከ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወይስማዕከ ፡ ዘትነግሮ ።

፯ ፤ ወጸውዖሙ ፡ ወአኀደሮሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወበ ሳኒታ ፡ ሐረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወቦ ፡ እምቢጾሙ ፡ እም ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ እለ ፡ ሐሩ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወበሳ ኒታ ፡ ቦአ ፡ ሀገረ ፡ ቂሣርያ ፡ ወሀሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ይጸንሖሙ ፡ ወጸውዓ ፡ አዝማዲሁ ፡ ወማኅፈሮ ።

፰ ፤ ወቦአ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወተቀበሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ወሰ ገደ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወአንሥአ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡ ወአነኒ ፡ ከማከ ፡ ሰብእ ።

፱ ፤ ወቦአ ፡ እንዘ ፡ ይትናገሩ ፡ ወረከበ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብአ ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለሊክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ኢይከውኖ ፡ ለፈጹ ፡ ብእሲ ፡ ለእይሁዳዊ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ወይባእ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ሕዝብ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፰ ።

፩ ፤ በነጋውም ፤ ሔደው ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ በር ፡ ኢዮጴ ደረሱ ፤ ጴጥሮስም ፡ በሰባት ፡ ሰዓት ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ፤ ያንጊዜም ፡ ርቦት ፡ ሊበላ ፡ ወዶ ፡ ነበር ፡ ሰዎቹም ፡ መብል ፡ ሲያዘጋጁለት ፡ ተደሞ ፡ መጣበት ።

፭ ፤ ሰማይ ፡ ተከፍቶ ፡ ታላቅ ፡ መጋረጃ ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ፤ በዐራቱ ፡ መዓዝንም ፡ ተይዞ ፤ በውስጡም ፡ የምድር ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡አራ ዊትም ፤ የሚንቀሳቀሱ ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ነበ ሩበት ፡ ጴጥሮስ ፡ ሆይ! አርደህ ፡ ብላ ፡ የሚል ቃልም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጣ ።

፮ ፤ ጴጥሮስም ፡ አቤቱ ! አይኾንም ፤ ርኵስ ፤ የሚያ ጸይፍም ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅም ፡ አለ ፤ ደግሞም ፡ ሁለተኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታ ርክሰው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

፯ ፤ ይህንንም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነገረው ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ተመለሰ፤ጴጥሮስም ፡ ሰላየው ፡ ራእይ ፤ ምን ፡ ይኾን ፡ ብሎ ፡ ሲያስብ ፡ እነሆ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የላካቸው ፡ ሰዎች ፡ የስምዖንን ፡ቤት ፡ እየጠየቁ ፡ በደጁ ፡ ቁመው ፡ ነበሩ ፤ ጠርተውም ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለው ፡ ስምዖን ፡ ወደ ፡ እዚህ ፡እን ግድነት ፡ መጥቶ ፡ እንደሆነ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ።

፰ ፤ ጴጥሮስም ፡ ስለ ፡ ታየው ፡ ነገር ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያ ወርድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እነሆ ፤ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ይፈልጉሃል ፤ ስለዚህም ፤ ተነሥተህ ፡ ውረድ ፤እኔም፡ ልኬያቸዋለሁና ፡ ሳትጠራጠር ፡ ከእነርሳቸው ፡ ጋር ፡ ሒድ ፡ አለው ።

፱ ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ ወርዶ ፡ እነሆ ፡ የምትፈ ልጉኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ለምን ፡ መጣችሁ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፤ ሹሙ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፤ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ የአይሁድ ፡ ሕዝብም ያውቁታል ፤ ቅዱስ ፡ መልአክ ፡ ተገልጦ ፡ ስለ ፡ አዘ ዘው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እንዲጠራኽ ፤ የምትነግረው ንም ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰማኽ ፡ አዞታል ፡ አሉት ።

፲ ፤ ተቀብሎም ፡ በቤቱ ፡ አሳደራቸው ፤ በነጋውም ፡ ጴጥ ሮስ ፡ ከእነርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሔደ ፤ ከኢዮጴ ፡ ብዙ ፡ ወንድሞች ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የሔዱ ፡ አሉ ፤ በነጋ ውም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ገቡ ፤ ቆርኔሌዎስም ፡ ዘመዶቹንና ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቹን ፡ ሁሉ ፡ ጠርቶ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ጴጥሮስም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፤ ቆርኔሌዎስ ፡ ሊቀበለው ፡ ወጣ ፤ ከእግሩም ፡ በታች ፡ ወድቆ ፡ ሰገደለት ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ አንተው ፡ ሰው ፡ ነኝና ፡ ተነሥ ፡ ብሎ ፡ አስነሣው ።

፲፪ ፤ እየተነጋገሩ ፡ ገቡ ፤ በዚያም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተከማ ችተው ፡ አገኙ ፤ ጴጥሮስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፤ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ሊገናኝ ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ ሊገባ ፡ እንደማይገባው ፡ እናንተም ፡ ታውቃላችሁ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፰ ።

፲፫ ፤ ወሊተሰ ፡ አርአየኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢያስተ
ራኵሶ ፡ ለሰብእ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ለመኑሂ ፡ ወይእ
ዜኒ ፡ ኢናፍቅየ ፡ መጸእኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ በዘለአክሙ ፡
ሊተ ፡ እስኩ ፡ አይድኡኒ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ኍኁሩ ፡
በዘጸዋዕክሙኒ ።

፲፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ረቡዕ ፡ ዮም ፡ እንዘ ፡ እጼሊ ፡
ጊዜ ፡ ተሠዓት ፡ ሰዐት ፡ በቤትየ ፡ አስተርአየኒ ፡
ብእሲ ፡ ይቀውም ፡ ቅድሜየ ፡ ወይለብስ ፡ ብርሃነ ፡
ወይቤለኒ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ጸሎትከ ፡ ወምጽዋትከ ፡
ተሰምዐ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለተዝካርከ ፡
ወይእዜኒ ፡ ለአከ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ ወይጸውዕዎ ፡
ለከ ፡ ለስምዖን ፡ ዘተሰምየ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘየኀድር ፡
ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ሰፋዪ ፡ ዘመንገለ ፡ ባሕር ፡ ወይነ
ግረከ ፡ ነገረ ፡ በዘተሐዩ ፡ ወዖቤሂ ፡ በእንቲአሁ ፡
ለአኩ ፡ ኀቤከ ፡ ሠናየ ፡ ገበርከ ፡ ዘመጸእከ ፡ ወይእ
ዜኒ ፡ ናሁ ፡ ኵልነ ፡ ሀሎነ ፡ ቅድሜከ ፡ ንግረነ ፡
ኵሎ ፡ ዘአዘዘከ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፭ ፤ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤሎ ፡ አማን ፡
ርኢኩ ፡ ከመ ፡ ኢያደሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለገጽ ፡
በኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ አላ ፡ ዘፈርሀ ፡ ወገብረ ፡ ጽድቀ ፡
ዕሩይ ፡ ውእቱ ፡ በኀቤሁ ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፯ ።
ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፲፮ ፤ ወፈነወ ፡ ቃሎ ፡ ለደቂቀ ፡ እሥራኤል ፡ ወዜነዎሙ ፡
ሰላመ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚእ ፡
ለኵሉ ፡ ተአምሩ ፡ ለሊከሙ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘኮነ ፡
በይሁዳ ፡ እኂዘ ፡ እምገሊላ ፡ እምድኅረ ፡ ጥምቀት ፡
ዘሰበከ ፡ ዮሐንስ ፡ በኢየሱስ ፡ ዘእምናዝሬት ፡ ዘቀ
ብዖ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወኀይለ ፤
ውእቱ ፡ መጽአ ፡ ወረድኦሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔገሎሙ ፡
ሰይጣን ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ።
ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፩ ።

፲፯ ፤ ወንሕነ ፡ ኵልነ ፡ ሰማዕቱ ፡ በዘገብረ ፡ በይሁዳ ፡
ወበኢየሩሳሌም ፡ ወቀተልዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ስቂሎሙ
ወእግዚአብሔር ፡ አንሥአ ፡ እሙታን ፡ በሣልስት ፡
ዕለት ፡ ወወሀቦ ፡ ያስተርኢ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡
ኦሕዛብ ።

፲፰ ፤ ወጌመነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወረሰየነ ፡ ሰማዕቶ ፡ ወበ
ላዕነ ፡ ወሰተይነ ፡ ምስሌሁ ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥአ ፡
እሙታን ፡ ፵ዓ ፡ ዕለተ ፡ ወአዘዘነ ፡ ከመ ፡ ንንግር ፡
ወንስብክ ፡ ለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሠይመ ፡
እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኮንነ ፡ ሕያዋን ፡
ወሙታን ፡ ወኵሎሙ ፡ ነቢያት ፡ ሰማዕቱ ፡ ከመ ፡
በስመ ፡ ዚአሁ ፡ የኀድግ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኃጢአቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ።
ሚክ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፰ ።

፲፫ ፤ ለእኔ ፡ ግን ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ማንንም ፡እንዳ
ልንቅፍና ፡ ርኩስም ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ አሳየኝ ፤
ስለዚህም ፤ ብትጠሩኝ ፡ ሳልጠራጠር ፡ መጣኹ ፡
አሁንም ፤ እስኪ ፡ ንገሩኝ ፤ እኔን ፡ የጠራችሁበት ፡
ነገሩ ፡ ምንድነው ? አላቸው ።

፲፬ ፤ ቆርኔሌዎስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ የዛሬ ፡ አራት ፡
ቀን ፡ ነው ፤ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በቤቴ ፡ ስጸልይ ፡እነሆ፡
የብርሃን ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡
ቆሞ ፡ ታየኝ ፤ ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ! በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ጸሎትህ ፡ ተሰማልህ ፤ ምጽዋትህም ፡ ታሰበ
ልህ ፤ አሁንም ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ልከህ ፡ በባሕር ፡
አጠገብ ፡ በአለችው ፡ በሰፈው ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡
ያለ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስን ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አስጠራው፤
የምትድንበትን ፡ ይነግርሃል ፡ አለኝ ፡ ያንጊዜውንም፡
ስለዚህ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ላክሁ ፤ አንተም ፡ ወደ ፡ እኛ ፡
መምጣትህ ፡ መልካም ፡ አደረግህ ፤ አሁንም ፡ እኛ ፡
ሁላችን ፡ በፊትህ ፡ ነን ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያዘ
ዘሽን ፡ ሁሉ ፡ ንገረን ፡ አለው ።

፲፭ ፤ ጴጥሮስም ፡ አፉን ፡ ከፈተ ፤ እንዲህም ፡ አለ ፤ እግዚ
አብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንዳያደላ ፡ በእውነት ፡አስ
ተዋልሁ ፤ ግን ፤ በሁሉ ፡ እርሱን ፡ የሚፈራና ፡ ቅን ፡
ነገርም ፡ የሚያደርግ ፡ ሕዝብ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ትክ
ክል ፡ ነው ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፯ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፲፮ ፤ ለእሥራኤል ፡ ልጆችም ፡ አካላዊ ፡ ቃሉን ፡ ላከ ፤
ሁሉን ፡ ፈጥሮ ፡ በሚገዛ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡
ሰላምን ፡ ሰበከላቸው ፤ ከናዝሬት ፡ በመጣው ፤ እግ
ዚአብሔር ፡ ኀይልን ፤ ሕይወትን ፡ ገንዘብ ፡ በአደረገ
ለት ፡ በኢየሱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሰበከው ፡ ጥምቀት ፡
በኋላ ፤ ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ በይሁዳ ፡ የኾነውን ፡ ነገር፡
ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችሁ ፤ እርሱ ፡ መጣ ፤ ሰይ
ጣን ፡ ያሸነፋቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አዳናቸው ፤ እግዚ
አብሔር ፡ በሀልውናው ፡ አለና ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፩ ።

፲፯ ፤ እኛም ፡ በይሁዳ ፡ አገርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በአደረ
ገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ፤ በዕንጨት ፡
ላይ ፡ ሰቅለው ፡ ገደሉት ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሦስተ
ኛው ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ አስነሣው ፤ ያስተ
ምርም ፡ ዘንድ ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ሰጠው ።

፲፰ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምስክሮቹ ፡ አድርጎ ፡ ሾመን ፡
ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ከተነሣም ፡ በኋላ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በላን ፡ ጠጣን ፤ በሕያዋንና ፡ በሙ
ታንም ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረ
ጠው ፡ እርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እን
ሰብክና ፡ እንመሰክር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘን ፤ ያመኑበ
ትንም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ እግዚአብሔር ፡
በእርሱ ፡ ስም ፡ እንዲያስተሰርይላቸው ፡ ነቢያት ፡
ሁሉ ፡ ምስክሮቹ ፡ ናቸው ። ሚክ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፰ ፡ ም ፡ ፻፭፱ ።

፻፱ ፤ ወእንዘ ፡ ይነግሮሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ወደንገፁ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ይሁዳ ፡ አይሁድ ፡ እለ፡ መጽኡ፡ ምስለ ፡ ጴጥሮስ ፡ እስመ ፡ ዲበ ፡ አሕዛብኒ ፡ ወረደ ፡ ጸጋሁ ፡ ለመንፈሠ ፡ ቅዱስ ፡ ወሰምዕዎሙ ፡ እንዘ ፡ ይነብቡ ፡ በነገረ ፡ በሐውርት ፡ ወይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፻፲ ፤ ወይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ መኑ ፡ እንከ ፡ ይክልዖሙ ፡ ከመ ፡ ኢይጠመቁ ፡ በስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምድኅረ ፡ ነሥኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ከማነ ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይጠመቁ ፡ በስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፭፱ ። ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ እምአሪተ ፡ ሙሴ ፡ ወውእቱ ፡ ፲ቱ ፡ ቃላት ፡ ዘጸሐፈ ፡ እግዚእነ ፡ በእደዊሁ ፡ ውስተ ፡ ጽላተ ፡ ዕብን ፡ ወወሀቦ ፡ ለሙሴ ፡ ገብሩ ፡ በደብረ ፡ ሲና ።

፪ ፤ ወነበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ቃላተ ፡ ወይቤ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ዘአውፃእኩከ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡ እምቤተ ፡ምቅናይ ፡ ቀዳሚ ፡ ትእዛዝ ፡ ኢታምልክ ፡ ካልአ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበሌየ ።

፫ ፤ ዳግም ፡ ትእዛዝ ፤ ኢትግበር ፡ ለከ ፡ አምላከ ፡ ከመ ዘበውስተ ፡ ሰማይ ፡ በላዕሉ ፡ ወከመ ፡ ዘበውስተ ፡ ምድር ፡ በታሕቱ ፡ ወኢበውስተ ፡ ማያት ፡ በታሕቲሃ ፡ ለምድር ፡ ኢትስግድ ፡ ሎሙ ፡ ወኢታምልኮሙ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ አምላክ ፡ ቀናዒ ፡ ዘእፈዲ ፡ ኃጢአተ ፡ አበው ላዕለ ፡ ውሉድ ፡ እስከ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡ ለእለ ፡ ይጸልዑኒ ፤ ወእገብር ፡ ሎሙ ፡ ምሕረተ ፡ እስከ ፡ ፲ቱ ፡ ፪ ፡ ትውልድ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅሩኒ ፡ ወየዐቅቡ ፡ ትእዛዝየ ።

፬ ፤ ሣልስ ፡ ትእዛዝ ፤ ኢትጸውዕ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ወኢትመሐል ፡ በሐሰት ፡ እስመ ፡ኢያነጽሖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘያነሥእ ፡ ስሞ ፡ በሐሰት ።

፭ ፤ ራብዕ ፡ ትእዛዝ ፤ ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ወአጽድቆታ ፤ ሰዱስ ፡ ዕለተ ፡ ተገበር ፡ ተግባረከ ፡ ወኵሎ፡ ዘተአዘዝከ ፡ ወበዕለት ፡ ሳብዕት ፡ ሰንበቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ኢትግበር ፡ ባቲ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ግብረ ፡ ኢአንተ ፤ ወኢወልድከ ፡ ወኢወለትከ ፡ ወኢገብርከ ፤ ወኢአመትከ ፡ ወኢብዕ ፡ ራይከ ፤ ወኢአድግከ ፡ ወኢኵሎሙ ፡ እንስሳከ ፡ ወፈላሲ ፡ ዘይነብር ፡ ኀቤከ ፡ እስመ ፡ በሰዱስ ፡ ዕለት ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡ ወባሕረ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡ ወአዕረፈ ፡ አመ ፡ ሳብዕት ፡ ዕለት ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፭፰ ፡ ም ፡ ፻፭፱ ።

፻፲፩ ፤ ጴጥሮስ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሲነግራቸው ፤ ይህንን ፡ በሰሙት ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረባቸው ፡ በይሁዳ ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፤ ከጴጥሮስ ፡ ጋር ፡ የመጡት ፡ ምእመናን ፡ አይሁድም ፡ ደነገጡ ፤ የመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ሀብቱ ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ወርዶአልና ፡ በየሀገሩ ፡ ቋንቋም ፡ ሲናገሩ ፡ ሰምተዋቸዋልና ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

፻፲፪ ፤ ጴጥሮስም ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እንዳ ይጠመቁ ፡ እንግዲህ ፡ የሚከለክላቸው ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እንዲጠመቁ ፡ አዘዛቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፻፭፱ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ሙሴ ፡ ከጻፋት ፡ አሪት ፤ እነዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጁ ፡ በድንጋይ ፡ ሠሌዳ ፡ ጽፎ ፡ ለባለሟሉ ፡ ለሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ የሰጠው ፡ ዐሥሩ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ።

፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡ ቃላት ፡ ተናገረ ፤ እንዲህ ፡ ብሎ ፤ ከምትገዛባት ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ያወጣኹኽ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ አለ ፤ መጀመሪያ ፡ ትእዛዝ ፤ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ።

፫ ፤ ሁለተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ ከላይ ፡ በሰማይ ፡ ባሉ ፤ ከታች ፡ በምድርም ፡ ባሉ ፤ ከምድር ፡ በታች ፡ በሚገኙ፡በውኃዎች፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ ፍጥረታት ፡ አምሳል ፡ ጣያት ፡ አታብጅ ፤ አትስገድላቸው ፤ አታምልካቸው ፡ለሚጠሉኝ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፤ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ የአባቶቻቸውን ፡ ኃጢአት ፡ ፍዳ ፡ በልጆች ፡የማመጣ ፤ ለሚወዱኝ ፤ ሕጌን ፤ ትእዛዜን ፡ ለሚጠብቁ ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ትውልድ ፡ ምሕረትን ፤ ቸርን ትን ፡ የማደርግ ፡ ለአምላክነቴ ፡ የምቀና ፡ አምላክ ፡ ፈጣሪኽ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ።

፬ ፤ ሦስተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ የፈጣሪህ ፡ የእግዚአብሔርን ስም ፡ ጠርተኽ ፡ በሐሰት ፡ አትማል ፤ ስሙን ፡ በሐሰት ፡ አንሥቶ ፡ የማለውን ፡ እግዚአብሔር ከፍዳ ፡ አያነጻውምና ።

፭ ፤ አራተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ አስብ እሷን ፡ ማክበርንም ፡ አስብ ፤ አስበኽም ፡ አክብራት ፤ ስድስቱን ፡ ቀን ፡ ሥራህን ፡ ሥራ ፤ የታዘዝከውንም ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፤ በሰባተኛዪቱ ፡ ቀን ፡ ግን ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዕረፍት ፡ናትና ፡ ታላላቁን፡ጥቃቅኑን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አትሥራባት ፤ አንተ ፤ ወንድ ፡ ልጅህ ፤ ሴት ፡ ልጅህ ፤ ወንድ ፡ ባርያህ ፤ ሴት ፡ ባርያህም ፡ አይሥሩ ፤ በሬህም ፡ አይታረስበት ፤ አሕያህም ፡ አይጫን ፤ ፈረስ ፡ በቅሎህንም ፡ ሁሉ ፡ አታውስ ፤ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ የሚኖር ፡ መጻተኛ ፤ በስድስቱ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይን ፤ ምድርን ፤ ባሕርን ፤ በሰማይ ፤ በምድር ፤ በባሕር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጥሮ ፡ በሰባተኛዪቱ ፡ ቀን ፡ ዐርፎአልና ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፹፱ ፡ ም ፡ ፻፴ ፡ ፻፴፭ ።

፮ ፤ ወበበይነዝ ፡ ባረካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዕለት ፡ ሳብዕት ፡ ወአጽደቃ ። ኀምስ ፡ ትእዛዝ ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ከመ ፡ ይኩንከ ፡ ጽድቀ ፡ ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ፡ በውስተ ፡ ምድር ፡ ዘወሀበከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ።

፯ ፤ ሳድስ ፡ ትእዛዝ ፤ ኢትቅትል ፤ ሳብዕ ፡ ትእዛዝ ፡ ኢትዘሙ ፤ ሳምን ፡ ትእዛዝ ፡ ኢትስርቅ ፤ ታስዕ ፡ ትእዛዝ ፡ ኢትስማዕ ፡ ላዕከ ፡ ቢጽከ ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ።

፰ ፤ ዐሥር ፡ ትእዛዝ ፤ ኢትፍቱ ፤ ብእሲተ ፡ ካልእከ ፡ ኢቤቶ ፤ ወኢገራህቶ ፤ ወኢገብሮ ፡ ወኢአመቶ ፤ ወኢላህሞ ፡ ወኢብዕራዮ ፡ ወኢኵሉ ፡ ዘውስተ ፡ እንስላሁ ፡ ወዘአጥረዮ ፡ አጥርዮ ፡ ቢጽከ ፤ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ይሬኢ ፡ ቃለ ፡ ወብርሃነ ፡ ዘለንጻስ ፡ ወቃለ ፡ ዘመጥቅዕ ፡ ወደብሩ ፡ ይጠይስ ፡ ወፈሪሆ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ቆመ ፡ ርሑቀ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፴ ።

፩ ፤ እምቃለ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተጎድጎ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወእለ ፡ ኢሐሰበ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወጌጋየሙ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢኀ ለቈ ፡ ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአቶ ።

፪ ፤ ብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ይሴብሑከ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘእምኀቤከ ፡ ረድኤቱ ፡ እግዚኦ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ንጹሓን ፡ በፍኖቶሙ ፡ ወእለ ፡ የሐውሩ ፡ በሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ የኀሥሡ ፡ ስምዖ ።

ምዕራፍ ፡ ፻፴፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ እምወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘዜነወ ፡ ማቴዎስ ፡ ሐዋርያ ፤ ወአመ ፡ ይመጽእ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ በስብሐቲሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ ፡ ምስሌሁ ፡ አሜሃ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ።

፪ ፤ ወያስተጋብኦሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወይፈልጦሙ ፡ ዘዘዚአሆሙ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ይፈልጥ ፡ ናላዊ ፡ አባግዐ ፡ እምአጣሊ ፡ ወያቀውሞሙ ፡ ለአባግዕ ፡ በየማኑ ፡ ወለአጣሊ ፡ በጸጋሙ ።

፫ ፤ አሜሃ ፡ ይብሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለእለ ፡ በየማኑ ፡ ንኡ ፡ ኀቤየ ፡ ቡሩካኑ ፡ ለአቡየ ፡ ትረሱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዘድልው ፡ ለክሙ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፤ እስመ ፡ ርኀብኩ ፡ ወአብላዕክሙኒ ፡ ጸማዕኩ ፡ ወአስተይክሙኒ ፤ ነግደ ፡ ኮንኩ ፡ ወተወከፍክሙኒ ፡ ዐረቁ ፡ ወአልበስክሙኒ ፡ ደወይኩ ፡ ወሐመጽክሙኒ ፡ ተሞቃሕኩ ፡ ወመጻእክሙ ፡ ኀቤየ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፹፱ ፡ ም ፡ ፻፴ ፡ ፻፴፭ ።

፮ ፤ ስለዚህም ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰባተኛዪቱን ፡ ቀን ፡ አበከራት ፤ አክብሮአትም ፡ አለ ፤ አምስተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ አባት ፡ እናትኽን ፡ እርዳ ፤ ጽድቅ ፤ ክብር ፤ ይኾንህ ፡ ዘንድ ፤ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠኽ ፡ ምድር ፡ ዘመንህ ፡ ይበዛ ፡ ዘንድ ።

፯ ፤ ስድስተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ ሰውን ፡ አትግደል ፤ ሰባተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ አትሰስን ፤ ስምንተኛ ፡ ትእዛዝ ፤ አትሰረቅ ፤ ዘጠነኛ ፡ ትእዛዝ ፤ በወንድምኽ ፡ ላይ ፡ በሐሰት ፡ አትመስክር ።

፰ ፤ ዐሥረኛ ፡ ትእዛዝ ፤ የወንድምህን ፤ የባልንጀራኽን ፡ ሚስት ፡ አትመኝ ፤ ቤቱን ፤ መሬቱን ፡ ወንድ ፡ ባሪያውን ፤ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ ላሙን ፤ በሬውን ፤ ከከብቱ ፡ ወገን ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ባልንጀራህ ፡ የገዛውን ፡ ሁሉ ፡ አትመኝ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ቃል ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤ የእሳት ፡ ብርሃን ፡ ያይ ፤ የነጋሪትን ፡ ድምፅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤ ተራራውም ፡ ይጨስ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ፈርቶ ፡ ርቆ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፻፴ ።

፩ ፤ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ከተናገረው ፤ ኃጢአታቸው ፤ የተሠረየላቸው ፡ ሰዎች ፡ የከበሩ ፤ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ ኃጢአታቸውንም ፤ በደላቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ያልቆጠረባቸው ፡ ሰዎች ፡ የከበሩ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአቱን ፡ ያልቆጠረበት ፡ ሰው ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

፪ ፤ በቤትህ ፡ የሚኖሩ ፤ ለዘላለሙ ፡ የሚያመሰግኑኽም ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ አቤቱ ፡ ረድኤቱ ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፤ በራሳቸው ፡ ንጹሓን ፡ የኾኑ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ አምልኩቱን ፡ የሚሹ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፻፴፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ሐዋርያው ፡ ማቴዎስ ፡ ከጻፈው ፡ ከቅዱስ ፡ ወንጌል ፤ የአብርሃም ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ መላእእክትን ፡ ሁሉ ፡ አስከትሎ ፡ በጌትነት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጌትነት ፡ ዙፋኑ ፡ ይገለጣል ።

፪ ፤ ሰዎቹን ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ይሰበስባቸዋል ፤ ጠባቂ ፡ በጎቹን ፡ ከፍየሎች ፡ እንዲለይ ፤ በየወገናቸው ፡ ይለያቸዋል ፤ ጻድቃንን ፡ በቀኙ ፤ ኃጥኣንን ፡ በግራው ፡ ያቆማቸዋል ።

፫ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፤ ንጉሥ ፡ በቀኙ ፡ የቆሙትን ፡ እንዲህ ፡ ይላቸዋል ፤ አባቴ ፡ የባረካችሁ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የተዘጋጀላችሁ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትን ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ኑ ፤ ብራብ ፡ አብልታችሁኛልና ፡ ብጠማ ፡ አጠጥታችሁኛልና ፤ እንግዳ ፡ ብሆን ፡ ተቀብላችሁኛልና ፤ ብራቁት ፡ አልብሳችሁኛልና ፤ ብታመም ፡ ጠይቃችሁኛልና ፤ ብታሰር ፡ መጥታችሁ ፡ ጠይቃችሁኛልና ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፮፻፱ ።

፩ ፤ አሜሃ ፡ ያወሥእዎ ፡ ጸድቃን ፡ ወይቤሉ ፡ እግዚኦ ፡ ግእዙኑ ፡ ርኢናከ ፡ ርኁበከ ፡ ወአብላዕናከ ፡ ጽሙ ፡ አከ ፡ ወአስተይናከ ፡ ወግእዙ ፡ ርኢናከ ፡ ነግደከ ፡ ወተወከፍናከ ፡ አው ፡ ዕሩቀከ ፡ ወአልበስናከ ፡ ግእዙ ፡ ርኢናከ ፡ ድውየከ ፡ ወሐወጽናከ ፡ አው ሙቁሐከ ፡ ወመጻእነ ፡ ኀቤከ ፡ ወነበብናከ ፡ ወእ ምዝ ፡ ያወሥኦሙ ፡ ንጉሥ ፡ ወይብሎሙ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ዘገበርከሙ ፡ ለእሉ ፡ እምእሉ ፡ ንኡ ሳን ፡ ሊተ ፡ ገበርክሙ ።

፪ ፤ አሜሃ ፡ ይብሎሙ ፡ ለእለ ፡ በጸጋሙ ፡ ሑሩ ፡ እም ኔየ ፡ ርጉማን ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘድ ልው ፡ ለሰይጣን ፡ ወለመላእክቲሁ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ርኁብኩ ፤ ወኢያብላዕከሙኒ ፤ ጸማዕኩ ፡ ወኢያስተይክሙኒ ፤ ነግደ ፡ ኮንኩ ፡ ወኢተወከፍክ ሙኒ ፤ ዐረቁ ፡ ወኢያልበስክሙኒ ፡ ደወይኩ ፡ ወኢ ሐወጽክሙኒ ፤ ተሞቃሕኩ ፡ ወኢመጻእክሙ ፡ ኀቤየ ፡ ወኢነበብክሙኒ ።

፯ ፤ አሜሃ ፡ ያወሥኡ ፡ ወይብሉ ፡ እግዚኦ ፡ ግእዙኑ ፡ ርኢናከ ፡ ርኁበከ ፤ አው ፡ ጽሙዓከ ፤ አው ፡ ነግ ደከ ፤ አው ፡ ዕሩቀከ ፡ አው ፡ ሙቁሐከ ፡ አው ድውየከ፡ወኢተልእክናከ ፤ አሜሃ፡ያወሥኡ ፡ወይ ብሎሙ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ዘኢገበርክሙ ። ለእሉ ፡ እምእሉ ፡ ንኡሳን ፡ ሊተ ፡ ኢገበርክሙ ።

፰ ፤ ወየሐውሩ ፡ እሉ ፡ ውስተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘለዓለም ፡ ወጻድቃንሰ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ።

፱ ፤ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘሃይማኖት ፡ እንተ ፡ አቅ ደምነ ፡ ወጸሐፍናሃ ፡ ወእመ ፡ ገበርከ ፡ ዘንተ ፡ትእ ዛዘ ፡ ወፀቀብከ ፡ ትእዛዘ ፡ ሃይማኖት ፡ አማን ፡ እንተ ፡ ትከውን ፡ ረድኦ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ኈር ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ ፡ ክብር ፡ ወስብሐት ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡ ወአሜን ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ።

፲ ፤ ተፈጸመ ፡ እመጻሕፍተ ፡ አበው ፡ መምህራነ ፡ቅድ ስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሐቲ ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ዘይነግር ፡ አናቅጸ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘአ ሚነ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ወትሥጉት ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሜን ።

፲፩ ፤ በረከቶሙ ፡ ቅድስት ፡ ወጎይለ ፡ ረድኤቶሙ ፡ ወሃ ይማኖቶሙ ፡ ፍጽምት ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወታ ድጎነነ ፡ እምተቃርኖቱ ፡ ለሰይጣን ፤ ወእምከረ ፡ ሰብእ ፡ እኩያን ፡ እስመ ፡ ንትአመኖሙ ፡ ለሥ ሉስ ፡ ቅዱስ ፡ እንበለ ፡ ወስኩ ፡ ወአንትኑ ፡ ለዓለመ ፡ ለዓለም ፡ አሜን ፡ ወአሜን ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፮፻፲ ።

፩ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ጸድቃን ፡ መቾ ፡ ተርበኽ ፡ አይተንኽ አብልተንኽ ፡ መቾ ፡ ተጠምተህ ፡ አይተንህ ፡ አጠ ጥተንኽ ፤ ምን ፡ ቀን ፡ እንግዳ ፡ ኾነህ ፡ አይተንህ ፡ ተቀብለንኽ ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ ተራቁተህ ፡አይ ተንህ ፡ አልብሰንህ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ ታመኽ ፡ አይ ተንኽ ፡ ጠይቀንህ ፤ ወይስ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ ታሥረህ ፡ አይተንህ ፡ መጥተን ፡ ጠየቅንህ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ንጉሡም ፡ ከእነዚህ ፡ ከወንድሞቼ ፡ ለአንዱ ፡ ማድረ ግ ፡ ለእኔ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይመልስላቸዋል ።

፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በግራው ፡ ያሉትን ፡ ለሰይጣን ፡ለሠ ራዊቱም ፡ የተዘጋጀ ፡ የማያልፍ ፡ ሥቃይ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ሒዱ ፡ ይላቸዋል ።

፫ ፤ ብራብ ፡ አላበላችሁኝምና፡ ብጠማ ፡ አላጠጣችሁ ኝምና ፤ እንግዳ ፡ ብኾን ፡ አልተቀበላችሁኝምና ፡ ብራቆት ፡ አላለበሳችሁኝምና ፡ ብታመም ፡ አልጠ የቃችሁኝምና ፡ ብታሰር ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥታችሁ ፡ አልጠየቃችሁኝምና ።

፬ ፤ በግራ ፡ ያሉ ፡ ኃጥኣንም ፡ አቤቱ ፡ መቾ ፡ ተርበኽ ፡ ተጠምተኽ ፡ ወይስ ፡ መቾ ፡ እንግዳ ፡ ኾነህ ፤ መቾ ፡ ታርዘህ ፤ ወይስ ፡ መቾ ፡ ታመህ ፤ ታስረህ ፤ አይተንህ ፡ አልጠየቅንኽ ፡ ብለው ፡ ይመልሳሉ ፤ ያንጊዜ ፡ ንጉሥም ፡ ከእነዚህ ፡ ከወንድሞቼ ፡ከነ ዳያኑ ፡ ለአንዱ ፡ አለ ፡ ማድረግ ፤ ለእኔ ፡ አለ ፡ ማድ ረግ ፡ ነው ፡ ብሎ ። ይመልስላቸዋል ።

፭ ፤ እነዚህ ፡ የማያልፍ ፡ ሥቃይ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡ ይሔዳሉ ፤ ጻድቃን ፡ ግን ፡ የማያልፍ ፡ ሕይወት ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይገባሉ ።

፮ ፤ አስቀድመን ፡ የጻፍናት ፡ የሃይማኖት ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ብትሠራ ፡ ይህንን ፡ ሃይማኖት ፡ አጽንተኽ ፡ ብትይዝ ፡ አንተ ፡ ከቮር ፡ አባቱ ፤ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋር ፡ ክብር ፡ ጌት ነት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በውነት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ትኾናለህ ፤ ዛሬም ፤ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ፡ ይኹን ፡ ይኹን ።

፯ ፤ ሐዋርያት ፡ ያሳመኗት ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ካሳ መኑ ፡ ከአበው ፡ መጻሕፍት ፡ የተሰበሰበ ፤ ሥላሴ ፡ በአካል ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ መኾናቸውን ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድም ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ስለማመን ፡ የተነገረ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸር ነት ፡ ተፈጸመ ፡ አሜን ።

፲፩ ፤ የከበረች ፡ በረከታቸው ፡ ድል ፡ የማትነጣ ፡ ረድኤ ታቸው ፤ ጥርጥር ፤ የሌለባት ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ከእኛ፡ ጋር ፡ ትኹን ፤ ሥሉስ ፡ ቅዱስን ፡ ያለ ፡ ማጕደል ፤ ያለ ፡ መጨመር ፡ እናምናለንና ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ከመከሩት ፡ ምክር ፤ ከሰይጣን ፡ ጠላትነት ፡ ታድ ነን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።